# — ክፍል አራት —

# መንፈስ ቅዱስ በደኅንነት ሥራ

# 12

# ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ

## 1. መለኮታዊ ቸርነት እና ሉዓላዊነት

የእግዚአብሔር ቸርነትና ሉዓላዊነት ትምህርት፥ የአምላክ ኃይል በዳነው ላይ ብቻ ሳይሆን፥ ባልዳነው ዓለም ላይም እንደሚሠራ ያስተምራል። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በቅድሚያ ለክርስቲያኖች ቢሆንም፥ የእግዚአብሔር አብን እና የእግዚአብሔር ወልድን ፈቃድ በዓለም ውስጥ ለመፈጸም እንደሚሠራም የተረጋገጠ ነው። ዝብርቅርቅ ባሉና ኃጢአት በሰፈነባቸው ወቅቶች ውስጥም መንፈስ ቅዱስ የሚሠራ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጥልናል። በዘፍጥረት 1፡2 የተጠቀሰው ሁኔታ መሬት ያለ መንፈስ ቅዱስ ነበረች ማለትን አያመለክትም። በኖኅ ዘመን የነበረው ኃጢአተኛ ትውልድም ከኃጢአቱ በመንፈስ ቅዱስ ታግዶ ነበር (ዘፍጥ. 6፡3)። በብልሹው ዘመነ መሳፍንት ጊዜ፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታጠቀው ሳምሶን ኖሯል። ከምርኮ በፊት በእስራኤል ውድቀት ዘመን የነበሩ ነቢያት በኃጢአተኛና በማያምን ሕዝብ መካከል ለማገልገል፥ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ኃይል የሚያሳዩ ሕያው ምስክሮች ነበሩ። በአዲስ ኪዳንም እግዚአብሔር፥ "ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ" እንደሚፈልግ እንድናውቅ ተጽፏል (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በየትኛውም ዘመን ለሚኖረውና ላላመነ ትውልድ፥ በተለይ ደግሞ በዓለም ባለችው ቤተ ክርስቲያን በቋሚነት በሚኖርበት በዚህ የጸጋ ዘመን፥ የተለየ አገልግሎት እንዳለው ለመመልከት እንችላለን።

## 2. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ መጠን

መንፈስ ቅዱስ ላልዳኑ ሕዝቦች የሚሠራው ጠቅላላ ሥራ አንዳንድ ጊዜ "ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ" [Common Grace/ካመን ግሬይስ] በመባል ይታወቃል። ይህ ሥራ ኃጢአት መከልከልንና ወንጌል የመግለጥ ተግባርን ሁሉ ይጨምራል። ለምሳሌ ቻርልስ ሆጅ ለሁሉ ስለተሰጠ ጸጋ ሲናገር፡- "መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም አቅጣጫ ይሁን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፥ እርሱ የእውነት፥ የቅድስናና የሕይወት መንፈስ በመሆኑ ሰዎች እውነትን እንዲቀበሉና እንዲያውቁ በአእምሯቸው ላይ ተጽዕኖ በማድረግ፥ ኃጢአትን በመከልከል፥ ለእውነት በማነቃቃት፥ ጥበብንና ብርታትን በመስጠት መልካም በምንለው ሁኔታ ውስጥ ሁሉ አለ... ይህን ነው በሥነ-መለኮት ቋንቋ ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ የምንለው" ብሏል።

ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጆን ካልቪን በሚከተለው መልክ ገልጦታል፡-

"ለሰው ልጆች የጋራ ጥቅም የሚውሉ እጅግ አስደናቂ የሆኑ መለኮታዊ የመንፈስ ስጦታዎች፥ እርሱ ደስ እንደሚለውና እንደሚፈቅድ የሚያከፋፍላቸው መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። ለማደሪያው ድንኳን ግንባታ ያስፈልግ የነበረን ጥበብ እና ችሎታ የእግዚአብሔር መንፈስ ለባስልኤልና ለኤልያብ መስጠት የነበረበት ስለዚህ ነው። በሰው ልጅ ሕይወት እጅግ አስደናቂ የምንላቸው እውቀቶች በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት ቢገለጡልን ልንደነቅ የማይገባንም ከዚህ የተነሣ ነው። ይህን በማድረጉም እግዚአብሔር ከኃጢአተኞች ጋር ግንኙነት መፍጠሩ ለምንድነው ብለን የምንጠይቅበት ምክንያት የለም። ታማኝ በሆኑ ሰዎች ላይ ስለሚያድረው የእግዚአብሔር መንፈስ በምንናገርበት ጊዜ፥ እኛን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አድርጎ የቀደሰንን መንፈስ ማለታችን ነው። እንዲሁም የዚህ መንፈስ ኃይል እንደ ተፈጥሮ ሕግ ፍጥረታት እንዲባዙ፥ የተፈጥሮ እንቅስቃሴያቸውም በሥርዓቱ እንዲቀጥል፥ የዝርያቸውም ባሕርይ እንዲጠበቅ ያደረገ ነው። ስለዚህ በፊዚክስ፥ በሎጂክ [Logic]፥ በሒሳብና በሌሎችም የሳይንስ ጥበቦች እንረዳ ዘንድ ጌታን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፥ እግዚአብሔርን በማይፈሩ ሰዎች ድካም እና አገልግሎት የተገኙ ቢሆኑ እንኳን ልንጠቀምባቸው ይገባል። ከእግዚአብሔር የተለገሱንን እነዚህን ነጻ ስጦታዎች ከመጠቀም ቸል ብንል ቸልተኝነታችን በሚያስከትለው ውጤት ከመሠቃየት በቀር ምርጫ የለንም።"

## 3. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ጠቃሚነት

መንፈስ ቅዱስ ላልዳኑ ሰዎች ወንጌልን ለመግለጥ የሚያከናውነው ሥራ፥ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለመፈለግ ከሚያከናውነው ሰፊ ሥራ አንዱና ዋናው ነው። ወንጌልን ያለ እርሱ እርዳታ መረዳት አይቻልም። ሥራው ወንጌልን ለመስበክና በክርስቶስ ኢየሱስ በሚሆን እምነት ሁለንተናዊ ጥሪት ማድረግን ለመግለጥ የታቀደ ነበር። "ለሁሉም የተሰጠ ጸጋ" እግዚአብሔር ለተመረጡት ከሚያደርገው "ውጤታማ ጥሪ" የሚቀድም ነው። ወንጌልን ለዓለም በመግለጥ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊነቱ፥ ከእግዚአብሔር እቅድ አንጻር ብቻ ሳይሆን፥ ወንጌል በሚገባ እንዲሰበክ ከማድረግ ጭምር ነው። ነፍሳትን ለክርስቶስ ለመማረክ ፍላጎት ያለው ክርስቲያን ሁሉ ይህን ጉዳይ በጥንቃቄ ማጥናት አለበት። ምክንያቱም እግዚአብሔር ባልዳኑ ነፍሳት ላይ ስላለው አሳብ መመሪያ የሚሰጥ ስለሆነ ነው።

ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሊነጣጠሉ በማይችሉ ሁለት ጠቃሚ ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

አንደኛው፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከመለኮታዊ የቸርነት ሥራ ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ ኃጢአትን በመከልከልና የዓለምን የኃጢአት ሂደት በማገድ የሰውን ልጅ ታሪክ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ እንዲዋጥ ማድረግ ሲሆን፥ ሁለተኛው፥ የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያመለክቱ መገለጦች የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ሲሆኑ፥ የመዳንን መንገድ በተፈጥሯዊ አእምሮው መረዳት ለማይችለው ሰው የደኅንነትን መንገድ ተረድቶት እንዲቀበለው ማድረግ ነው። በዘመነ ክርስትና ሁሉ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ትኩረት፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የደኅንነትን መንገድ ለጠፉ ነፍሳት ማመልከትና የሚያድን እምነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ይህን አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ለመደገፍ የምናቀርባቸው ጥቅሶች ጥቂት ቢሆኑም፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር ግን እጅግ አስፈላጊ ነው።

ከዓለም ጋር ግንኙነት ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከበርካታ ምክንያቶች የተነሣ በጣም አስፈላጊ ነው። ሰይጣን ኃይል አለው፤ ክርስቲያኖችንና እውነትን ይጠላል። ስለዚህ ለወንጌል ስርጭት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ ለማመቻቸትና በኃጢአተኛው ዓለም ውስጥ ሥርዓትን ለማስከበር ይህን ኃይል መታገል ያሻል። በመሆኑም ኃጢአትን ከመከልከልና ክርስቲያን በዓለም ሳለ የሚኖረውን አንጻራዊ ነጻነት ከማብራራት አኳያ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን ለጠፉ ነፍሳት የመግለጥ ሥራ፥ በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የመጥራት ሥራውን ለመፈጸም እጅግ አስፈላጊ ነው። የሰውን ድካም በማገዝ ነፍሳት እንዲድኑ ያደርጋል። ስለዚህ ይህ መሠረታዊ ትምህርት የወንጌል ሥራ ሙሉና አርኪ ውጤት እንዲያገኝ በማድረግ ጠቀሜታ አለው።

## 4. የጸጋ ለሰው ልጅ አስፈላጊነት

የአዳም ውድቀት ብዙ ችግሮችን አስከትሏል። ከእነዚህም መካከል ኃጢአት ወደ ሰው ዘር ሁሉ መተላለፉ፥ የሰዎች ከክርስቶስ ተለይተው መንፈሳዊ ሞት መሞታቸው፥ በግልጥ የሚታይ የውድቀት ባሕርይ መያዛቸውና ለዚህ ጥናታችን በጣም አስፈላጊ የሆነውን ጉዳይ፥ ማለት የእግዚአብሔርን እውነት ለመረዳት አለመቻላቸው ይገኙበታል። የሰው ልጅ ደካማ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ መስክሯል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፡14፥ "ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም" ተብሎ በቀጥታ ተጽፏል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡18 ደግሞ ወንጌል ለሚጠፉት ሞኝነት እንደሆነ ተገልጧል፡- "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።"

ያልዳኑ አሕዛብ በጨለማ እንደሚመላለሱም ተገልጧል፡- “እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸው ደንዳናነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ፤ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ” (ኤፌ. 4፡18)። በሮሜ 8፡7 መሠረት ፍጥረታዊ አእምሮ ለእግዚአብሔር ሕግ መገዛት አይችልም፡- “ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና መገዛትም ተስኖታል።” ክርስቶስ በዮሐንስ 6፡44፥ “የላከኝ አብ ካሰበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም” ማለቱ ተፈጥሮዊው ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት እንደማይችል መናገሩ ነው ። ከፍጥረታዊ የብቃት ጉድለት ሌላም ሰይጣን የጠፉትን ሰዎች ልብ አሳውሯል (2ኛ ቆሮ. 4፡4)። እግዚአብሔር ካልረዳውና ሁኔታዎችን ካልለወጠለት በቀር የሰው ልጅ ተስፋ በሌለው ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ፍጡር ነው።

በሰው በኩል ጉድለት (ያለመብቃት) የሚመጣው ጠቅላላ አቋሙ የተበላሸ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔርንና ጸጋውን ባለማወቅ ስሜቱን፥ ፍላጎቱንና አዝማሚያውን ብቻ ሲያጣምምና ማስተዋሉ ሲጨልምበት ነው። የሰው ልጅ በኃጢአት በመውደቁ ክፉ እና ደግን የመለየት አቅሙን አላጣም። ከውድቀት በኋላ እንኳን ኃላፊነት ያለበትና አንጻራዊ ነጻነት ያለው ነው። የማስተዋል ችሎታው እስካሁን ስላለ ምናልባት በዚህ አንጻር ያልተለመደ ብርታት ልናይበት እንችላለን። ለመልካም ነገር ያለው የተቃና አሳብ መጣመምና የክፋት አዝማሚያ ከወደቀው ተፈጥሮው የመነጨ ሲሆን፥ መነሻው ደግሞ በተፈጥሮው ጽድቅ ወዳድ የሆነውን እግዚአብሔር ለመቀበልና በዚያም ደስ ለመሰኘት ፈጽሞ አለመቻሉ ነው። የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እንዲጠላ የሚያደርገው ዋነኛ ምክንያት እርሱን አለማወቁ ነው። የሰው ፈቃድ፥ የተፈጥሮ ብቃትን የማለፍ ኃይሉ፥ ከሰው ልጅ ውድቀት በፊትም ሆነ አሁን ምንም ልዩነት የለውም። በራሱ የእግዚአብሔርን እውነት ለመረዳት ጨርሶ አይችልም። ስለዚህ የዚህ ችግር መፍትሔ የሚገኘው፥ ፍጥረታዊ ሰው በሚደርስበት የእድገት፥ ወይም የተዳፈነ ችሎታን በማጎልበት ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ኃይል በሚገለጥበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጭ እግዚአብሔር ለጠፋው የሰው ዘር ሳይገለጥ የሚቆይ፥ የክርስቶስ ሞትም ለሰው ልጅ የማይጠቅም፥ እግዚአብሔር የተመረጡትን ለማዳን የነበረው ዓላማም ሊሟላ ጨርሶ የማይችል ይሆን ነበር። ስለዚህ የዚህ መሠረታዊ ትምህርት ጠቃሚነት ጠንቃቃ ጥናትን የሚጠይቅ ይሆናል።

## 5. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ባሕርያት

አስቀድመን እንደገለጥነው “ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ” የሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስ በዓለም ላይ ስለሚያከናውነው ሥራ የሚናገሩ ብዙ አሳቦችን የሚያጠቃልል ነው። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ፥ የሰው ዘር የእግዚአብሔርን ነገር

ለመቀበል ያለበትን ችግር ለመረዳት ልዩ አስተዋጽኦ አለው። በዚህ ስሜት ስናየው ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ በማንኛውም ጊዜ በምንም ዓይነት መንገድ የተሰጠውን የእግዚአብሔር እውነት የሚገልጥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው። አርምኒያን [Arminian]* የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ይህን ጸጋ "በቂ ጸጋ" [Sufficient Grace/ሰፊሸንት ግሬይስ] ብለው ይጠሩታል። ይህን የመሰለና ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ እምነትን ሊያመጣ የሚችል የተሟላ መገለጥ ይሰጣል ይላሉ። "ውጤት አስገኝ ጸጋ" [Efficacious Grace/ኤፊኬሽስ ግሬይስ]፥ ወይም "የማይገታ ጸጋ" [Irresistible Grace/ኢሬዚስተበል ግሬይስ] በመባል የሚታወቀውም ቢሆን በዚሁ እውነት ክልል ውስጥ ያለ ሲሆን፥ በባሕርይና በአሠራሩ ግን የተለየ ነው። ውጤት (ወይም 'ሥርየት') አስገኝ ጸጋ የምንለው፥ ወንጌልን ውጤታማ በሆነ መንገድ በመግለጥ ሰዎችን ወደሚያድን እምነት የሚመራ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው። ይህን የጸጋ ጉዳይ፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጤትን በሚያስገኝ ጸጋ ውስጥ፥ በሚለውና በሚቀጥለው ምዕራፍ በሰፊው እንመለከተዋለን።

*ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያለው ግንኙነት።* የእግዚአብሔር ቃል ለጠፉ ነፍሳት መሰበክ እንዳለበት ቅዱሳት መጻሕፍት አበክረው ይናገራሉ። ወንጌላችን "የማዳን ኃይል ነውና" (ሮሜ 1፡16)። ሰዎች ደግሞ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ ታዘዋል። ለዚህ ነው ጳውሎስ ይህን ጥያቄ በማንሣት "ካልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?" (ሮሜ 10፡14) ብሎ "እምነት ከመስማት ነው መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው" ወደሚል ማጠቃለያ (ሮሜ 10፡17) የደረሰው። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ የተጠቀሰው፥ እግዚአብሔርንና ጸጋውን ለዓለም ለመግለጥ የሚያገለግል መለኮታዊ መንገድ ነው። ይህ ቃል ነው የመንፈስ ሰይፍ ተብሎ የተጠራው። እግዚአብሔር ራሱን ለመግለጥ ሲፈልግ ሌሎች የተለያዩ መንገዶች ቢኖሩትም የደኅንነትን መንገድ ለሰው ልጅ የገለጠው ሊሰበክና ሊነበብ በሚገባው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በአንድ ወይም በሌላ መልክ ቅዱሳት መጻሕፍት ባይሰጡን ኖሮ ደኅንነት ሊገኝ አይችልም ነበር። ስለዚህ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመምራት የሚፈልጉ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ አለባቸው።

እንደ ጥምቀትና ቅዱስ ቁርባን ያሉት ቅዱሳት ምሥጢራት ለወንጌል ምስክርነት የሚያበረክቱት ድርሻ አላቸው። የእነዚህ ምስጢራት ጥቅም በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከሚገባ በላይ ስፍራ የተሰጣቸው ቢሆንም፥ የወንጌልን መልእክት በአምሳያነት ለመግለጥ የየራሳቸው ስፍራ

---

* የአርምኒያን [Arminian] የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ስማቸውን የወሰዱት የዚህ ትምህርት ጀማሪ ከነበረው ከጃኮበስ አርምኒየስ [Jacobus Arminius] ነው። አርምኒየስ ከ1559-1609 ዓ.ም. የኖረ የሆላንድ ተወላጅ ነው።

አላቸው። በተለይም ቅዱስ ቁርባን “ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን የምንናገርበት” በመሆኑ በሚገባ መካሄድ አለበት (1ኛ ቆሮ. 11፡26)።

የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ መሠረታዊ ትምህርት ጋር ያለውን ግንኙነት ስንመለከት፥ ከመሠረታዊ ትምህርቱ አንጻር ሁለት ተቃራኒ አቅጣጫዎችን ለማየት ይቻላል። ሉተራውያን* [Lutherans] የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የእግዚአብሔር ቃል የተለየ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የማያስፈልገው፥ ለውጤታማነት በራሱ ኃይል ያለው ነው ብለው እስኪናገሩ ድረስ በእግዚአብሔር ቃል ሕያው ባሕርይ ላይ ያተኩራሉ (ዕብ. 4፡12)። የሉተራን ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ በዓለም ውስጥ መኖሩንና ኃይሉን ሙሉ ለሙሉ ብትቀበልም፥ ሥራው ግን በቃሉ ላይ ብቻ እንደተወሰነ ታመለክታለች። የሉተራውያንን አቋም ቻርልስ ሆጅ ባጭሩ ሲገልጠው፥ “ይህ መለኮታዊ ውጤታማነት በቃሉ

---

* የሉተራን ቤተ ክርስቲያን የተሰየመው፥ ማርቲን ሉተር (1483-1546) በተባለው ሰው ስም ነው። ማርቲን ሉተር በጀርመን አገር በአይስሌበን ከተማ ተወለደ። በ1506 ዓ.ም. የአውግስቲኒያን መነኩሴ፥ በ1507 ደግሞ ቄስ ሆነ። ትምህርቱን የተከታተለው በኤርፈርት ዩኒቨርስቲ ሲሆን፥ በ1512 ዓ.ም. ከዊተንበርግ ዩኒቨርስቲ ዶክትሬቱን ተቀብሏል። እዚያው እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አስተምሯል።

በ1510 ዓ.ም. ሮምን በጎበኘበት ጊዜ የካህናቱ ብልሹ ድርጊት በጣም ያሳዘነው ሲሆን፥ አንዳንዶቹ የሮም ቤተ ክርስቲያን ትምህርቶችም አጠያያቂ ሆኑበት። በ1517 ዓ.ም. ጳጳሱ በሮም ከተማ የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ ክርስቲያን ለማሠሪያ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ያስችል ዘንድ በዊተንበርግ አጠገብ “ኢንደልጀንስ”** እንዲሸጥ ጃን ተጸል የሚባል ሰው ላከ። ሉተርም ይህን ድርጊት አጥብቆ ተቃወመ። ለውይይት ሊቀርቡ ይገባል ያላቸውን 95 ነጥቦች ዘርዝሮ በመጻፍ በቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ ለጠፈ። ሉተር የሮም ቤተ ክርስቲያንን ሥልጣንና ድርጊት የተቃወመ ሲሆን፥ አሳቡም በብዙ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር። በመጨረሻም በ1520 ዓ.ም. የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ሉተር እምነቱን እንዲቀይር ወይም እንዲወገዝ አዘዘ። ሉተር በወርምስ ከተማ ከቤተ ክርስቲያኑ ባለሥልጣናት ጋር ቢገናኝም፥ ትእዛዙን አልተቀበለም። የመከላከያ አሳቡን በዚህ ታዋቂ በሆነ አባባሉ ነበር የደመደመው:- “ሕሊናዬ የእግዚአብሔር ቃል ምርኮኛ ነው...እዚህ ቆሚያለሁ፤ ምንም ነገር ለማድረግ አልችልም።”

ሉተር ወደ ቤቱ ሲሄድ ከመንገድ በጓደኞቹ ታፍኖ ለአንድ ዓመት ያህል በምሽግ ተደብቆ ኖረ። በዚህ ቦታም ታላቅ ሥራ መሆኑ የተረጋገጠለትን፥ መጽሐፍ ቅዱስን የሕዝቡ ቋንቋ ወደሆነው ጀርመንኛ የመተርጎም ሥራ ጀመረ።

---

** “ኢንደልጀንስ” [Indulgence] በሕይወት ያሉ ሰዎች ከጊዜያዊ ቅጣት እንደሚድኑ ተስፋ የሚሰጥ፥ ለሞቱ ደግሞ ከፐርግቶሪ*** በቶሎ ነጻ እንዲሆኑ የሚያደርግ በቤተ ክርስቲያን የሚሸጥ የምስክር ወረቀት ነው።

---

*** “ፐርግቶሪ” [Purgatory] በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት፥ አማኞች ከሞቱ በኋላ ሙሉ ይቅርታ ስላልተደረገለት ኃጢአታቸው የሚሠቃዩበትና መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የሚጠብቁበት ቦታ ነው።

ውስጥ ያለና ከቃሉም ለይተን ልናየው የማይቻለን ነው›› ብሏል። ይህ አመለካከት ያለበት ትልቅ ችግር፥ ብዙ ያልዳኑ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ቢሰሙም ሆነ ቢያነቡ በሕይወታቸው ምንም ለውጥ ያለመከሠቱ ነው። ሉተራውያን ለዚህ ምላሽ፥ መንፈስ ቅዱስ ሥራውን የሚሠራበት ኃይል የተመሠረተው በእምነት ላይ ነው ይላሉ። አንድ ሰው የማያውቀውን ነገር እንዴት ሊያምን እንደሚችል ለመግለጥ ግን አስቸጋሪ ነው። እውነቱ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ፥ ያላመኑ ሰዎችን ይወቅሳል። የደኅንነትን መንገድ ይገልጥላቸዋል፤ ይህም ሆኖ አንዳንዶች ከወንጌል እውነት ያፈገፍጋሉ። መንፈስ ቅዱስ ላላመኑ ሰዎች ወንጌልን በመግለጥ ረገድ ያለው ሥራ ግን፥ የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ተግባር እንጂ በሰዎች መቀበልና አለመቀበል የሚወሰን አይደለም። የብዙ ክርስቲያኖች ልምምድ፥ ሰው ስለ ደኅንነት ተረድቶ ለተወሰነ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ሊያምፅና ክርስቶስን ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆን ሊቆይ፥ በመጨረሻም በክርስትና ወደማመን ውሳኔ ላይ ሊደርስ እንደሚችል ያሳያል።

ለሁሉ ስለተሰጠ ጸጋ በተቃራኒ አቅጣጫ የያዘው ሌላ መሠረታዊ ትምህርት፥ የእግዚአብሔር ቃል ጨርሶ አያስፈልግም የሚል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ኃጢአትን ከመከልከል፥ ቸርነትን ከማድረግ፥ ከእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት (አድራጊነት) አጠቃላይ ሥራ ጋር የግድ ግንኙነት አለው ማለት ባንችልም፥ የወንጌሉ የምስራች የሚመጣው ግን በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ውስጥ ድርሻ የለውም የሚለው አንዱ ከረር ያለ አቋም በሁለት ተቃራኒ የሥነ-መለኮት አመለካከቶች ይደገፋል። እነርሱም ‹‹ራሽነሊዝም››* [Rationalism] እና ‹‹ሚስቲሲዝም››** [Mysticism] ናቸው። በእርግጥ ‹‹ዲይስቶች›› የሚያስቡት፥ እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ እንደማይኖርና ማንኛውም መንፈሳዊ ልምምድ የሰው አእምሮ የተለመደ ተግባር ነው ብለው ነው። በእነርሱ አመለካከት ለሁሉ የተሰጠ አጠቃላይ ጸጋ ሙሉ ለሙሉ የሰው ልጅ በእውቀቱ ብርታት የደረሰበት ተፈጥሮአዊ ሂደት ነው። ከ‹‹ዲይስቶች›› ይልቅ ለዘብ ያለ አቋም ያላቸው ‹‹ፐሌጂያን›› [Pelagian] በመባል የታወቁት ሲሆኑ፥ በእነርሱ አስተሳሰብ ሰው በተፈጥሮው እውነትን ለመረዳትና ከዚህ መረዳቱ አንጻር የራሱን

---

* ራሽነሊዝም፡- ይህ ቃል የሚያመለክተው፥ በመረጃ ላይ የተመረኮዘ ነገር የሚከተል የአስተሳሰብ መርህን ነው።

---

** ሚስቲሲዝም፡- ይህ ቃል ከራሽነሊዝም ተቃራኒ የሆነና አንድ ሰው በስሜቱ የሚመራበት የአስተሳሰብ መርህ ነው። (ቃሉ ሰው ከመናፍስት ዓለም ጋር አንድ ዓይነት ግንኙነት ላይ እንዲደርስ የማድረግ የጠለቀ አሳብንም አዝሏል። ይህ ልምምድ እንደ ግለሰቡና የእምነት ቡድኑ ሁኔታ ይለያያል።)

ውሳኔ ለማድረግ የሚችል ነው። የራሽናሊዝም አሳብ የቅዱሳት መጻሕፍትን መገለጥ በሁሉም አቅጣጫ የሚቃወም ሲሆን የካልቪን ሥነ-መለኮት ትምህርት ተከታዮች* ይህን ትምህርት የተሳሳተ ነው በማለት በትኩረት አልተመለከቱትም።

የ"ሚስቲክ" [Mystic] አሳብ ከፍ ብለን ያየነውን አመለካከት በቀጥታ የሚቃረን ነው። የዚህ አስተሳሰብ አራማጆች እግዚአብሔር ሊቀበሉት ፈቃደኛ ለሆኑ ሁሉ ቀጥተኛ መገለጥን ይሰጣል በማለት የተገለጠው እውነት ተቀባዮቹ በሚገባ ሊረዱት የሚችሉት ነው ይላሉ። ይህ አመለካከት ከክርስትና ጋር ያላቸውን የአስተሳሰብ ግንኙነት ሁሉ በማለፍ ያልዳኑ ሰዎች እንኳ ሊረዱት የሚችሉት ዓይነት ልዩ መገለጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ማግኘት ይችላሉ የሚለውን ስሕተት ሁሉ ይጨምራል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሳይሰሙ እውነተኛ ደኅንነት ሊያገኙ አይችሉም። ወንጌል ወዳልደረሰበት አካባቢ የሚሄዱ ሚሲዮናውያን እንኳን፥ ክርስቲያናዊ ኅብረተሰብ ወይም በልዩ መገለጥ የዳነ አንድ ክርስቲያን አግኝተው አያውቁም። የእነርሱ አመለካከት የተመሠረተው በቃሉ፥ ወይም በልምምድ ሳይሆን፥ በመላ ምት ላይ ስለሆነ ውድቅ ሊሆን ይገባዋል።

መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውነው ሥራ በተለይ የማያምኑ ሰዎች ወንጌልን እንዲረዱ ማድረግ ነው። መንፈስ ቅዱስ ቃሉ በሚሰበክበት ጊዜ በተፈጥሮው ለዚህ እውነት ዕውር የሆነ ሰው እንዲገነዘብ ይረዳዋል። ለሚጠፉ ሰዎች የመጸለይ አስፈላጊነት ከግንዛቤ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ይህን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ጠቃሚነት ማወቅ ተገቢ ነው።

*ለዓለም የሚሰጠው የመገለጥ መጠን።* መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን በዓለም ላይ እንዲኖር ያስፈለገበት ተቀዳሚ ምክንያት፥ እውነትን ለዓለም የመግለጥ አገልግሎቱ ነው። እንደ ክርስቶስ ቃል፡- "እርሱ መጥቶ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ጽድቅ፥ ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል" (ዮሐ. 16፡8)።

---

* ጆን ካልቪን [John Calvin](1509-1564) የተወለደው በፈረንሣይ ሲሆን፥ አብዛኛውን ጊዜውን በሥራ ያሳለፈው ግን ጄኔቫ (ስዊዘርላንድ) ውስጥ ነው። ሉተር [Luther] የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ትቶ ከሄደ ከ15 ዓመታት በኋላ፥ እርሱም በ1534 ዓ.ም. ይህችን ቤተ ክርስቲያን በመልቀቅ ከተሃድሶ ትምህርት መሪዎች መካከል አንደኛው ለመሆን በቃ። ዛሬ ትምህርቱ "ሪፎርምድ ቲያሎጂ/Reformed Theology"** በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ ይህም ለፕሬስቢቴሪያን እና ለ"ሪፎርምድ" ቤተ ክርስቲያናት መሠረት ነው።

---

** "ሪፎርምድ" የሚለው ቃል፥ በእንግሊዝኛ የሥነ-መለኮት ሊቃውንትን ለማመልከት፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን ዓይነቶችን ለመግለጥ በጥቅም ላይ የሚውለው የካልቪናውያንን ትምህርት ከሉተራውያንና ከአናባፕቲስት ለመለየት ነው። የዚህ ትምህርት መሠረታዊ ጅማሬ የመጀመሪያው የአዳሽ እንቅስቃሴ መሪ ከነበረው የዙሪክ (የስዊዘርላንድ) ሰው ኧልሪክ ዝዊንግሊ፥ እና "የክርስትና ሃይማኖት ተቋም" የሚለውን ምርጥ የፕሮቴስታንት የሥነ-መለኮት ትምህርት ሥራን ከጻፈው የጄኔቫው ጆን ካልቪን የወጣ ነው።

ይህ ሦስት ዘርፍ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ቀጥሎ ባለው ክፍል ውስጥ የበለጠ ግልጥ ሆኖ ቀርቧል። ዓለምን ስለ ኃጢአት የመውቀስ ሥራው በተለይ ያለማመንን ኃጢአት በሚመለከት ባልዳነው ሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚያመለክተውን ጉዳይ የመግለጥ ሥራ እንደሆነ በቁጥር ዘጠኝ "ስለ ኃጢአት በእኔ ስለማያምኑ ነው" በሚለው ቃል ተገልጧል። በክርስቶስ ሞት ምክንያት የኃጢአት ኩነኔ የለም። የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ጥያቄ ሁሉ የሚያሟላ ሆኗል። ያልዳኑ ሰዎችን የመጨረሻ ዕጣ የሚመለከት ወሳኝ ጥያቄ በክርስቶስ የማመንና ያለማመን ጉዳይ ብቻ ነው። ባሕርይን ከማነጽ ወይም በተሻለ የቅድስና ሕይወት መኖርን ከማበረታታት በላይ፥ ለመዳን በክርስቶስ ማመን የግድ አስፈላጊ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ ግልጥ ያደርገዋል።

መንፈስ ቅዱስ ለዓለም የሚገልጠው ሁለተኛ ነገር፥ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። እንደ ዮሐንስ 16፡10 አባባል፥ ይህ መገለጥ አስፈላጊ የሆነው፥ እርሱ በምድር ላይ ከእንግዲህ ስለማይኖር ነው፤ "ስለ ጽድቅም ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው።" ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ሕልውናውና የማስተማር ሥራው የእግዚአብሔር ጽድቅ መግለጫ ነበር። ወደ ሰማይ በሚያርግበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ስፍራውን ተክቶ ማገልገሉ አስፈላጊ ሆነ። ለማያምኑ ሰዎች እንደሚሰጠው አገልግሎት ከሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጽድቅ በሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች ይገልጣል። የመጀመሪያው ነገር፥ ጉዳያችን ጻድቅ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር መሆኑ ነው። ይህ ግንኙነትም ምድራዊ የመምሰል ወይም የማነጻጸር ጥያቄ አይደለም። የእኛ ሕይወት የሚታየውና የሚለካው በእግዚአብሔር አካላዊ ሕልውናና ጻድቅነት ነው። ለማያምን ሰው መንፈስ ቅዱስ የሚገልጠው ሁለተኛ ነገር፥ እግዚአብሔር ለአማኝ የሚሰጠውና በክርስቶስ በኩል የሚገኝ ጽድቅ መኖሩን ነው። እርግጥ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ የሚያኖረውን ይህን ጽድቅ በሚገባ ሳይረዱ በእምነት ወደ ክርስቶስ የሚቀርቡና የሚድኑ እንዳሉ ጥርጥር የለንም። እንዲሁም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሰጣቸውን ጽድቅ እንደሚሰጣቸው በድንግዝግዝ ብቻ የሚረዱና አስደናቂው የማጽደቅ ሥራ ያልገባቸው ብዙዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን ያልዳነ ሰው ቢያምን እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ልክ እንደ ጻድቅ ሰው ከእርሱ ጋር ጉዳዩን ሊፈጽም እንደሚችል በትክክል ማመን ይገባዋል። ይህ መገለጥ ከወንጌል የሚለይ አይደለም።

ላልዳኑ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሰጣቸው ሦስተኛ መገለጥ ደግሞ መስቀሉ ከፍርድና ከሰይጣን ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ክርስቶስ ሲናገር፥ መንፈስ ቅዱስ ዓለምን የሚወቅሰው፥ "ስለ ፍርድ የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው" (ዮሐ. 16፡11) አለ። ፍርድ እውነተኛና

የማይቀር መሆኑን መንፈስ ቅዱስ ላልዳነው ሰው ልብ ይገልጥለታል። ያልዳኑ ሰዎች ኃጢአት ፍርዱን በመስቀል ላይ እንደተቀበለና በክርስቶስ ለሚታመኑ ሁሉ ከኃጢአት ፍርድና ከኩነኔ ነጻነት እንደተሰጣቸው ሊያውቁ ይገባል። ስለ እነርሱ ክርስቶስ እንደተፈረደበትና እንደሞተ፥ ስለዚህም የኃጢአት ፍርድ እንዳስፈላቸው ማየት አለባቸው። ለዚህም ምልክት እንዲሆን "የዚህ ዓለም ገዥ" የሆነው ሰይጣን እንደተፈረደበት ተጠቅሷል። ሰይጣን በመስቀል ላይ ተሸንፏል። መስቀሉ በሰይጣን ላይ የተገለጠ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ሰይጣን በፍርድ ከተወገዘና ከተፈረደበት ቆይቷል። አሁን የተፈረደበትን ፍርድ ለመፈጸም ብቻ በመጠባበቅ ላይ ነው። እግዚአብሔር ሰይጣን በዚህ ዘመን ታላቅ ኃይል እንዲሆን ቢፈቅድለትና ነጻነት ቢሰጠውም፥ መጨረሻው ግን የታወቀ ነው። ክርስቶስን ለመቀበል ፈቃደኞች የማይሆኑ ሁሉ የእርሱ የመጨረሻ ዕጣ ተካፋዮች ይሆናሉ።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ላልዳኑት ሰዎች ያለው አገልግሎት ግልጥ የሆኑ ሦስት መሥመሮችን የተከተለ ነው። በመጀመሪያ ያልዳነ ሰው ደኅንነት በክርስቶስ በማመን ላይ የተመሠረተ መሆኑን መረዳት አለበት። ሁለተኛው ነገር ጽድቅ የእግዚአብሔር አካላዊ ሕልውና ክፍል እንደሆነና ይህም ለኃጢአተኞች በክርስቶስ በኩል የተዘጋጀላቸው መሆኑን መገንዘብ ነው። ሦስተኛው ነገር ደግሞ ባልዳነ ሰው ላይ ፍርድ መምጣቱ የማይቀር እውነት እንደሆነና ኃጢአተኞች ይድኑ ዘንድ፥ በምትካቸው በተፈረደበትና በተገደለው ክርስቶስ ውስጥ መገኘት ያለባቸው መሆኑ ነው። እነዚህ ነገሮች ሁልጊዜ በግልጥ የሚታዩ ባይሆኑም፥ ኃጢአተኛ ይድን ዘንድ በክርስቶስ ላይ መመሥረት ያለበት መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ላልዳነ ሰው ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ፥ ውጤት ሊያመጣ የሚችል የወንጌል ስብከት እንዲኖር ማድረግ መሆኑ መናገር እንኳ የሚያስፈልገው አይደለም።

## 6. ኃጢአትን የመከልከል ተግባር

*የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር በብሉይ ኪዳን።* የመንፈስ ቅዱስ ዓለምን ከኃጢአት የመጠበቅ ሥራ በታላቁ መከራ ጊዜ፥ ማለት ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ ኃጢአተኛነት ከሚበዛበት፥ ያልተከለከለ ኃጢአት ምን እንደሚመስል ለማሳየት እግዚአብሔር ከሚጠቀምበት ከዚያ ጊዜ በቀር በየትኛውም ዘመን ይገኛል። ነገር ግን ኃጢአትን የመከልከል ሁኔታው በየዘመናቱ የተለያየ ነበር።

በዘፍጥረት 6፡3፥ "እግዚአብሔር መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም እርሱ ሥጋ ነውና. . ." አለ በሚለው ቃል ውስጥ የብሉይ ኪዳን

ኃጢአትን የመከልከል ተግባር መመሪያ ይገኛል። ይህ ክፍል በኖኅ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን በመከልከል ረገድ የነበረውን ሰፊ ተግባር ያሳየናል። ከኃጢአት የሚጠብቀው የእግዚአብሔር እጅ በግሩም ሁኔታ የተገለጠው ኢዮብ በእግዚአብሔር እንደተጠበቀ በሚናገረው በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ነው። በኢዮብ ላይ የደረሰው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር የተፈቀደ ቢሆንም፥ ሰይጣን እግዚአብሔር ከፈቀደለት ውጭ በኢዮብ ላይ ምንም ለማድረግ አይችልም ነበር። በግልጥ ባይነገርም፥ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር እንደነበር መሠረታዊው ትምህርት ያረጋግጥልናል።

ኃጢአትን የመከልከል አብዛኛው የመንፈስ ቅዱስ ተግባር በተለያየ መንገድ እንደሚፈጸም ተገልጧል። መንፈስ ቅዱስ በነቢያት አማካይነት የገለጠው እውነት፥ በተለይ ሊመጣ ስላለው ፍርድ የገለጠው ነገርና የቅዱሳት መጻሕፍት ኃይል ኃጢአትን ለመከልከል የረዱ ነገሮች ናቸው። በዓመፃቸውና መንፈስ ቅዱስን በማስመረራቸው ምክንያት በሕዝቡ ላይ የመጣባቸው ፍርድ (ኢሳ. 63፡10-11) የራሱ የሆነ ውጤት ነበረው። የመንፈስ ቅዱስ ሕልውናና ኃይል ኃጢአትን ለመከልከል እጅግ ረድቷል። በብሉይ ኪዳን ዘመናት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሰውን ልጅ የታሪክ አቅጣጫ ለመለኮታዊ ቸርነትና ጥበቃ በማዘጋጀት ላይ ነበር።

*የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር በዚህ ዘመን።* የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር በብሉይ ኪዳን እንደነበር ሁሉ በዚህ ዘመንም ቀጥሏል። ለዚህ አገልግሎቱ ተጨማሪ የሆነ ማረጋገጫ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡7 እናገኛለን፡- "የዓመፅ ምስጢር አሁን ይሠራልና ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ።" የዚህ ክፍል የመነጋገሪያ አሳብ የዓመፅ ሰው፥ እርሱም የጥፋት ልጅ የሆነው የሚገለጥበትን የጌታ ቀን መምጣት የሚመለከት ጉዳይ ነው (2ኛ ተሰ. 2፡3)። በዚህ ክፍል መሠረት የሚከለክለው እስከሚወገድ ድረስ የጥፋት ልጅ ሊገለጥ አይችልም። ስለዚህ ይህ ዘመን የጥፋት ልጅ እንዳይገለጥ ባደረገውና ዓመፅ ከልካይ በሆነው መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ይጠቀማል። ይህ ዓመፅን የሚከለክል አካል በብሉይ ኪዳን መሠረት ስንመለከተው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እንረዳለን።

የቅዱሳት መጻሕፍት ተርጓሚዎች ዓመፅ የሚከለክለውን አካል ማንነት በሚመለከት አልተስማሙም። በሰፊው የታወቀውና አንደኛው አመለካከት፥ ይህ ዓመፅን የሚከለክለው አካል በምድር ላይ ያለ ሰብዓዊ መንግሥት ነው የሚል ነው። ሰብዓዊ መንግሥት ግን የዓመፅ ልጅ በሚገለጥበት በታላቁ የመከራ ጊዜም ይኖራል። ሕግና ሥርዓቶች ሁሉ የሚያዘነብሉት ኃጢአትን ወደ መከልከል ቢሆንም፥ ሁኔታቸው በዚህ ክፍል እንደተገለጠው አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል ይህን

ዓላማ ከፍጻሜ እንዲያደርሱ እንደተደረጉና ጥቅም ላይ እንደዋሉ የሚታዩ ናቸው። ስለዚህ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር መንገዱ ምንም ይሁን ምን፥ ከእግዚአብሔር የሚመጣ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አድርጎ መቁጠር የተሻለ ነው። ነገር ግን ቲሰን [Thiessen] የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ እንደጻፈው "ኃጢአትን የሚከለክል ማነው? ዴኒ [Denney]፥ ፊንድሊ [Findley]፥ አልፎርድ [Alford]፥ ማፌት [Moffat]፥ የተባሉ ሰዎች ይህ በተለይ በሮም ግዛት ውስጥ የነበረውን ሕግና ሥርዓት የሚያመለክት ነው ብለዋል። ነገር ግን ኃጢአትን በሚከለከለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውስጥ ሰብአዊ መንግሥታት በአስፈጻሚነት ቢያገለግሉም፥ በእነርሱ አሠራር ላይ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በጎ ተጽዕኖ እንደምታደርግ እናምናለን። ደግሞም ከእያንዳንዱ ሰብአዊ መንግሥት ጀርባ ያን መንግሥት የመሠረተውና ያቋቋመው እግዚአብሔር አለ (ዘፍጥ. 9፡5-6፤ ሮሜ 13፡1-7)። እርሱም ይቆጣጠረዋል (መዝ. 75፡5-7)። ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የዓመፅን መስፋፋት የሚገታ እግዚአብሔር ራሱ ነው" ብሏል።

አንዳንዶች የሚያቀርቡት አመለካከት ደግሞ፥ የኃጢአትን እውነተኛ ባሕርይ ሰዎች እንዳይረዱ በማድረግ ሰይጣን ራሱ ዓመፅን (ኃጢአትን) ይከለክላል የሚል ነው። ሰይጣን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በተገለጠበት ሁኔታ ስናየው፥ ይህን አሳብ ማጣጣሙ አስቸጋሪ ይሆናል። ሰይጣን በዓለም ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ታላቅና ለግምት የሚያስቸግር ቢሆንም፥ በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዓለም አቀፍ ሥልጣን እንደተሰጠው አልተነገረም። በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡3-10 እንደተገለጠው የዓመፅ ልጅ ከመምጣቱ በፊት ኃጢአትን የሚከለክለው ይወገዳል። ይህ ሰይጣን ነው ማለት ፈጽሞ አስቸጋሪ ነው። በተቃራኒው የታላቁ መከራ ጊዜ የሰይጣን ሥራ በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጥበት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ ክፉ ቀን ሰይጣን ወደ ምድር እንደሚጣልና የጥፋት ኃይሉን እንደሚጠቀም ይናገራል (ራእይ 12፡9)። ስለዚህ ሰይጣን ዓመፅን የሚከለክል ነው ብሎ ማሰብ በምክንያታዊነት የሚያዝ አቋም አይደለም።

በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን ለመከላከልና ሰዎችን ለመርዳት የታገለ መሆኑን ካመን፥ በዚህም ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሠራ፥ ተመሳሳይ አገልግሎት እንደሚኖረው አንጠራጠርም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በምድር እያለች በዓለም ላይ የመጨረሻ ፍርዱን የሚያመጣ ባይሆንም፥ በስሙ የተጠሩ ሕዝቦቹን የማውጣት ዓላማውን ለመፈጸም ግን፥ ሉዓላዊነቱ በሰዎች ድካምና ክፋት ላይም ሆነ በሰይጣን ኃይል ላይ ይሠለጥናል። በቤተ ክርስቲያን ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ ያገኘው ግንዛቤ መጠነኛ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጥበቃ ውጭ ኃጢአት በሞላበት ዓለም ውስጥ መኖሩ ለክርስቲያኖች አስቸጋሪ ይሆን ነበር።

*ኃጢአትን በመከልከል ተግባር የሚጠቀሙ ነገሮች።* ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ የሚናገሩት ሰፊ ነገር የለም። ነገር ግን የኃጢአትን አቅጣጫ የሚቆጣጠሩ ሌሎች በርካታ ነገሮች መኖራቸው ለዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ክርስቲያን በምድር ላይ ሲኖር ዓለም በኃጢአት እንዳትቀጥል ለሚያደርጉ ኃይሎች የሚሰጠው አስተዋጽኦ በርካታ ነው። የክርስቲያኖች አንድነት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፥ የመጽሐፍ ቅዱስን መመዘኛ ባታሟላ እንኳን፥ በዓለም ላይ ከፍተኛ በጎ ተጽዕኖ ታሳድራለች። መጽሐፍ ቅዱስ በደረሰበት ቦታ ሁሉ ባመኑት ላይ ብቻ ሳይሆን፥ ባልዳነው ዓለም ላይም በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ያሳድራል። በእግዚአብሔር ተሹመው የተቀመጡ ሰብአዊ መንግሥታትም ለመለኮታዊ ዓላማ ፍጻሜ አንድ መንገድ ናቸው። እነዚህ ክንውኖች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ባይሆኑም፥ ይህን ዓላማውን ለመፈጸም እርሱ የሚጠቀምባቸው ሁኔታዎች ናቸው። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ፥ አስፈላጊ ከሆኑ የእግዚአብሔር ሥራዎች አንዱና ለመለኮታዊ ቸርነትና ጥበቃ ለሁሉ የተሰጠ የጸጋ ክንውን አካል መሆኑን ለማየት እንችላለን።

## 7. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ውሱንነት

ቀደም ሲል ካደረግነው ውይይት በመነሣት፥ ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ከሥርየት አስገኝ ጸጋ በጣም ያነሰ መሆኑን መረዳቱ አያስቸግርም። ያልዳነ ሰው ወንጌልን በሚገባ እንዲረዳና በተረዳው ነገር የአስተዋይነት እርምጃ እንዲወስድ ለመምራት ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ የሚሠራው ሥራ ቀላል ባይሆንም፥ በሰው ፈቃድ ላይ ምንም ለማድረግ ስለማይችል ደኅንነትን ለመስጠት የሚበቃ አይደለም። ሁለት ያልዳኑ ሰዎች እኩል ወንጌልን ተረድተው አንዱ ወደሚያድን እምነት ጨርሶ ላይደርስ፥ ሌላው ደግሞ በክርስቶስ አምኖ ሊድን ይችላል። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ያልዳኑትን ወደ ደኅንነት ሊያመጣ ከሚችል ከየትኛውም ዓይነት ሥርየት አስገኝ የእግዚአብሔር ሥራ የተለየ መሆን አለበት።

ለሁሉም የተሰጠ ጸጋ፥ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከሚረዳበት ልምምድ ያነሰ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን በሰጡ ክርስቲያኖች ውስጥ ማደር፥ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት እንዲረዱ ብርሃን ይሆንላቸዋል። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ በአጠቃላይ ደኅንነት ርእስ ላይ በቂ ገለጣን በመስጠት በእምነት መሠረት ላይ ያሳርፋል። ይህ ጸጋ በደኅንነት እውነት ክልል ውስጥ እንኳ ከተፈጥሮአዊ ሰው መረዳት በላይ አይደለም። ከግብረገባዊና አሳማኝ ከሆነ እውቀት ጋር የቀረበ ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን፥ በራሱ ወደ ውሳኔ የሚያመጣ ምንም ነገር ግን የለውም።

ለሁሉም የተሰጠ ጸጋ፥ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ባደረ ክርስቲያኖች የሚታየውን ልምምድ ያለምንም ገደብ የሚሰጥ አይደለም።

ለሁሉም የተሰጠ ጸጋን ብቻ በተለማመዱ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑት ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ሊገኙ አይችሉም። ያልዳኑ ሰዎች አንዳንዶቹን ክርስቲያናዊ አኗኗሮች ውጫዊ ሕይወት መኖር ቢችሉም፥ የውስጣዊ ለውጥ ልምምድ ጨርሶ የላቸውም። እርግጥ በአንዳንድ ሁኔታዎች የዳነውንና ያልዳነውን ሰው ለመለየት ማስቸገሩ የሚካድ አይደለም።

ምንም እንኳን ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ በባሕርዩና በውጤቱ ውሱን ቢሆን፥ ያለምንም ሁኔታ የተገለጠ ነው ለማለት አይቻልም። ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በግልጥ የተያያዘ ባይሆንም፥ ሃይማኖታዊ ስሜትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ ጋር የተያያዙ ለመሆናቸው አያጠራጥርም። ይህ ለሁሉ የተሰጠ የጸጋ ደረጃ ግን የወንጌልን ጉዳይ ለመረዳት የሚያበቃ አይደለም። በስፋት ስንመለከተው ኃጢአትን የመከልከል ኃይል ሳይኖረው እንደማይቀር እናስባለን። ሰዎች ደኅንነት ሳያገኙ በውጫዊ መንገድ ክርስቶስን እንዳመኑ የመናገራቸውና፥ ጥሩ ግብረገባዊ ሕይወት የመኖራቸው ምክንያት ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ውጤት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ቻርልስ ሆጅ እንዲህ ብሎ ጽፏል፦ "ያልተለወጡ ሰዎች ንስሐ እንደገቡ፥ እንዳመኑ፥ የመንፈስ ቅዱስ ተካፋይ እንደሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ቃል መልካምነትና ሊመጣ ያለውን ኃይል እንደቀመሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ተነግሯል።" ስለዚህ ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ሥራ ውስጥ ሁለንተናዊ ከሆነው ሃይማኖታዊ ስሜትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ጀምሮ ደኅንነትን እስከመግለጥ ድረስ የተለያዩ ደረጃዎች መኖራቸው የሚያጠራጥር አይደለም። በዚህ ሁሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ክርስቶስን ለደኅንነታቸው ወደ ማወቅ ደረጃ ይመጡ ዘንድ በሥራው ይተጋል። ያለዚህ ቀዳሚ አገልግሎት የሥርየት ጸጋ የሚቻል አይደለም።

መንፈስ ቅዱስ ላልዳነው ዓለም ያለው የጸጋ ሥራ የማያልቅና፥ እግዚአብሔር በጽድቅ የተሞላ ፍርዱ ዓላማ የሆኑት ሁሉ የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት ወደ ማወቅ እንዲደርሱ የሚታገል መሆኑን የሚያሳይ ሌላ ማረጋገጫ ነው። ያለዚህ አገልግሎት ይህች ዓለም ለክርስቲያኖች የማይቻሉ ሁኔታዎችን የምትፈጥርና የወንጌል ስብከትም ውጤት የማይታይባት ትሆን ነበር። አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም በሆነ ክብር የሚቆመው የጸጋ ምርኮ፥ በክርስቶስ የተሰጠውን ተግባር ለመወጣት መንፈስ ቅዱስ ላለው ውጤታማ ኃይል በቂ ምስክር የሚሆን ነው።

# 13

# ውጤት አስገኝ ጸጋ

## 1. የትምህርቱ አስፈላጊነት

ሰዎች ውጤት ባለው የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት እምነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሥነ-መለኮት ትምህርት ቋንቋ "ውጤት አስገኝ ጸጋ"* ይባላል። ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ ቀጥሎ በጊዜም ሆነ በታማኝነት ቅደም ተከተል ሰዎችን ወደ ደኅንነት ለማምጣት የሚያስፈልገው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሥርየት አስገኝ ጸጋ ነው። ይህ ጉዳይ በአንዳንድ የሥነ-መለኮት ትምሕርቶች በአግባቡ ግንዛቤ ያላገኘና የተሳሳተ ትርጉም የተሰጠው ነው። ይሁን እንጂ ትምሕርቱ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥሩ ውጤት የሚሰጥ አቅጣጫን በተመለከተ ሁሉ ያመለክታል። እግዚአብሔር ሰዎችን በማዳን ረገድ ያለውን እጅግ አስፈላጊ ተግባር ያመለክታል። ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትም አስፈላጊ የሆነ ክፍል ነው።

ከተግባራዊነት አኳያም የአማኙን ደኅንነት በተመለከተ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር በጥንቃቄ ሊጠና የሚገባውና እጅግ አስፈላጊም ነው። ይህ ትምህርት በክርስቶስ ለሚያምን ሁሉ እግዚአብሔር በሕይወቱ ስለሚሠራው ሥራ የሚናገር የከበረ መገለጥ፥ ለመንፈሳዊ ልምምዱ እና ክቡር ለሆነ ተስፋው መሠረት ነው። መንፈስ ቅዱስ በደኅንነት ውስጥ ስላለው ሥራ ግልጥ የሆነ አሳብ ከተያዘ፥ ስለ ደኅንነት ዋስትና የሚነሡ በርከት ያሉ ውዥንብሮችን ለማስወገድ ይቻላል። ይህ ትምህርት "ደኅንነት የሚገኘው በሥራ ነው" የሚለውን ፍልስፍና ውድቅ ያደርገዋል። የደኅንነታችንን ዋስትና ከስሜታዊ ልምምድ ነጻ ያደርጋል። በተጨማሪም ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ትክክለኛ ስፍራ በመስጠት፥ "የቅድስና [Holiness] እንቅስቃሴ"** ከተባለው ቡድን የተሳሳተ ገለጣ ነጻ ያወጣል።

---

* በዚህ መጽሐፍ "ውጤት አስገኝ ጸጋ" እና "ሥርየት አስገኝ ጸጋ" የሚሉትን ሐረጎች በማፈራረቅ ተጠቅመንባቸዋል።

** በ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ መጀመሪያ ላይ በርከት ያሉ አነስተኛ የሃይማኖት ክፍሎች፥ ፍጹምነትን በዚህ በምድራዊ ሕይወት ልንደርስበት የምንችለው ነገር ነው በማለት ያስተምሩ ነበር። አብዛኛዎቹ የዚህ ትምህርት ተከታዮች በጆን ዌስሊ [John Wesley] ከተመሠረተው የመቶዲስት [Methodist] ቤተ ክርስቲያን የወጡ ናቸው። አንዳንድ ፍጹምነትን በሕይወት ዘመናችን እንለማመዳለን የሚሉ አብያተ ክርስቲያናት፥ ከጴንጠቆስጣዊ አብያተ ክርስቲያን ጋር በሚስማማ አሳባቸው፥ በልሳን መናገርንና የፈውስ ስጦታዎች በዚህ ዘመን እንደሚሠሩ ያምናሉ።

ደግሞም በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ራሱ እንዴት አድርጎ በመሥራት ላይ እንዳለ ለመረዳት ጥሩ መሠረትን ይሰጣል።

አንድ ሰባኪ ትክክለኛ ወንጌል ይሰብክ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በደኅንነት ውስጥ ያለውን ሥራ አጥርቶ መረዳቱ እጅግ አስፈላጊና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። የእግዚአብሔር አስፈላጊ ሥራ፥ ሰው ማድረግ ያለበት ነገርና ነፍሳትን ለክርስቶስ ለመማረክ የሚያስፈልገው የእግዚአብሔር ኃይል ተገቢ ግንኙነታቸው ይታያል። ይህ ሰባኪው በራሱ መርሐ ስብከትና ችሎታ ላይ ከመደገፍ ነጻ የሚያደርገው ሲሆን፥ ወንጌልን በሥልጣን እና በኃይል ለመስበክ ማድረግ ካለበት ጥረት ሳይዘናጋ፥ ለፍሬያማ አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ላይ እንዲደገፍ የጸሎትን ኃይል ወደ መለማመድ ይመራዋል። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚኖረው ኅብረትም በአገልግሎቱ ከፍተኛ ለውጥ ያስገኝለታል።

ይህን ትምህርት በተለያየ መንገድ ለማብራራት የሚጥር ማንኛውም ጸሐፊ፥ አቀራረቡ ትሕትናን የተሞላ መሆን አለበት። መሠረታዊው የእምነት ትምህርት ከሕይወት ጋር የሚዛመድበት ነገር እጅግ ሰፊ ነው። በዚህ ትምህርት ውስጥ የሰው ጥበብ ጣልቃ ገብነት ቢታይም መለኮታዊው ጥበብ እጅግ አስፈላጊና ዋነኛ ነው። ከሰው ጥበብ ይልቅ መለኮታዊው ጥበብ ለውጤታማ ትምህርት ዋነኛ ስለሆነ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን ብቻ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

## 2. ውጤት አስገኝ ጸጋ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት

የውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚለው ርእስ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቋንቋ ቢሆንም፥ ቀድሞም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ያለው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ደኅንነት የሚያመጣ መለኮታዊ ጥሪ እንዳለ በተደጋጋሚ ይናገራሉ (ሮሜ 1፡1፥ 6፥ 7፤ 8፡28፥ 30፤ 9፡11፥ 24፤ 11፡29፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡1፥ 2፥ 9፥ 24፥ 26፤ 7፡15፥ 17፥ 18፥ 20-22፥ 24፤ ገላ. 1፡6፥ 15፤ 5፡8፥ 13፤ ኤፌ. 1፡18፤ 4፡1፥ 4፤ ቈላ. 3፡15፤ 1ኛ ተሰ. 2፡12፤ 4፡7፤ 5፡24፤ 2ኛ ተሰ. 2፡14፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡12፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡9፤ ዕብ. 3፡1፤ 9፡15፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡15፤ 2፡9፥ 21፤ 3፡9፤ 5፡10፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡3፥ 10)። ደኅንነትን የሚያስገኝ ይህ መለኮታዊ ጥሪ፥ ወንጌልን በመግለጥ እና ወደሚያድን እምነት በመምራት ውጤት ማምጣቱ እርግጠኛ ስለሆነ "ውጤት አስገኝ ጸጋ" በመባል ይታወቃል። ከዚህኛው የእግዚአብሔር ሥራ በተነጻጻሪነት ወንጌልን ለሚሰሙ ሁሉ የሚደረግ

አጠቃላይ የደኅንነት ጥሪ አለ። በዚህ ስሜት ነው ክርስቶስ "ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና" ያለው (ማቴ. 9፡13)።

ለንስሐና ለእምነት የሚደረግ ጥሪ ሁልጊዜ ተቀባይነት የማያገኝ መሆኑ ግልጥ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ራሱ፥ "የተጠሩ ብዙዎች ናቸው የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና" ብሏል (ማቴ. 22፡14)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ጥሪ የሚናገሩ በርካታ ጥቅሶችን በምንመረምርበት ጊዜ የሚናገሩት፥ ሥርየት ስለሚያስገኘው ጥሪ መሆኑን እንረዳለን። ስለዚህ ውጤት አስገኝ ጥሪ ከአጠቃላይ ጥሪ ጋር በተነጻጻሪነት እንደቀረበ ሁሉ፥ ውጤት አስገኝ ጸጋም ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ ጋር በተነጻጻሪነት ይቀርባል። ተግባራዊ ዓላማን በሚመለከት፥ ጸጋው በጥሪው ውስጥ እንደሚካተት በማሰብ መለኮታዊ ጥሪና በውስጡ ያለው ጸጋ እንደ አንድ ጉዳይ እንደሚታዩ ለማሰብ እንችላለን።

ስለ ውጤት አስገኝ ጥሪ የሚናገሩ በርካታ ክፍሎችን በማጥናት የዚህን እውነት ብዙ ገጽታዎች ለመግለጥ እንችላለን። የመጀመሪያው ነገር ይህ መሠረታዊ ትምህርት ያለጥርጥር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ ነው። ደኅንነትና መለኮታዊ ጥሪ አንዱ ያለ ሌላው ሊሆኑ የማይችሉና የማይነጣጠሉም ናቸው። ክርስቲያኖች "ቅዱሳን ልትሆኑ የተጠራችሁ" (ሮሜ 1፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡2)፥ "ለዘላለም ሕይወት" የተጠራችሁ (1ኛ ጢሞ. 6፡12)፥ "ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን" ተጠርታችሁ (1ኛ ጴጥ. 2፡9)፥ "በገዛ ክብሩና በበጎነቱ" የተጠራችሁ (2ኛ ጴጥ. 1፡3) ተብለዋል። ጳውሎስ "ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ" (ሮሜ 1፡1፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡1)። "አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም፥ እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው" (ሮሜ 8፡30)። ስለ ክርስቲያኖች፥ "የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ" (ሮሜ 1፡6)፥ እና "እንደ አሳቡም ለተጠሩ" (ሮሜ 8፡28) ተብሎላቸዋል። በጣም አስፈላጊ የሆነ ጥቅስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡23-24 ይገኛል፡- "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ፥ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፤ ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎች ቢሆኑ የእግዚአብሔር ኃይል እና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።" ላልተጠሩ ሰዎች ወንጌል ሞኝነት ሆኖ ሲቀር፥ ለተጠሩት ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ከእነዚህ ክፍሎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለደኅንነት የመጥራቱ አገልግሎት በጣም አስፈላጊና በበርካታ ስፍራዎች የተጠቀሰ መሆኑን በመናገር ለማጠቃለል እንችላለን።

## 3. ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ ነው

ውጤት አስገኝ ጸጋ በቀላሉ ልንረዳው የማይቻለን አሠራር ቢሆንም፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጠው አፈጻጸሙ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። አብዛኛዎቹ የካልቪን የሥነ-መለኮት ትምህርት መምህራን፥ ስለዚህ አሳብ ያላቸው አስተያየት አንድ ሲሆን፥ ቅዱሳት መጻሕፍትም በርካታ ምስክርነት ይሰጣሉ። ቻርልስ ሆጅ በጉዳዩ ላይ የሚከተለውን ጽፏል፦

> "ማንኛውም ድርጊት ከሚከተሉት በሦስት ወይም በአንዱ መንገድ ምክንያት ሊከናወን ይችላል፦ 1ኛ. የእግዚአብሔር ኃይል በቀጥታ ሲገባበት (ተአምራት)፥ 2ኛ. በእግዚአብሔር ተቆጣጣሪነትና ምሪት የተፈጥሮ ኃይላት ነገሮች እንዲከሠቱ በማድረግ (ምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ)፥ 3ኛ. እግዚአብሔር በቀጥታ በሰው ልብና ፈቃድ ውስጥ በመሥራት ሰው እርሱ የሚጠብቅበትን እንዲፈጽም በማድረግ ማድረግ።" ውጤት አስገኝ ጸጋ በሦስተኛው አሳብ ውስጥ የሚጠቃለል ነው።

ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት የታመነ ምስክርነት ይሰጣሉ። ስለ ውጤት አስገኝ ጥሪ የሚናገሩ ክፍሎች በሙሉ ሥራው የእግዚአብሔር መሆኑን አስቀድመው መገንዘባቸውን ያመለክታሉ። ውጤት አስገኝ ጸጋ ከሰው ነጻ ፈቃድ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ጋር የተዛመደ ነው። ለዚህ ነው ጳውሎስ፥ "ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ" ወዘተ. (ሮሜ 1፡1) የተባለው። በቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ ጥሪ ለሰው ነጻ ፈቃድ ስፍራ እንደሚሰጥ የሚናገር አንዳችም ነገር የለም። መለኮታዊ ጥሪ ሁሉን ቻይና ሉዓላዊ ከሆነው እግዚአብሔር የሚመጣ ነው።

በሰው ልጅ አጠቃላይ ውድቀትና ብቁ ያለመሆን ላይ ባላቸው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መሠረት፥ የካልቪን የትምህርተ-መለኮት መምህራን ውጤት አስገኝ ጸጋ ያለምንም እርዳታ እግዚአብሔር ራሱ የሚፈጽመው ተግባር መሆኑን ያረጋግጣሉ። ሰው ወንጌልን በሚሰማበት እና በሚረዳበት ደግሞም ደኅንነት እንደሚያስፈልገው በሚገነዘብበት ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ቅድመ አስፈላጊነት ሙሉ ለሙሉ ቢስማሙም፥ ውጤት አስገኝ ጸጋ ግን የሰውን ልብ በክርስቶስ ባለ እምነት ላይ እንዲያርፍ ለሰው ፈቃድ ኃይል መስጠት የእግዚአብሔር ሥራ ነው በማለት ይገልጡታል። በሁሉም ረገድ የውጤት አስገኝ ጸጋ ግብ ደኅንነት ነው፤ ምክንያቱም ደኅንነት የሚፈጸመው በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ነውና።

"የዌስትሚንስተር የእምነት መግለጫ" [Westminster Confession] እንደሚከተለው ያስፍረዋል፦

"ሀ. እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሕይወት የወሰናቸውንና ደስ የተሰኘባቸውን ብቻ ራሱ በወሰነና ባቀደ ጊዜ ከፍጥረታቸው ኃጢአተኞችና ሟቾች ከሆኑበት ደረጃ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ወዳለ ጸጋ እና ደኅንነት በቃሉ እና በመንፈሱ ጥሪ ያደርግላቸዋል። የእግዚአብሔርን ነገር ይረዱ ዘንድ መንፈሳዊ አእምሮአቸውን ለደኅንነት ያበራላቸዋል፤ ድንጋይ ልባቸውን ወስዶ የሥጋ ልብ ይሰጣቸዋል። አእምሮአቸውን በታላቅ ኃይል በማደስ ለበጎ ነገር ይወስናቸዋል፤ ልክ በነጻነትና በምርጫቸው እንደሚመጡ ዓይነት በሚገባ ወደ ክርስቶስ በመሳብ በጸጋ ብቁ ያደርጋቸዋል።

"ለ. ይህ ውጤት አስገኝ ጥሪ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ነጻ እና ልዩ ጸጋ ነው። ይህ የሚሆነው በሰው ውስጥ ቀድሞ በሚታይ አንዳች ነገር ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ፥ አነቃቅቶትና አድሶ ለጥሪው መልስ መስጠት እንዲችልና የተሰጠውን ጸጋ አምኖ እንዲፈጽም እስኪደረግ ድረስ ሰው ምንም ማድረግ አይችልም ነበር።"

ውጤት አስገኝ ጸጋ በአሠራሩ ምክንያት አንድ ጊዜ የሚከናወነውን የቅጽበት ተግባር እንጂ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ሂደት አይደለም። ከዚህ ቀደም ብለው ያሉ ዝግጅቶች በሙሉ በራሱ ደኅንነትን መስጠት የማይችል ለሁሉ የሚሆን ጸጋ አካል ናቸው። ብዙ ክርስቲያኖች ወደ ደኅንነት ለመራቸውና እግዚአብሔር ለሁሉ በሚሆን ጸጋ ላከናወነው ሥራ ምስክርነት መስጠት ይችላሉ። የውጤት አስገኝ ጸጋ ሥራ ግን የተለየና ወሳኝ ነው። አንዲት ነፍስ ከመንፈሳዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት በቅጽበት ትሸጋገራለች። የእግዚአብሔር ተግባር እንደመሆኑ መጠን ሥራው በቀላሉ ለአእምሮ የሚገባ አይደለም። እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር ከአበጀው በኋላ፥ ሕያው ነፍስ ያደረገው እንዴት እንደሆነ የሰው አእምሮ ለመመርመር እንደማይችል ሁሉ፥ የውጤት አስገኝ ጸጋ አሠራርንም መመርመር አይችልም።

## 4. የውጤት አስገኝ ጸጋ እርግጠኛነት

ርእሱ እንደሚያመለክተው ውጤት አስገኝ ጸጋ አንድን ነፍስ ወደ ደኅንነት በማምጣት ሥራው ሁልጊዜ ውጤታማ ነው። ይህ ጸጋ ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ ጋር ሲነጻጸር ለየት ይላል። ከዚህ የምናገኘው ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ በቀጥታ ሊገታ የሚችል መሆኑንና "አርምኒያን" እንደሚሉት ደኅንነትን ለማምጣት በቂ ቢሆንም እንኳ፥ ውጤታማ አለመሆኑን ነው።

ውጤት አስገኝ ጸጋ ግን ውጤታማ የሆነው ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ በመጠንና በኃይል በልጠ ሳይሆን፥ ሁሉን ቻይ ከሆነው እግዚአብሔር የሚወጣና የሚፈለገውን ውጤት ማምጣቱም እርግጠኛ ስለሆነ ነው። ከእግዚአብሔር ሥራዎች አንዳንዶቹን ላለመቀበል ይቻል ይሆናል። በክርስቲያን ሕይወት በሚገኝ ኃጢአት ምክንያት የሚያዝነው መንፈስ ቅዱስ፥ ክርስቲያን ከክፉ መንገዱ እንዲመለስ የሚያቀርበው ልመና ተቀባይነት አያገኝም ይሆናል። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ሥራ እውነትን ለመቀበል ፈቃደኝነትን የሚጠይቅ ባይሆንም ውጤት አስገኝ ጸጋ ግን ልንገታው የማንችለው ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ቻርልስ ሆጅ ሲጽፍ:- "በአውግስጢኖስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መሠረት፥ ውጤት የማስገኘት መለኮታዊ ጸጋ፥ በዳግም ልደት ውስጥ የሚመሠረተው፥ በመስማማት ወይም ጠንክሮ በመተባበር ወይም ተቀባዩ በጸጥታ በመቆየት ሳይሆን በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ነው። 'የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል' የተናገረውን መፈጸም ነው። የአውግስጢኖስ ትምህርት ይህ እንደሆነ ታምኖበታል" ብሏል።

ውጤት አስገኝ ጸጋ የማይገታ ነው ስንል፥ ሊቋቋመው የሞከረ ኃይል ነበር ለማለት ሳይሆን፤ ጨርሶ የሚገታ አለመሆኑንና የተሞከረም አልነበረም ለማለት ነው። ይህ የዚህ ልዩ ጸጋ ባሕርይው ነው። ውጤት አስገኝ ጸጋ አይገታም። በዚህ መሠረት ኤ. ኤች. ስትሮንግ [A. H. Strong] የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ እንዲያውም "የማይገታ" የሚለውን ቃል ባንጠቀም ይሻላል በማለት የተሻለ አባባልን አቅርቧል:- "ይህ ልዩ ጥሪ፥ ፍቱን እና አጥጋቢ ነው። ይኸውም ከቶ በማይሻር ሁኔታ ኃጢአተኛን ወደ ደኅንነት የመምራት ተግባሩን ይፈጽማል። ይህም ሁለት ነገሮችን ያመለክታል።

"ሀ. የእግዚአብሔር ተግባር በሰው ፈቃድ ላይ የሚጫን ሳይሆን፥ ከአእምሮአችን ሕግ ጋር መስማማት ነው። ስለዚህ መግታት የሚለው ቃል ማስገደድ ወይም ግዳጅ ከሚለው፥ እግዚአብሔር በሰው ነፍስ ውስጥ ለሚሠራው ሥራ ባዕድ ከሆነ አሳብ ነጻ መሆኑ ታውቆ ይህ ስሜት ውድቅ መሆን አለበት።

"ለ. በውጤት አስገኝ ጸጋ ውስጥ የእግዚአብሔር ሥራ፥ የኃጢአተኛን የጨለመ አእምሮና ፈቃድ እንዲሁም የጊታን የማዳን መንገድ እንዲመርጥ ማስቻል ነው" (ዮሐ. 1፡12-13)።

ውጤት አስገኝ ጸጋ በሙላት ግንዛቤ ሲያገኝ፥ በተጠቃሚዎቹ ደኅንነት ውስጥ እርግጠኛ ውጤት ይገኛል። በሁሉም ሁኔታዎች፥ ውጤት አስገኝ ጸጋን የሚቀበል በአንድ አፍታ ይድናል። በእያንዳንዱ ሰው ልምምድ ውስጥ ስናየው ደግሞ በክርስቶስ ማመን የየግለሰቡ ምርጫና

ተግባር ነው። ያም ሆኖ ከንውኑ የውጤት አስገኝ ጸጋ ሥራም ነው። ውጤት አስገኝ ጸጋ ዓመፀኛ በሆነ ልብ ውስጥ ሠርቶ አያውቅም። ደግሞም ማንም ከራሱ ፈቃድ ውጭ ድኖ አያውቅም። ይልቁን "ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና" (ፊልጵ. 2፡13) ከሚለው መመሪያ ጋር ሁልጊዜ የሚስማማ ነው።

## 5. የውጤት አስገኝ ጸጋ መከላከያ

*የእግዚአብሔር ሥራ የተፈለገውን ውጤት የሚያስገኝ መሆን አለበት።* ውጤት አስገኝ ጸጋ ለሰው ልጅ እንደተሰጠና የተፈለገውን ውጤት እንደሚያስገኝ ቢያንስ አራት የተለያዩ መረጃዎችን ለማቅረብ እንችላለን። ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ እንደመሆኑ መጠን ውጤታማ ለመሆኑ እርግጠኞች ነን። ቀደም ሲል እንዳየነው ይህ ተግባር ከሰው ፈቃድ ጥገኝነት ውጭ ሁሉን ቻይ ከሆነው እግዚአብሔር የሚወጣ ስለሆነ ውጤታማ መሆኑ እርግጥ ነው። ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ አፈጻጸም ውስጥ የተገለጠው ሁኔታ የእግዚአብሔርን የማሳመን ሥራ ሊገታ ቢችልም፥ ሁሉን አድራጊነቱንና ሉዓላዊ ሥራውን ግን ጨርሶ ሊገታ አይችልም። ቻርልስ ሆጅ፡- "ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል ነው ብለን ከወሰንን፥ ይህን ርእስ በሚመለከት የሚነሡ አወዛጋቢ ጥያቄዎችን ሁሉ ይመልሳል. . . መላ ምቱን በመቃወም በርካታ ጽሑፎች ተጽፈዋል። ጽሑፎች ሁሉ ዳግም መፍጠር ወይም የሥርየት ጥሪ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ከተቀበሉ መላ ምታቸው ዋጋ ያጣል" ብሏል።

*የውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ እምነት አስቀድሞ መወሰን ለሚለው ትምህርት በጣም አስፈላጊ ነው።* ለእግዚአብሔር እቅድ የተመረጡ ሁሉ ይድኑ ዘንድ የግድ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ለተመረጡት ሁሉ ለሌሎች ከተሰጠው የበለጠ ጸጋ ይሰጣቸው ዘንድ አስፈላጊ ነው። የተመረጡትን ወደ ደኅንነት ለማምጣት ጸጋ ውጤታማ መሆን አለበት። የእግዚአብሔር አስቀድሞ መወሰንና የሥርየት ጥሪ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በግልጥ የተያያዙ ናቸው። እግዚአብሔር ሰውን የሚጠራው እንደ አሳቡ ነው (ሮሜ 8፡28)። ይህ አሳብ ሰፋ ተደርጎ በሚከተለው ሁኔታ ተገልጧል። "አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው" (ሮሜ 8፡30)። እዚህ ላይ ተገልጦ የምናየው ጥሪ ውጤት አስገኝ ጥሪ እንደሆነ ግልጥ ነው። አስቀድሞ የተወሰኑ ሁሉ ተጠሩ፤ የተጠሩ ሁሉ ደግሞ ጸደቁና ከበሩ። እዚህ ላይ ለወንጌል የሚደረግ አጠቃላይ ጥሪና የተፈለገውን ውጤት የሚያመጣው ልዩ ጥሪ በግልጥ

ተለይተው ቀርበዋል። የውጤት አስገኝ ጥሪና የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ግንኙነት የቱንም ያህል ምሥጢራዊ ይሁን የውጤት አስገኝ ጥሪ ጭብጥ እርግጠኛነት አያጠራጥርም። የመዋጀት ዓላማ እንዲፈጸም የተመረጡት ሁሉ ወደ ክርስቶስ መምጣታቸው አስፈላጊ ነው (ዮሐ. 6፡37፥ 39፤ 17፡12)።

*ውድቀትና መንፈሳዊ ሞት ውጤት አስገኝ ጸጋን ይሻሉ።* የመንፈሳዊ ሕይወትን ከዳግም ልደት በፊት አለመኖር ስንመለከት፥ የውጤት አስገኝ ጸጋን አስፈላጊነት እንገነዘባለን። የውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የተመሠረተው በዚህ አሳብ ላይ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ምውት የሆነ ሰው መንፈሳዊ ሥራን ሊሠራ አይችልም። ከውጤቱ አንጻር ስናየው ፍጹም ውድቀት የውጤት አስገኝ ጸጋን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ይጠይቃል። ኤፌሶን 2፡8፡- “ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም” ይላል። ይህን ክፍል በሚመለከት የተለያየ አተረጓጎም ቢኖርም፥ ክፍሉ ጸጋ፥ ደኅንነትና እምነትም ጭምር የሚመጡት ከእግዚአብሔር መሆኑንና በርሱ ሥራ በማያምን ሰው ልብ ውስጥ ሊፈጠሩ አለመቻላቸውን ነው። ቻርልስ ሆጅ ስለዚህ ነጥብ ሲጽፍ፡- “የውርስ ኃጢአት መንፈሳዊ ሞትን አስከትሎ ማንኛውንም ዓይነት መንፈሳዊ በጎነት የማድረግ ችሎታን አጥፍቷል፤ በሚለው አቋም የሚስማሙ ሁሉ ከዚህ ሁኔታ ለመዳን የሚቻላቸው በየትኛውም ዓይነት ግብረገባዊ ወይም መለኮታዊ የማሳመኛ ክርክር ሂደት ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ታላቅ ኃይልና ቅጽበታዊ ተግባር ነው” ብሏል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው መንፈሳዊ ሞት ደረጃና ፍጹም ውድቀት የገለጠውን ነገር ከተቀበልን፥ የችግሩ መፍትሔ የውጤት አስገኝ ጸጋ ትምህርት መሆኑንም መቀበል አለብን። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ሕይወትን ሊሰጥም ሆነ የሰውን ፈቃድ ሊያድስ አይችልም። ወንጌልንና በውስጡ ያሉ ዋና ነገሮችን የሚመለከት መረዳትን የሚሰጥ ብቻ ነው። መረዳት ብቻ ደግሞ ባገኘነው አዲስ እውቀት ላይ ተግባራዊ እርምጃ እንድንወስድ ሊያደርገን አይችልም።

*ከዳግም ልደት ጋር ያለው ተመሳሳይነት።* ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑ ከዳግም ልደት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጋር ባለው ተመሳሳይነት ይደገፋል። ልክ እንደ ውጤት አስገኝ ጸጋ፥ የዳግም ልደት ሂደትም የማግባባት ጉዳይ ወይም ምክንያታዊ ለውጥ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ዳግም ልደት ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ ከሆነ፥ ውጤት አስገኝ ጸጋም በዚሁ ውስጥ ይካተታል። ሁለቱም በቀላሉ የማንረዳቸው ቢሆኑ እንኳን ለደኅንነት አስፈላጊዎች ናቸው።

# 6. በውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ ትምህርት ላይ የሚቀርቡ ተቃውሞዎች

*ከሰው ጥረት አንጻር።* ሰፋ ባለ ሁኔታ በእምነት ላይ የተመሠረተ ትምህርት፥ በምክንያት ላይ ከተመሠረተ ትምህርት ይልቅ ተቃውሞ እንደሚገጥመው የታወቀ ነው። የተለመደው ተቃውሞ፥ “ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሰው ልጅ ለማመን የሚያደርገውን ጥረት ሁሉ ይጻረራል” የሚል ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጅ ለውጤት አስገኝ ጥሪም ሆነ በክርስቶስ ማመንን በሚመለከት ስላለበት ኃላፊነት በቂ ምስክርነት ይሰጣሉ። የሰው ልጅ የሚያደርገው ጥረት ከመለኮት ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት መገንዘብ የሚያስቸግር መሆኑ እርግጥ ነው። የዚህ ችግር መፍትሔ ግን ከእምነት ውጭ ሊገኝ አይችልም። በውጤት አስገኝ ጸጋ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ የሰውን ልጅ ኃላፊነቱን ከመወጣት ወደ ኋላ ሊጎትተው አይገባም። ነገር ግን እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ሰው ለማድረግ መሻት የለበትም። በደኅንነት ክልል ውስጥም ሰው መፈለግ ያለበት ለመዳን ነው እንጂ ራሱን ለማዳን አይደለም። የደኅንነት ምስጢር ሊያድነን በሚችለው በእግዚአብሔር ላይ በመደገፋችን የተወሰነ ነው።

ከማመናችን በፊት የጸጋ ሥራ አስፈላጊ መሆኑን መረዳታችን፥ የሰዎችን ደካማነት ይበልጥ ያስገነዝበናል። በዚህም የተነሣ ሰዎች ሁሉን ማድረግ በሚችል እግዚአብሔር ላይ ራሳቸውን መጣል እንዳለባቸው እንረዳለን። ክርስቶስ እንዲፈውሰው የለመነው ዓይነ ስውር ራሱን ለማዳን ፈጽሞ አለመቻሉ ከልመና አላገደውም። ነገር ግን፥ መሻቱ ሊያድነው ወደሚችለው ክርስቶስ መራው። ስለዚህ ይህ ፍጹም ውድቀትን የሚመለከት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ በሚያደርገው ጥረት ተስፋ ከማስቆረጥ ይልቅ፥ የእግዚአብሔርን ኃይል ሊያጎላና የደኅንነትን ፍጹም አስፈላጊነት ሊገልጥ ይገባል። ቅዱሳት መጻሕፍት ይህን ጉዳይ እንዲህ በማለት ያስታውሱናል፥ “አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም” (ዮሐ. 6፡37)። በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ጥሪ እርግጠኛነት ይታየናል። የተመረጡ ሁሉ ወደ ክርስቶስ ይመጣሉ። በሌላ በኩል ወደ ክርስቶስ የሚመጣ ሁሉ ወደ ውጭ አይወጣም። ስለዚህ የሰው ልጅ ወደ ክርስቶስ የመምጣት ኃላፊነቱ እንዳልተነሣለት እናያለን።

*የሰው ኃላፊነት በተቃራኒው ሲታይ።* በውጤት አስገኝ ጸጋ ትምህርት ላይ የሚነሣው ሁለተኛ ተቃውሞ መሠረት ደግሞ፥ “ትምህርቱ የሰውን ልጅ ኃላፊነት ይጻረራል”፤ ሥራውን የሚሠራው እግዚአብሔር

ራሱ ብቻ ከሆነ፥ የሰው ልጅ ባለማመን ኃላፊነት መጠየቅ የለበትም የሚል ነው። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ብቁ አለመሆን ኃላፊነትን ያስወግዳል አይልም። የሰው ልጆች የሚፈረድባቸው የተለመደውን ኃጢአታዊ ተፈጥሮ በመከተላቸው ነው። "በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል" (ዮሐ. 3፡18) የሚለው እውነት የማይለወጥ ነው። ያለመብቃት ጉዳይ ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ተቀንሷል። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ የሰውን ፈቃድ ለማደስ ወይም ሰውን ወደ ደኅንነት ለማምጣት በቂ ባይሆንም፥ የወንጌልን ቃል፥ የደኅንነትን አስፈላጊነት፥ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የሚያመጣውን ፍርድና የሰው ልጅ ክርስቶስን የመቀበል ኃላፊነት እንዳለበት ለመግለጥ ይችላል፥ ይገልጣልም። እግዚአብሔር ለማመን የሚፈቅደውን ማንኛውንም ሰው እንደማይቃወም ግልጥ ነው። ውጤት አስገኝ ጸጋ በሌለበት በማንኛውም ሁኔታ ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን እንመለከታለን። በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና በሰው ልጅ ኃላፊነት መካከል ያለውን ግንኙነት በሰው አእምሮ ለመፍታት ባይቻልና አለመጣጣም ያለ ቢመስል እንኳን ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል መገለጥ በእምነት ሊቀበል ይችላል።

*በቂ ጸጋ ለሁሉም ተሰጥቷልን?* የውጤት አስገኝ ጸጋን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚቃወመው ሦስተኛ አሳብ፥ ለማመን የሚያስችል በቂ ጸጋ ለሰው ልጆች ሁሉ ተሰጥቷል በሚለው የተሳሳተ ቅድመ አሳብ ላይ ይመሠረታል። በዚህ ትምህርት መሠረት ውጤት አስገኝ ጸጋ የሚታየው አንዳንድ ጊዜ የሚፈለገውን ውጤት የሚያመጣ፥ በሌላ ጊዜ የማይሳካለት ሆኖ ነው። ይህ ከፊል-ፐሌጂያን [Semi-Pelagian] የሥነ-መለኮት ትምህርት አስተሳሰብ ሲሆን፥ በአንዳንድ አተረጓጎም ረገድ ልዩነት ቢኖራቸውም የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና፥ የአርምኒያንም አቋም ነው። የዚህ ተቃውሞ ደካማ ጎን "ሁሉም እንዲያምኑ በቂ ጸጋ ተሰጥቷቸዋል" የሚለው የተሳሳተ እምነት ነው። ይህን ቅዱሳት መጻሕፍት አያስተምሩም፤ ከሕይወት ልምምድ ጋርም የሚጋጭ ነው። አንዳንድ ሰዎች ወንጌልን እየሰሙ የጸጋን ሥራ የሚቃወሙት ጸጋው በባሕርዩ ውጤት አስገኝ ስላልሆነ ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ለተመረጡት የደረሰው የእግዚአብሔር የደኅንነት ጥሪ ውጤታማነቱ እርግጠኛ በመሆኑ የተጠሩት ሁሉ በዚህ ጸጋ ድነዋል። የአርምኒያን አመለካከት ለዚህ እውነታ በቂ ማብራሪያ የለውም።

የውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ ትምህርት የሰው አእምሮ የማይረዳው ነገር ነው። የውጤት አስገኝ ጸጋን ፅንሰ-አሳብ መረዳትን አስመልክቶ የሚነሡ ችግሮች ሁሉ መፍትሔ የሚገኝላቸው አይደሉም።

ይህም የሰው ልጅ መለኮታዊው ሥራ ማለትም ደኅንነት በሕይወቱ እንዴት እንደሚከናወን ለመገንዘብ ካለበት የእውቀት ውሱንነትና የራሱ ፈቃድ ከተሳሳተ ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባው ከመሆኑ የተነሣ እንጂ፥ የተገለጡት እውነቶች በራሳቸው ሥርዓት የማይሄዱ ሆነው አይደለም። ተፈላጊውን ውጤት የሚያስገኝ ጥሪ መኖሩን የሚያረጋግጡ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ይህን ትምህርት መቃወም፥ መለኮታዊን የደኅንነት ዕቅድ እርግጠኛ ተፈጻሚነትን እንደመካድ ነው።

# 14

# ዳግም ልደት

## 1. የዳግም ልደት አስፈላጊነት

ከማንኛውም የሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርቶች ይልቅ የዳግም ልደት መሠረታዊ ትምህርት ለውጤታማ ስብከት እንደ መልህቅ የሚቆጠር ነው። የዚህን ትምህርት ባሕርይ ከግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት አለመቻልና አስፈላጊነቱን በግልጥ አለመረዳት፥ የወንጌል ስብከት የሚፈለገውን ውጤት እንዳያስገኝ ያደርገዋል። ወንጌላውያንም ሆኑ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን ይህን ትምህርት በሚገባ መረዳት እንዳለባቸው ሊገነዘቡ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳግም ልደት የሚያቀርበው ፅንሰ-አሳብ ቀላል ነው። ስለሆነም ለትክክለኛነት ስብከት ሃይማኖታዊ ታሪኩን ማጥናቱ በፍጹም አስፈላጊ አይደለም። መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ታሪክ ግን ይህ ጉዳይ ለችግር የተዳረገ መሆኑን ገልጦ፥ ትምህርቱን በሚገባ አለመረዳት አደገኛ መሆኑን ያስጠነቅቃል። የዳግም ልደት መሠረታዊ ትምህርት በሚገባ ለሚመለከቱት፥ ለሚያስቡበትና ከዚህ እውነት ባገኙት ብርሃን ለሚኖሩ ሁሉ በረከትን ያስገኛል።

## 2. የዳግም ልደት ትርጉም

*የቃሉ ፍቺ።* በአጠቃላይ የዘላለምን ሕይወት ከመስጠት ጋር የተያያዘ ቢሆንም፥ ዳግም ልደት የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ስፍራ ብቻ ነው የሚገኘው (ማቴ. 19፡28፤ ቲቶ 3፡5)። ከእነዚህ ሁለት ስፍራዎች በአንዱ ብቻ በዚህ ስሜት ቀርቧል። እሱም "ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ" የሚለው ነው (ቲቶ 3፡5)። 'ፓሊንጄኔስያስ' ['palingenesias'] የሚለው የግሪክ ቃል "አዲስ ልደት፥ እንደገና መሠራት፥ መታደስ፥ እንደገና መፈጠር" በሚሉ ቃሎች በሚገባ ተተርጉሟል። ይህ ቃል ለሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን፥ በሺሁ ዓመት መንግሥት የሚታደሱትን ሰማይና ምድርንም በሚመለከት አገልግሎት ላይ ውሏል (ማቴ. 19፡28)። ዳግም ልደት ከሰው ተፈጥሮ ጋር ያለውን ግንኙነት ስንመለከት የዘላለምን ሕይወት የሚገልጡ የተለያዩ አገላለጦችን እንደሚያካትት መመልከት እንችላለን። እነርሱም አዲስ ሕይወት፥ አዲስ ልደት፥ መንፈሳዊ ትንሣኤ፥ አዲስ ፍጥረት፥ አዲስ አእምሮ፥ ሕያው ሆኑ፥ የእግዚአብሔር ልጆችና ወደ መንግሥቱ መፍለስ የሚሉት ናቸው። በቀላል

አባባል ስንገልጠው፥ ዳግም ልደት በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ የዘላለምን ሕይወት ሊወክሉ የሚችሉ ነገሮችን በሙሉ ያካትታል።

*በሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ ያለው አጠቃቀም።* የሥነ-መለኮት ሊቃውንት "ዳግም ልደት" በሚለው ቃል ላይ ያላቸው መረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር ትንሽ የተምታታ ነው። እንደ "መለወጥ"፥ "መቀደስ" እና "መጽደቅ" የመሳሰሉት ቃላት በዳግም ልደት አሳብ ውስጥ በመመሳሰል ወይም በመካተት ይገለጣሉ። የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት፥ ዳግም ልደት፥ በደኅንነት ውስጥ የሚካተቱትን እንደ መጽደቅና መቀደስ ብቻ ሳይሆን፥ የመክበርንም አሳብ እንደሚያጠቃልል አድርጋ ትቆጥራለች። በሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት "ዳግም ልደት" የደኅንነትን መንገድ፥ ተግባር፥ ሂደትና የመጨረሻ ግቡን ሁሉ እንደሚያካትት ተደርጎ ተወስዷል።

የፕሮቴስታንት ሥነ-መለኮት ሊቃውንት የዳግም ልደትን ትርጉም በማስፋፋት ረገድ ብዙ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ከቀድሞ ጀምሮ የነበሩ ሉተራውያን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዳግም ልደት፥ አንድ ኃጢአተኛ ጠፍቶ ከነበረበት ሁኔታ መጽደቅን ጨምሮ ወደ ደኅንነት የሚደርስበትን ጠቅላላ ሂደት እንደሚጨምር አድርገው ተጠቅመውበታል። ኋላም ሉተራውያን መጽደቅ የሕይወትን መታደስ (ለውጥ) የሚጨምር ስላልሆነ፥ የዳግም ልደት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መቀደስን አያካትትም፥ የሚለውን አቋም በመያዝ ይህን መሠረታዊ ትምህርት የሚመለከት ማብራሪያ ለመስጠት ሞክረዋል። የሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕፃናት በውኃ ጥምቀት ጊዜ ዳግም ይወለዳሉ የሚለውን አቋማቸውን አሁንም እንደያዙ ናቸው። እንዲህም ሆኖ ይህ ዳግም ልደት ወደምትታየው ቤተ ክርስቲያን የመግባታቸው ምልክት እንጂ፥ እውነተኛ ደኅንነት መቀበላቸውን የሚያመለክት አይደለም ይላሉ። ስለዚህ በዚህ አቋማቸው ዳግም ልደት ለደኅንነት የዝግጅት ሥራ ይገልጣሉ።

የሕፃናትን ዳግም ልደት በሚመለከት ቫለንታይን የተባለው የሉተራን ሥነ-መለኮት ሊቅ፥ "ሕፃናት ዳግም የሚወለዱት በጥምቀት ነው እንበልን? መልሳችን በሚገባ አዎን፥ የሚል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህን የምንለው የሕይወት መሠረቱና ፈጻሚው ጸጋው በመሆኑ፥ የመጨረሻ ቃል ኪዳናዊ የሆነ ሥራ ከእግዚአብሔር በሚሰጥ ጽድቅ፥ በመንፈስ ቅዱስ ቸርነት እና ኃይል የሚሆን ነው ለማለት ይቻላል" ብሏል። ሆኖም ቫለንታይን ጥምቀት ለሕፃናት አዲስ ልደትን ይሰጣል የሚለውን አባባል ይቃወማል። ቫለንታይን በሌላ ስፍራ ሲጽፍ፥ "መጽደቅ ከዳግም ልደት እና ከመቀደስ የሚቀድም ነው" ብሏል። የሉተራውያን ሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዳግም ልደት የሚለውን ቃል መጽሐፍ ቅዱስ

የዘላለም ሕይወት ስለመስጠት በሚናገር ስሜት አይጠቀሙበትም። መቀደስን ከዳግም ልደት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውጭ ማድረጋቸው ግን እርግጥ ነው።

ከተሐድሶ ሥነ-መለኮት ሊቃውንት አንዱ ካልቪንና ተከታዮቹ ይህን ጉዳይ በሚመለከት አንድ ጥርት ያለ አቋም ባለመያዝ ሌሎች የሠሩትን ስሕተት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ፈጽመዋል። በአሥራ ሰባተኛው ክፍለ-ዘመን አካባቢ መለወጥ ከዳግም ልደት ጋር ተመሳሳይ ተደርጎ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ አመለካከት መለወጥ የሰው፥ ዳግም ልደት ደግሞ የእግዚአብሔር ተግባር የመሆኑን ዋና መሠረታዊ እውነት የዘነጋ ነበር። ከዚህም ሌላ መለወጥ ብዙ ጊዜ ከዳግም ልደት ጋር የተያያዘ ቢሆንም፥ ክርስቶስ በተነበየው በጴጥሮስ መመለስና መታደስ (ሉቃስ 22፥32) እንደሚታየው ሁልጊዜ የሚሆን ግን አይደለም። ካልቪን እንኳ በመለወጥና በዳግም ልደት መካከል ግልጥ የሆነ ልዩነት ማሳየት ሳይችል ቀርቷል። ቻርልስ ሆጅ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለጥ ግሩም የሆነ አሳብ አቅርቧል። ሼድ ከሆጅ ጋር በመስማማት የሚከተለውን ተነጻጻሪ አሳብ አቅርቧል፥ "ዳግም ልደት በአንድ ወቅት የሚሆን አንድ ድርጊት ሲሆን፥ መለወጥ ግን አንድ ተግባር ወይም ሂደት ነው። ዳግም ልደት የሕይወት መነሻ ሲሆን፥ መለወጥ የሕይወት ዘገምተኛ ለውጥና መግለጫ ነው። ዳግም ልደት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ተግባር ሲሆን፥ መለወጥ ግን ሙሉ በሙሉ የሰው ልጅ ተግባር ነው። ዳግም ልደት ምክንያት፥ መለወጥ ግን ውጤት ነው። ዳግም ልደት ቅጽበታዊ፥ መለወጥ ግን ሂደታዊ ነው" ብሏል።

ባለፈው ምዕተ ዓመት የካልቪኒዝም ሥነ-መለኮታዊ ሊቃውንት ዳግም ልደት የዘላለም ሕይወት መስጠትን በሚገባ እንደሚያመለክት ተስማምተዋል። ቻርልስ ሆጅ እንዳለው:- "ዳግም ልደት የሚጠቅመው፥ ለጠቅላላ የመቀደስ ሥራ ወይም በመለወጥ ውስጥ ለሚኖር የመጀመሪያ ሥራ፥ ደግሞም መለስተኛ ለሆነ የማጽደቅ ሥራ ወይም በየትኛውም ደረጃ ለሚታይ ውጫዊ ለውጥ አይደለም። ነገር ግን ሰው ከመንፈሳዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ለሚሸጋገርበት ቅጽበታዊ ለውጥ ነው። ይህ በአሁኑ ጊዜ ስለ ዳግም ልደት የተደረሰበት ሁለንተናዊ ስምምነት ነው።" ስለዚህ የዳግም ልደትን መሠረታዊ ትምህርት የሚያጠና ሰው ማተኮር ያለበት፥ ደኅንነት የዘላለምን ሕይወት ከመስጠት ጋር ያለውን የግንኙነት አቅጣጫ ነው። በደኅንነት ውስጥ የዘላለም ሕይወትን በመስጠት ሥራ ዙሪያ ያሉ የሚቀድሙ ወይም ከእርሱ ቀጥለው ወዲያውኑ የሚመጡ ነገሮች ተለይተው ለብቻቸው የሚታዩና የእግዚአብሔር ሥራዎች መሆን አለባቸው።

## 3. ዳግም ልደት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው

*የእግዚአብሔር ሥራ።* ዳግም ልደት በባሕርዩ ፍጹም የእግዚአብሔር ሥራ ነው ። አንዳንድ ጊዜ እንደ ውጤት የታየ ቢሆንም፥ እያንዳንዱ ሁኔታ የሚያመለክተው ዳግም ልደት የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ነው። እጅግ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ዳግም ልደት ይናገራሉ (ዮሐ. 1፡13፤ 3፡3-7፤ 5፡21፤ ሮሜ 6፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ ኤፌ. 2፡5፥ 10፤ 4፡24፤ ቲቶ 3፡5፤ ያዕ. 1፡18፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡9)። ዳግም የተወለደ ሰው ከእግዚአብሔር ተወለደ እንጂ "ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለደም" (ዮሐ. 1፡13) ተብሎ በግልጥ ተጽፏል። ዳግም ልደት ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ከሆነው ትንሣኤ ጋር ተመሳሳይ ነው (ዮሐ. 5፡21፤ ሮሜ 6፡13፤ ኤፌ. 2፡5)። በሌሎች ክፍሎች ደግሞ ዳግም ልደት በባሕርይ ከእግዚአብሔር የሆነ የመፍጠር ሥራ ተደርጎ ቀርቧል (ኤፌ. 2፡10፤ 4፡24፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡17)። እንግዲህ ዳግም ልደት ከሌሎች አስፈጻሚ አካሎች ተለይቶ በእግዚአብሔር ተአምራዊ ኃይል የሚፈጸምና የሱ ሥራ መሆኑን በግልጥ ለመመልከት እንችላለን።

*ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሥራ ነው።* ዳግም ልደት በሚገባ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሥራ ነው። እንደ ሥርየት አስገኝ ጸጋ ሁሉ የዳግም ልደት ሥራም ብዙ ጊዜ የተገለጠው በሥላሴ አካላት መካከል ልዩነት ሳይደረግ በእግዚአብሔር ሥራነቱ ሲሆን፥ በጥቂት ቦታዎች ተለይቶ የእግዚአብሔር አብ፥ የእግዚአብሔር ወልድ፥ በሌሎች ጥቂት ስፍራዎች ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተደርጎ ቀርቧል። ቢያንስ በአንድ ስፍራ የሥላሴ የመጀመሪያው አካል የዳግም ልደት ምንጭ እንደሆነ ተገልጧል (ያዕ. 1፡17-18)። ክርስቶስ ከዳግም ልደት ጋር የተያያዘበት ሁኔታም በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራዎች ተጠቅሷል (ዮሐ. 5፡21፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡12)። መንፈስ ቅዱስ የዳግም ልደት ፈጻሚ እንደሆነ በግልጥ ቀርቧል (ዮሐ. 3፡3-7፤ ቲቶ 3፡5)። የሥላሴ አካላት አንድነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ እያንዳንዱ አካል የራሱ የሆነ ድርሻ አለው። በሌሎቹ የእግዚአብሔር ሥራዎች እንደሆነው ሁሉ፥ የሥላሴ አካላት በክርስቶስ መፀነስ ውስጥ ስፍራ ነበራቸው። በዳግም ልደትም የመጀመሪያው የሥላሴ አካል የአማኙ አባት ይሆናል፤ ሁለተኛው የሥላሴ አካል የራሱን የዘላለም ሕይወት ይሰጠዋል (1ኛ ዮሐ. 5፡12)፥ ሦስተኛው የሥላሴ አካል፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ዳግም ልደትን በብቃት የሚያስፈጽም ይሆናል። የደኅንነት ሥራ የክርስቶስ ነው ባልንበት መንገድ የዳግም ልደት ሥራ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ነው ለማለት እንችላለን።

## 4. ዳግም ልደት የዘላለምን ሕይወት የማግኘት ሂደት ነው

*የዘላለም ሕይወት ለዳግም ልደት ማዕከሉ ነው።* በዳግም ልደት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ያለው ማዕከላዊው ነገር ዘላለማዊ ሕይወት ማግኘት ሲሆን፥ ያስፈለገውም በመንፈሳዊ ሞት መከሠት ምክንያት ነው። የዘላለም ሕይወት የሚገኘው እንዴት እንደሆነ ለመረዳት የሚታይ ዘዴ ወይም ሂደት ስለሌለ በእርግጥ አስቸጋሪ ይሆናል። ዳግም ልደት በባሕርዩ ተአምራዊ ስለሆነ ከሰው አእምሮ በላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዳግም ልደት ውስጥ የሚገኘውን የዘላለም ሕይወት ለመግለጥ ሦስት የተለያዩ ምሳሌዎች ያቀርባል።

*አዲስ ልደት።* አንዳንድ ጊዜ ዳግም ልደት አዲስ ልደት በሚለው ሥዕላዊ አገላለጥ ይቀርባል። ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ እንዳለው "እንደገና መወለድ ያስፈልጋል" (ዮሐ. 3፡7)። ከሰብአዊ ወላጆች ከመወለድ ጋር ሲነጻጸር ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን "ከእግዚአብሔር" መወለድ አለበት (ዮሐ. 1፡13)። በያዕቆብ 1፡18 መሠረት፥ "ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን።" ይህ ሥዕላዊ አገላለጥ የእግዚአብሔር ልጅ ከሰማያዊ አባቱ ጋር ያለውን ጥብቅ ግንኙነትና፥ በክርስቶስ ውስጥ ያለ አማኝም ከእግዚአብሔር ከሚመጣ የዘላለም ሕይወት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጥ እጅግ በጥሩ ሁኔታ የቀረበ ነው።

*መንፈሳዊ ትንሣኤ።* ቅዱሳት መጻሕፍት ዳግም ልደትን በመንፈሳዊ ትንሣኤ መስለው በተደጋጋሚ አቅርበውታል። ክርስቲያን "ከሞት ወደ ሕይወት" እንደተሻገረ ተገልጧል (ሮሜ 6፡13)። ደግሞም እግዚአብሔር፥ "ገና በበደላችን ሙታን በነበርን ጊዜ በክርስቶስ ሕያዋን እንዳደረገን" ተጽፏል (ኤፌ. 2፡5)። ኢየሱስ ራሱም እንዲህ ብሏል፦ "እውነት እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ" (ዮሐ. 5፡25)። በትንሣኤ ሕያዋን የመሆናችን እውነት ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሸጋገሩ ሰዎች እንድንኖር የሚያበረታታን ሆኗል (ሮሜ 6፡13፤ ኤፌ. 2፡5-6፤ ቈላ. 2፡12፤ 3፡1-2)።

*አዲስ ፍጥረት።* ዳግም ልደት በፍጥረት ወይም እንደገና በመፍጠር ሥራም ተገልጧል። "መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" (ኤፌ. 2፡10)፤ ስለዚህ "ለእውነትም በሚሆን ጽድቅ እና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ ተብለን ተመክረናል (ኤፌ. 4፡24)። በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17 የተሰጠው ማብራሪያ እጅግ ግልጥ ነው። "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ

ፍጥረት ነው፥ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል።" ዳግም ልደትን የሚገልጠው የአዲስ ፍጥረት አምሳያ፥ ይህ ሥራ በባሕርዩ በሰው ሕይወት ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት አዲስ ባሕርይንና አዲስ ችሎታን እንደሚሰጥ የሚያመለክት ነው። ይህን ያገኘ ሰው በዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ዳግም የተወለዱትን ሁሉ የሚያጠቃልለው አዲስ ፍጥረት አካል ይሆናል። የዚህ አዲስ ፍጥረት ራስም ክርስቶስ ነው። ለክርስቲያን የተሰጠው ይህ አዲስ ሕይወት፥ ዳግም በተወለዱት መካከል ብቻ በሚገኘው አዲስ ችሎታና ተግባር የሚገለጥ ይሆናል። ይህም እውነት የመነጨውና የተመሠረተው ለዳኑ ሁሉ በሚሆነው ሌላ መለኮታዊ አገልግሎት ላይም ነው።

*የዘላለምን ሕይወት የተቀበልነው በእምነት ነው።* በዳግም ልደት መሠረታዊ ትምህርት ሊዘነጋ የማይገባው በጣም አስፈላጊ እውነት፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመነ ሰው ሁሉ የዘላለም ሕይወት የተቀበለ መሆኑ ነው። ይህ እውነት፥ ዳግም ልደትን ከደኅንነት የሚቀድም ወይም አንዲት ነፍስ ወደ እምነት ትመጣ ዘንድ የሚያደርጋት ነገር አድርጎ ከማሰብ ያድናል። ዳግም ልደት የደኅንነት ማዕከል ነው። ያለ ዳግም ልደት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ ግንኙነት አይኖረውም። ዘላለማዊ ሕይወትንም ያጣል። ጽድቅ እና ቅድስና በተለይ ኃጢአትን በሚመለከት ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፥ ዳግም ልደት ደግሞ ሕይወትን የሚሰጥ ነው። ይህ ትምህርት ሰው ራሱን የማዳን ውስጣዊ ችሎታ አለው የሚለውን ፍልስፍና ውድቅ ያደርገዋል። ዳግም ልደት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፤ የትኛውም ሰብአዊ ጥረት የዘላለምን ሕይወት ሊሰጥ አይችልም። ትክክለኛው የዳግም ልደት ትምህርት፥ በኃጢአቱ ሟች ለሆነ የሰው ዘር የተትረፈረፈ ቸርነት ላሳየ እግዚአብሔር ስም ክብር ይሰጣል።

## 5. ዳግም ልደት የተፈጸመበት የተለየ መንገድ የለም

*የካልቪን ሥነ-መለኮት ሊቃውንት ለዳግም ልደት የተለየ መንገድ አለ የሚለውን አሳብ ተቃውመዋል።* ሊቃውንቱ መለኮታዊው የዳግም ልደት ሥራ ይፈጸም ዘንድ ምንም ዓይነት የተለየ መንገድ ተግባራዊ አልሆነም ይላሉ። ዳግም ልደትን ለማምጣት ልዩ መንገድ ተግባራዊ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የሚያስችለን ስለ ሥርየት አስገኝ ጸጋ ያለን አመለካከት ነው። የፔሌጂያን እና የአርምኒያን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ፥ ከሰው ልጅ ፈቃድ፥ ከሰው ከፊል ችሎታ እና ከተፈጥሮ ኃይላት ጋር በመተባበር ዳግም ልደትን የሚያመጣ ስለሆነ፥ ዳግም ልደት የሰውን ምግባር የሚጨምር መንገድ እንዳለው ያመለክታሉ።

ይህ አሳብ ችግርን የሚያስነሣ ነው። ምክንያቱም ሰው በደኅንነቱ ውስጥ ሊያደርግ የሚችለው አንዳችም ነገር እንደሌለ ከተቀበልንና የሥርየት አስገኝ ጸጋን መሠረታዊ ትምህርት ካመንን፥ ዳግም ልደት የሚከናወነው ያለ አንዳች የተለየ መንገድ መሆኑን መቀበል አያስቸግርም።

*የሰው ፈቃድ ምንም ውጤት ማምጣት አይችልም።* የካልቪን ሥነ-መለኮት ትምህርት የሥርየት አስገኝ ጸጋን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከመጠበቅ አንጻር የሰው ፈቃድ የነፍስን መዳን በማስገኘት ረገድ ምንም ዓይነት ለውጦችን ለማምጣት አይችልም የሚል አቋም ያለበት ነው። ከእምነት ጋር በተገናኘ ሁኔታም ቢሆን የሰው ፈቃድ ተግባራዊ የሚሆነው በሥርየት አስገኝ ጸጋ ውስጥ ነው። ወንጌልን በመስማት ረገድ የሰው ልጅ ፈቃድ ከሥርየት አስገኝ ጸጋም ውጭ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል። በዳግም ልደት ውስጥም የሰው ፈቃድ አንዳችም ነገር ለማድረግ የሚችል አይደለም። የዳግም ልደት ሥራ ባሕርዩ ማንኛውንም ዓይነት የሰው እርዳታ አይፈልግም። ተፈጥሮአዊ በሆነው የመወለድ ሂደት ውስጥ አንድ ሕፃን ይፀነስ እና ይወለድ ዘንድ የሚያደርገው ነገር እንደሌለ ሁሉ፥ አንድ ሰውም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ዳግም ይወለድ ዘንድ የሚያደርገው አንዳችም ነገር የለም። እርግጥ በአዲስ ልደት ውስጥ የሰው ፈቃድ የዳግም ልደትን ሥራ የሚቃወም አይደለም። በመለኮታዊ ጸጋ እንዲያምንም አይገደድም። በሥጋ ትንሣኤ ጊዜ የአካል ትንሣኤ ይፈጸም ዘንድ የሞተው አካል የሚያደርገው አንዳችም ነገር እንደሌለ ሁሉ፥ በዳግም ልደት ውስጥም የሰው ፈቃድ ምንም ማድረግ አይችልም። ይህ ነገር የሰው ፈቃድ ተጽዕኖ እንደተደረገበት ወይም ሰው ፈቃድን እንደተቀማ የሚያሳይ ወይም የማመን ኃላፊነት እንደሌለበት የሚያመለክት አይደለም። ነገር ግን ዳግም ልደት፥ በሚያምን ሰው ልብ ውስጥ የሚሠራ ፍጹም የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

*ሌላ መንገድ አያስፈልግም።* የዳግም ልደት ሥራ በሌላ በማንኛውም መንገድ የሚፈጸም አይደለም። ብዙ ጊዜ ከዳግም ልደት በፊት የሚፈጸሙ፥ ለሁሉ እንደተሰጠ ጸጋና እሱ እንደሚያስከትለው ውጤት ያሉ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም፥ ከዳግም ልደት ሥራ በግልጥ የተለዩ መሆን አለባቸው። የሥርየት አስገኝ ጸጋ ሥራ ከዳግም ልደት ጋር አብሮ የሚሄድና ፍጹም አስፈላጊ ነገር ቢሆንም፥ በራሱ ዳግም ልደትን የሚያስገኝ አይደለም። ሥርየት አስገኝ ጸጋ ግን ዳግም ልደትን በእርግጠኛነት የሚፈጸምና የሚቻል ነገር ያደርገዋል። ዳግም ልደት ቅጽበታዊ ተግባር በመሆኑ ለአፈጻጸሙ ምንም የተለየ መንገድ አያስፈልገውም። የእግዚአብሔር ሥራ እንደሆነ በተደጋጋሚ መገለጡና ቅዱሳት መጻሕፍት

ስለ ሥርየት አስገኝ ጸጋ የሰጡት መገለጥ ዳግም ልደትን ለማምጣት ሌላ መንገድ ያስፈልጋል የሚለውን ትምህርት ውድቅ ለማድረግ በቂ መረጃዎች ናቸው።

## 6. ዳግም ልደት በልምምድ የምናረጋግጠው ነገር አይደለም

*ልምምድ ዳግም ልደትን ተከትሎ የሚመጣ ነገር ነው።* ስለ ክርስትና እምነት በሚሰጥ ምስክርነት ውስጥ ስለ ዳግም ልደት ልምምድ እጅግ ብዙ ነገር ተብሏል። ዳግም ልደት በቅጽበት የሚፈጸም የመለኮት ፈቃድና ተግባር ከሆነ፥ ልምምድ አይደለም ወደሚል ማጠቃለያ እንደርሳለን። እርግጥ አዲስ ልደትን ተከትለው የሚመጡ እጅግ በርካታ ልምምዶች በሕይወታችን ሊፈጸሙ ይችላሉ። በተለመደው መንገድ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን ልምምድ፥ ከአዲስ ልደት በኋላ ወዲያውኑ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል። ይህ እውነት ዳግም ልደት የልምምድ ውጤት ያለመሆኑን አሳብ የሚሽር አይደለም። ዳግም ልደት ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ ነው በሚለው አሳብ ከተስማማን፥ ልምምድ ጊዜ የሚጠይቅ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ አይሳነንም። ስለዚህ አዲስ ልደትን የሚመለከቱ ልምምዶች በሙሉ ከዳግም ልደት ቀጥለው የሚመጡና ከተገኘው አዲስ ሕይወት የሚመነጩ መሆናቸውን ለማሰብ እንችላለን፤ ይህን ጉዳይ በተመለከተ እውነተኛ ያልሆነን ነገር ልንለማመድ አንችልም። ልምምድ ከመገኘቱ በፊት ዳግም ልደት ሙሉ በሙሉ መፈጸም አለበት። ዳግም የተወለደች ነፍስ ቅጽበታዊ የሆነ የአዲስ ሕይወት ግንዛቤ አላት። የአዲስ ልደት ሥራ ልምምድንም ሆነ ትንተናን የሚመለከት አይደለም። አዲስ ሕይወት የበርካታ ልምምዶች መንሥኤ ሊሆን ይችላል፤ የአዲስ ልደት ሥራን ግን ሰው እንደማገኘውም ልምምድ በራሱ የሚለማመደው አይደለም።

*ዳግም ልደት በልምምድ ላይ የሚመሠረት አይደለም።* ዳግም ልደት በልምምድ ላይ የሚመሠረት አለመሆኑ ያልዳኑ ሰዎች ከዚያ የሚቀድሙና ልንለማመዳቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ ከሚል አሳብ እንዲገላገሉ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አለው። ነፍሳትን ለጌታ ለመማረክ የሚፈልጉትንም ዳግም ልደት ከመፈጸሙ በፊት በከፊልም ቢሆን የደኅንነትን ፍሬ ከመጠበቅ ያድናቸዋል። አንድ ሰው ከመዳኑ በፊት የተለየ ነገር ሊሰማው ይገባል የሚለው አመለካከት፥ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን እምነት ቀላልነት እና ከእግዚአብሔር ብቻ ሊመጣ የሚችለውን እውነተኛ ዳግም ልደት እንዳይረዱት አድርጓቸዋል።

የዳግም ልደት ትምህርት ልምምዳዊ አለመሆኑን የሚገልጠው አሳብ፥ የሉተራውያን ቤተ ክርስቲያን አቋም የሆነው የሕፃናት ዳግም ልደት ትምህርት እንዲጀመር በር ከፍቷል። ከዚህ በመነሣት ዳግም ልደት ልምምድ እስካልሆነ ድረስ፥ ሕፃናት ዳግም የማይወለዱበት ምንም ምክንያት የለም የሚል የመከራከሪያ አሳብ ያቀርባሉ። ሼድ የተባለው የሥነ-መለኮት ሰው ዳግም ልደት ልምምድ እስካልሆነ ድረስ፥ ሕፃናት ዳግም መወለድ ይችላሉ የሚለውን ትምህርት እንደሚከተለው ያቀርባል።

> "ዳግም ልደት ሕሊናዊ ግንዛቤን የማይጠይቅ፥ በሰው ነፍስ ውስጥ የሚሠራ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። በዳግም ልደት ምክንያት የሚፈጠር ውስጣዊ ስሜት የለም። የማንኛውም ሰው ሕሊና በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆነበትን የመንፈስ ቅዱስ ቅጽበታዊ ሥራ ሊገነዘብ አይችልም። ይህ ሥራ የእግዚአብሔር የራሱ ብቻ ስለሆነ፥ ሰው እንዲያውቀው አስፈላጊ አይደለም። ይህ እውነት ሕፃናትን እና አዋቂዎችን በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ስለሚያኖራቸው፥ የሕፃናትን ዳግም ልደት ከአዋቂዎቹ እኩል ያደርገዋል። መጽሐፍ ቅዱስ የሕፃናትን ዳግም ልደት በሚመለከት ያስተምራል። ሉቃስ 1፡15፦ 'ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል።' ሉቃስ 18፡15-16፦ 'ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተውአቸው አትከልክሏቸው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና።' የሐዋርያት ሥራ 2፡39፦ 'የተስፋው ቃል... ለልጆቻችሁ ነው'፥ 1ኛ ቆሮ. 7፡14፦ 'ልጆቻችሁ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።' የሕፃናት ዳግም ልደት በአምሳያም ተገልጧል። ሀ. በብሉይ ኪዳን በነበረ የሕፃናት ግርዘትና ለ. በአዲስ ኪዳን ባለ የሕፃናት ጥምቀት።"

ሼድ በማስረጃነት ካቀረባቸው ጥቅሶች አንዳቸውም የሕፃናትን ዳግም ልደት አያረጋግጡም። የዳግም ልደት ተግባር የሚጠቀስበት አስቸጋሪ ልምምድ መኖሩን ብዙ ክርስቲያኖች ባያውቁትም ስለ ሕፃናት ዳግም ልደት ግልጥ ማረጋገጫ የሚያቀርቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሉም። ዳግም ልደት የሚፈጸምበት ትክክለኛው ጊዜ የሚያድን እምነት በተገለጠበት ቅጽበት ነው። ዳግም ስለተወለዳችሁ እመኑ የሚል ጥያቄ ለሰው ልጆች የቀረበበት ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። ነገር ግን አምነው የዘላለምን ሕይወት እንዲቀበሉ ነው የተጋበዙት። ክርስቲያኖች ክርስቶስን ከመቀበላቸው በፊት "በኃጢአታቸውና በበደላቸው ሙታን እንደነበሩ" በግልጥ ተነግሯቸዋል (ኤፌ. 2፡1)።

ውሳኔ ለማድረግ ከሚችሉበት ዕድሜያቸው በፊት የሚሞቱ ሕፃናት ሁኔታ የተለየ ችግር ነው። ትክክለኛው መሠረታዊ የእምነት

ትምህርት፥ ሕፃናት ዳግም የሚወለዱት በሚሞቱበት ጊዜ ነው እንጂ ከዚያ በፊት አይደለም፥ ውሳኔ ከሚያደርጉበት ዕድሜ ከደረሱ ደግሞ ዳግም የሚወለዱት ክርስቶስን በሚቀበሉበት ቅጽበት ነው የሚል ይመስላል። የሕፃናት ጥምቀት ዳግም ልደትን ለማምጣት የሚያስችል አለመሆኑ ግልጥ ነው። ይህን ጉዳይ የሚመለከተው የካልቪን ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት የሉተራውያንን ትምህርት ይቃረናል። የሕፃናትን ዳግም ልደት መሠረታዊ ትምህርት ከተቀበልን፥ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ እንገባለን። ለዘላለም ድኗል ልንል የማንችለውን ሰው ዳግም የተወለደ ነው ማለቱ በጣም አስቸጋሪ ነው።

## 7. የዳግም ልደት ውጤት

ከዳግም ልደት ሥራ ጋር የተያያዙ ነገሮች እጅግ ብዙ ናቸው። በአንድ ወቅት ሙት የነበረች ነፍስ የእግዚአብሔርን ሕልውና የሚያሳየውን የዘላለምን ሕይወት ትቀበላለች። የዳግም ልደት ውጤት፥ የዘላለምን ሕይወት ማግኘት ነው በሚለው እውነት ልናጠቃልለው እንችላለን። ሌሎቹ የዳግም ልደት ውጤቶች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት አስፍቶ በመመልከት የሚገኙ ናቸው። ሕይወት የሚለውን ቃል መተርጎም አስቸጋሪ ቢሆንም፥ ዘላለማዊ ሕይወት ቁሳዊ ባይሆንም፥ ዳግም በተወለደ ሰው ሕይወት ግን የሚታዩ ነገሮች ይኖሩታል።

*አዲስ ተፈጥሮ።* የዘላለም ሕይወት ዳግም በተወለደ ሰው ውስጥ ከሚያከናውናቸው ሥራዎች የመጀመሪያው መለኮታዊ ተፈጥሮን ማላበስ ነው። አዲሱ ተፈጥሮ ኃጢአት የማድረግ ችሎታና ፈቃድ ያለውን አሮጌ ተፈጥሮ ሙሉ በሙሉ ሳያጠፋ እንኳን፥ ከዘላለም ሕይወት ቀጥሎ ለሚመጣው የእግዚአብሔር ፈቃድ የመገዛት ከፍተኛ ጉጉት ያለው ይሆናል። አዲሱ ተፈጥሮ "አዲስ ፍጥረት" (2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ ገላ. 6፡15)፥ ወይም "አዲስ ሰው" (ኤፌ. 4፡24) በተባለው ሰው ውስጥ መገኘቱ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣል። አዲሱን ተፈጥሮ በተቀበለ ሰው ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የአኗኗር፥ እንዲሁም ስለ እግዚአብሔርና የእርሱም ስለሆኑ ነገሮች ያለው የአመለካከትና የልባዊ ለውጥ ይጠበቃል።

በዳግም ልደት የሚገኘው አዲስ ተፈጥሮ፥ ከውድቀት በፊት ከነበረው ከአዳም ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ጋር አንድ ተደርጎ ሊታይ አይገባም። የአዳም ተፈጥሮ ያልተፈተነና ኃጢአት የሌለበት ነበር። ዳግም ለተወለደ ሰው እንደ ምንጭና ተፈጥሮውን እንደሚወስን ተቆጥሮ የተሰጠው ዓይነት የዘላለም ሕይወት አልነበረውም። የአዳም ሰብአዊ ተፈጥሮ ለኃጢአትና ለፈተና የተጋለጠና ለመውደቅ የሚችልም ነበር። በዳግም ልደት የሚሰጠው

መለኮታዊ ተፈጥሮ ግን በቀጥታ በኃጢአት ጉዳይ የሚገባ መሆኑ አጠራጣሪ ነው። ዳግም የተወለደ ሰው ኃጢአት ሊያደርግ እንደሚችልና እንደሚያደርግም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ቢናገርም፥ ኃጢአትን የሚያደርገው ሰብእና ስሕተት በጥሞና ቢጤን፥ ኃጢአቱ የኃጢአታዊ ተፈጥሮው ውጤት እንደሆነ እናያለን። ይህ ነገር ክርስቲያን ያለ ኃጢአት መሆን ይችላል ወይም ኃጢአትን ማድረግ አይችልም ከሚለው አባባል ጋር ጨርሶ ሊምታታ አይገባም። ፍጹምነት ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን እስካልተወገደ ድረስ የምንደርስበት ነገር አይደለም። ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን የሚወገደው ሥጋዊ አካላችን ሲሞት ወይም በመነጠቅ ጊዜ የአሁኑ አካላችን ሲለወጥ ነው።

አዲሱ ተፈጥሮ የኃጢአት መነሻ ሊሆን ባይችልም፥ አሮጌውን ተፈጥሮ ሙሉ በሙሉ የማጥፋት ችሎታ የለውም። ድል የማድረጊያ ኃይል የምናገኘው እግዚአብሔር በውስጣችን በማደሩ ምክንያት ነው። አዲሱ ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እናደርግ ዘንድ አዲስ ፈቃድ የሚሰጠን ሲሆን፥ የኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን ዝንባሌ ባለበት ሁኔታ እንኳን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የርሱ ኃይል ያስችለናል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆናችንን የምናውቀው በአዲሱ ተፈጥሮ ፈቃድ ውስጥ ስንገባ ነው። አዲሱ ተፈጥሮ አዲሱን ሕይወት ያመጣ ስለሆነ፥ ዘላለማዊ ሕይወትና አዲሱ ተፈጥሮ ሊለያይ በማይችል ሁኔታ አንድ ሆነዋል።

*አዲስ ልምምድ።* ዳግም ልደት በራሱ ልምምድ ባይሆንም የበርካታ ልምምዶች ምንጭ ነው። ዘላለማዊ ሕይወትን የመስጠት ተግባር ቅጽበታዊ በመሆኑ ልምምድ ሊሆን ባይችልም፥ ከዳግም ልደት በኋላ የሚኖረው ዘላለማዊ ሕይወት የአዲሱ መንፈሳዊ ልምምድ ምንጭ መሆኑ የሚጠበቅ ነው። አዲስ ሕይወት አዲስ ችሎታን ይዞ ይመጣል። ከዳግም ልደት በፊት በመንፈሱ ሙት የነበረና ለመንፈሳዊ እውነት ዕውር የነበረ ሰው፥ በዳግም ልደት ለአዲስ ዓለምና እውነት ሕያው ይሆናል። አንድ ዕውር ሰው ዓይኑ በሚበራለት ጊዜ የቀለምን ውበትና እይታ ለመገመት እንደሚሞክር፥ አዲስ የተወለደ ሰው ነፍስም መንፈሳዊ እውነትን ለመረዳት ሙከራ ታደርጋለች። የመንፈስ ቅዱስን የማስተማር አገልግሎትም ለመጀመሪያ ጊዜ ለመረዳት ይችላል። ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረትን ማድረግንና በፍጹም ነጻነት የመጸለይ ደስታን ይለማመዳል። ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር በዋለ መጠን፥ ለፍጥረታዊ ሰው ፍጹም እንግዳ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ መለማመድ ይጀምራል። ሁለንተናው ደስታ፥ ኀዘን፥ ፍቅር፥ ሰላም፥ ምሕረትና በመንፈሳዊ ዓለም

ውስጥ ያሉትን እውነቶች ሁሉ ለመለማመድ አዲስ ችሎታ ያገኛል። ዳግም ልደት ልምምድ ባይሆንም፥ የክርስቲያናዊ ልምምዶች ሁሉ መሠረት ነው። ዳግም ልደት ከደኅንነት ተለይቶ የማይታይና ራሱን በሰጠ ክርስቲያን ጤናማ ልምምድ ውስጥ የሚገለጥ ነው። ሰውን ወደ ክርስቲያናዊ ልምምድ የማይመራ ዳግም ልደት አጠያያቂ ይሆናል።

*የዘላለም ዋስትና።* ዳግም ልደትን በሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ የሚነሣው አንዱና ዋናው ውዥንብር፥ አንዲት ነፍስ በትክክል ዳግም ከተወለደች ደኅንነትዋ ለዘላለም የተጠበቀ ነው የሚለውን ትምህርት ላለመቀበል ከሚደረግ ጥረት የተነሣ የሚፈጠረው ሁኔታ ነው። የዘላለም ሕይወት የተሰጠው ሰው ሊወሰድበት አይችልም። ይህ ዳግም የተወለደውን ሰው ወደ ክብር ለማምጣት እግዚአብሔር ያለውን የማይሻር ዓላማ ያሳያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ዳግም የተወለደ ሰው ከቶ አናይም። ክርስቲያኖች በኃጢአት ምክንያት ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድ ሲያጡ፥ በንዛዜና በመመለስ መታደስ ቢያስፈልጋቸውም የዳግም ልደት መሠረታዊ እውነት ግን ሊለወጥ አይችልም። በመጨረሻ ልናስበው የሚገባ ነገር፥ ይህ በምድር የምናየው መንፈሳዊ ልምምድ፥ ዳግም የተወለደ ሰው ከኃጢአትና ከፈተናው ነጻ ከሆነ በኋላ ለሚጠብቀው ከፍተኛ ልምምድ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ነው። ዳግም ልደት በሙላት የሚገለጠው ዳግም የተወለደው ሰው ሙሉ ለሙሉ በሚቀደስበትና በሚከብርበት ጊዜ ነው። በዚህ ምድር የምንለማመደው ነገር በኃጢአታዊ ተፈጥሮአችንና አካላችን ምክንያት እጅግ ውሱን ሆኖ የከበረውን የዘላለም ሕይወት በጥቂቱ ብቻ ያሳያል። በሕይወት የምንለማመደው ነገር ግን ዳግም ልደትን፥ ቋሚ ተስፋንና የውስጥ እርግጠኛነትን የሚያመለክት መሆን አለበት። ‘‘በእናንተ መልካሙን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቻለሁ’’ (ፊልጵ. 1፥6)።

# 15

# የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

## 1. ለረጅም ጊዜ የታወቁ የአመለካከት ልዩነቶች

ከአማኙ ደኅንነት ጋር ከተያያዙ በርካታ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መካከል በጣም የሚያስቸግረው፥ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት የሚመለከት ትምህርት ማቅረብ ነው። በባሕርዩ ከሥርየት አስገኝ ጸጋ በጣም ቀለል ያለ ቢሆንም፥ እጅግ በርካታ የሆኑ ትርጉሞች ስለተሰጡት ሰዎች ዋና ትርጉሙን በማይገባ መንገድ ተረድተውታል። በአጠቃላይ ሲታይ ይህን መሠረታዊ ትምህርት በሚመለከት የተለያዩ አመለካከቶችን ያንፀባረቁ ጸሐፊዎች ሁሉ፥ በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ላይ ይስማማሉ። ያም ሆኖ ማንኛውም ጸሐፊ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያለው የአመለካከት አዝማሚያ አጠቃላይ አቋሙን ለመገምገም እንደ መሠረት ሊቆጠር ይችላል። መሪል ኤፍ. ኧንገር [Merrill F. Unger] "የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ሥራ" በሚል ርእስ በቅርቡ በጻፈው መጽሐፍ፥ ለብዙ ጊዜ የታወቀውን የተሳሳተ አመለካከት ለማስተካከል ሞክሯል።

ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በመመርመር ረገድ ውዥንብር የሚፈጠረው በብዙ ምክንያቶች ነው። ለልዩነቶች መፈጠር ዋናው ምክንያት ግን፥ የቤተ ክርስቲያንን ልዩ ባሕርይ ለይቶ ለማወቅ አለመቻል ነው። አብዛኛዎቹ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት፥ ቤተ ክርስቲያን የዘመናት ሁሉ የቅዱሳን ስብስብ ናት የሚሉ ሲሆን፥ አንዳንዶች ከዚህም ሰፋ አድርገው ደኅንነትን ሳያገኙ እንኳ በውጫዊ መልክ የቤተ ክርስቲያን አካላት የሆኑትን ይጨምራል የሚል አሳብ አላቸው። ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት ይህን አሳብ ከተቀበልን፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከዚህ አሳብ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ይሆናል። የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ አገልግሎት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለማይገኝና፥ ስለ ሺሁ ዓመት መንግሥት በተነገረው ትንቢት ውስጥም ስለሌለ፥ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በተለይ ከጰንጠቆስጤ ዕለት ጀምሮ ጻድቃን ከሙታን ተነሥተው ሕያው የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እስከምትነጠቅበት ዕለት ድረስ ባለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን የሚፈጸም ነው። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ያሉ ቅዱሳንን ብቻ የምታካትት ናት ካልን፥ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ አማኞችን ሁሉ ወደ ክርስቶስ አካል የማጥመቁ ሥራ የተለየ ትርጉም ያለው ይሆናል። ይህ ምልክት በዚህ ዘመን ያሉ ቅዱሳን የሚታወቁበት ልዩ መለያና፥ ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር

የሚኖራቸውን የጠበቀ ኅብረት ምሥጢር የሚገልጥ ይሆናል። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ትምህርት መረዳት፥ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ልዩ መለያ እንደሆነ ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት።

ለውዥንብሩ መፈጠር ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች በርካታ ናቸው። ጥምቀት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ከዳግም ልደትና ከመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ማደር ጋር ተያይዟል። እነዚህ አገልግሎቶች ከማጥመቅ አገልግሎት ጋር በተመሳሳይ ቅጽበት የሚፈጸሙ ቢሆኑም፥ በተፈጥሮአቸው ግን የተለዩ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ብዙ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር በአንድነት ቀርቧል። በተለይ እንደ ዶልመን [Dolman] ያሉ የቀድሞ ጸሐፊዎች ጥምቀትንና ሙላትን አንድ አድርገው አቅርበዋቸዋል። የዶልመን ትምህርት በጣም ጠቃሚ ቢሆንም የቃሉ አጠቃቀም ግን በጣም ተምታቷል። የአንዳንዶቹ ጸሐፊዎች ትምህርት ደግሞ በጭራሽ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ አይደለም።

ከትክክለኛው እውነት እጅግ የራቀ ሆኖ የምናገኘው ነገር፥ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ከአንዳንድ ጊዜያዊ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና ልዩ ልምምዶች ጋር በሚያያይዙ የቅድስና እና ጰንጠቆስጣዊ* [Pentecostal] እንቅስቃሴዎች በመባል በሚታወቁ ትምህርቶች ውስጥ ነው። በጥንት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታይ የነበረ የልዩ መገለጥ ተግባር እና በልሳን የመናገር ጉዳዮች ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር መምታታት የለባቸውም። እነዚህ የተለዩ አገልግሎቶች ለጻኑ ሰዎች ብቻ የተገለጡ ቢሆኑም፥ ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተለመዱ ምልክቶች ሆነው መታየት የለባቸውም። በተለይ ልንቃወመው የሚገባ ትምህርት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ደኅንነትን ተከትሎ የሚመጣ የተለየ የመቀደስ ተግባር ነው የሚለውን አሳብ ይሆናል።

1. የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት የሚመለከቱ የአመለካከት ግጭቶች በርካታና የተምታቱም ስለሆኑ፥ ይህን ርእስ የሚያጠና ማንኛውም ሰው ለቅዱሳት መጻሕፍት እጅግ ቅርብ መሆን አለበት። በተለይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ ሊሰጥ የማይችልባቸውን ግምታዊ አስተሳሰቦች ማራቅ ይገባዋል። ለዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ቅዱሳት መጻሕፍት በቂ መረጃዎችን የሚሰጡ ስለሆነ፥ ጠንቃቃ አጥኚ ይህን እውነት በትክክል ወደሚረዳበት ደረጃ ለመድረስ መጣር አለበት። በአጠቃላይ ስለ መንፈሳዊ ጥምቀት የሚናገሩ አሥራ አንድ ጥቅሶች አዲስ ኪዳን ውስጥ አሉ (ማቴ. 3፡11፤ ማር. 1፡8፤ ሉቃስ 3፡16፤ ዮሐ. 1፡33፤ ሐዋ. 1፡5፤ 11፡16፤ ሮሜ 6፡1-4፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ ገላ. 3፡27፤ ኤፌ. 4፡5፤ ቈላ. 2፡12)።

---

* በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የአሳታሚውን መግለጫ ይመልከቱ።

ከጳንጠቆስጤ ዕለት በፊት የተነገሩት ማመሳከሪያ ጥቅሶች በሙሉ ትንቢታዊ ናቸው። ከዚያ በኋላ የተነገሩት ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነባሪ እውነት መሆኑን ይናገራሉ። ሌሎች ምንባቦችን ለመተርጐም እንደ መሠረት ሊወሰድ የሚገባው ዓቢይ ክፍል 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥13 ነው።

## 2. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም ነው

*ደኅንነትና ጥምቀት የሚነጣጠሉ አይደሉም።* ብዙ ጊዜ የሚነገር አንድ የተሳሳተ አስተሳሰብ፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ የተሰጠ ልዩ አገልግሎት ነው የሚለው ነው። በተቃራኒው ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን በዳነ ወቅት ወዲያው በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቅ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ስለዚህ፥ ደኅንነትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አብረው የሚሄዱ ናቸው። እንደውም ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ መዳን የማይቻል ነው። ይህ አሳብ መሠረታዊው የእምነት ትምህርት በሚገኝበት ጥቅስ በሚገባ ተገልጧል። "አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎች ብንሆንም ባሪያዎችም ብንሆን፥ ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል" (1ኛ ቆሮ. 12፥13)።

*ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል።* ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እንደተጠመቁና ከክርስቶስ አካልም ጋር የተዋሐዱት በዚህ ምክንያት እንደሆነ ከዚህ ክፍል እናረጋግጣለን። ይህ ክፍል የሚገኘው በበርካታ ኃጢአት፥ በክፍፍልና ከእምነት ፈቀቅ በማለት ምክንያት የጥፋተኝነት ስሜት ለሚሰማት ቤተ ክርስቲያን በተጻፈ መልእክት ውስጥ መሆኑን ማስተዋል ይጠቅማል። ይሁን እንጂ በዚህ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ሰዎች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው እንደነበር ጳውሎስ ያሳስባቸው ነበር። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሕሊና ወቀሳ ነጻ ለሆኑ ብቻ የተሰጠ ወይም ከጥረት የተነሣ የሚደረስበት ከፍተኛና ልዩ ግብ አይደለም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ሁሉ የሚሠራው ሁለንተናዊ አገልግሎት እንደሆነ ነው ቃሉ የሚያስረግጠው።

*አንዲት ጥምቀት።* ይህ አሳብ በኤፌሶን 4፥5 ተደግፏል፦ "አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት።" ይህ ክፍል በርከት ባሉ ልዩ ልዩ መንገዶች የሚተረጎም ቢሆንም፥ ለአማኞች ሁሉ የጋራ የሆነ ነገር መሆኑ ግልጥ ነው። ሁሉም አንድ ጌታ፥ አንድ ሃይማኖት ወይም አስፈላጊ የሆነ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትና አንዲት ጥምቀት አላቸው። አሳቡ የሚናገረው ስለ ውኃ ጥምቀት እንዳልሆነ ግልጥ ነው። የውኃ ጥምቀት

በተለያዩ ክርስቲያኖች የተለያየ አተረጓጎም ተሰጥቶት የሚፈጸምና በጥቂቶች ዘንድ ደግሞ በጭራሽ የማይፈጸም ሥርዓት ነው። በዚህ ስፍራ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አምሳያ ሳይሆን እውነታ ነው የምናየው። ክፍሉ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም እንደሆነ ለማረጋገጥ ያገለግላል። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚናገሩ ሌሎች ክፍሎች በሙሉ ከዚህ አመለካከት ጋር የሚስማሙ ናቸው።

*በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅን እንሻ ዘንድ የተሰጠ ማበረታቻ አይገኝም።* ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ይፈልጉ ዘንድ የተነገረ አንዳችም ነገር የለም። ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ እናዘጋጅ ዘንድ የተነገሩ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም፥ ይህ ዝግጅት ጥምቀት ተብሎ አልተጠራም። በየትኛዎቹም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከደኅንነት ቀጥሎ የተፈጸመ ነገር ተደርጎ አልቀረበም። ይልቁንም ከደኅንነት ሊነጠል የማይቻል ነገር እንደሆነ ታይቷል። በዚህም ዘመን ያለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መዳን አይቻልም። ከዚህ አንጻር ሲታይ፥ በሁሉም አቅጣጫ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም መሆኑን በመናገር ማጠቃለል እንችላለን።

## 3. ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ

*የአካል አንድነት።* ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ዋና ዋና ውጤቶች አንዱ የአማኞች በክርስቶስ አካል ውስጥ አንድ መሆን ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 መሠረት የአማኞች ጥምቀት፥ "አንድ አካል" ለመሆን ነው። ቤተ ክርስቲያንን በሰው አካል ሥዕላዊ መግለጫነት በማቅረብ እያንዳንዱ ክርስቲያን ወደዚህች ሕያው ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት እንደሚቀላቀል በግልጥ ቀርቧል። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሕያው የሆነውን የቤተ ክርስቲያን አንድነት የመመሥረትና ሰዎችን ወደዚህ አንድነት ለመጨመር የሚከናወን አገልግሎት ነው።

*የክርስቶስ አካል፥ እጅግ ጠቃሚ የእምነት ትምህርት።* የቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስ አካልነት የሚገልጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እጅግ ብዙ ናቸው። ከእነዚህም አብዛኛዎቹ የዚህን አካል አመሠራረት እና ዕድገት ያሳያሉ (ሐዋ. 2፡47፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡15፤ 12፡12-14፤ ኤፌ. 2፡16፤ 4፡4-5፥ 16፤ 5፡30-32፤ ቈላ. 1፡24፤ 2፡19)። ክርስቶስ የዚህ አካሉ እራስ እንደሆነ ተገልጧል (1ኛ ቆሮ. 11፡3፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 5፡23-24፤ ቈላ. 1፡18)። ክርስቶስ አካሉን እንደሚመግብ የሚናገሩም ቢያንስ ሦስት ጥቅሶች ይገኛሉ (ኤፌ. 5፡29፤ ፊልጵ. 4፡13፤ ቈላ. 2፡19)። የክርስቶስ አካል ማለት የቤተ ክርስቲያን መቀደስ ጉዳይ በኤፌሶን

5፡25-27 የተገለጠ ሲሆን፥ በሌሎች ክፍሎችም በተዘዋዋሪ ተመልክቷል። ክርስቶስ ለአካሉ ስላበረከታቸው ስጦታዎች የሚናገሩ በርካታ ጥቅሶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ (ሮሜ 12፡3-8፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡27-28፤ ኤፌ. 4፡7-16)። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል መሆኗን የሚናገረው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የአዲስ ኪዳን ዓቢይ ክፍል ነው።

*በአካሉ ውስጥ ያለ ስፍራ።* የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሥራ የአካሉን የተለያዩ ብልቶች አንድነት ያረጋግጣል። የዘር እና የባሕልን ልዩነት ሳይመለከት እውነተኛ አማኞች በሙሉ በክርስቶስ ሕያው አካል ውስጥ አንድ ሆነዋል። ይህ በአያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተረጋገጠ ሲሆን፥ መሠረቱም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። አንድነቱ ግለሰቦች በብዙሃን የሚዋጡበት ዓይነት ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ተግባር እያንዳንዱ አማኝ በክርስቶስ አካል ውስጥ የራሱ የሆነ ልዩ ስፍራ የሚይዝበት ነው። እያንዳንዱ አማኝ ለአጠቃላዩ አካል ሙላት እና ፍጹምነት አስፈላጊ ነው። አካሉ "እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ" በጅማት እንደተጋጠመ ነው (ኤፌ. 4፡16)። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ዋና መሠረታዊ ትምህርት በሚገባ መረዳት የቤተ ክርስቲያንን ጅማሬ ለመረዳት ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን አሠራርና ሉዓላዊ ዝግጅትም ለመገንዘብ አስፈላጊ ነው።

## 4. ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ

*አዲስ ስፍራ።* የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማኙን ወደ ክርስቶስ አካል መጨመር ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቶስ ውስጥ የሚያኖረውም ነው። ይህን እውነት ክርስቶስ አስቀድሞ ይጠባበቅ እንደነበር ከተናገረው ቃል እንመለከታለን። "እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ" (ዮሐ. 14፡20)። "እናንተም በእኔ እንዳላችሁ" የሚለው ግንኙነት የሚፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ክርስቲያኖች የሚይዙት የዚህ ስፍራ ዋናነት ብዙ መጋነንን የማይሻ፥ ራሱን በራሱ የሚገልጥና እጅግ ጠቃሚ ጉዳይ ነው። ማንኛውም ግለሰብ ከመዳኑ በፊት በአዳም ውስጥ ሆኖ የአዳምን ተፈጥሮ፥ ኃጢአት፥ እንዲሁም የመጨረሻ ዕጣ ይካፈል ነበር። በደኅንነት ደግሞ በአዳም ከነበረበት ስፍራ ተወስዶ ክርስቶስ ውስጥ እንዲሆን ተደርጓል። የደኅንነቱ ዝርዝር ሁኔታዎች ሁሉ ከዚህ አዲስ ከተሰጠ ስፍራ የሚመነጩ ናቸው። መጽደቁ፥ መቀደሱ፥ ነጻ መውጣቱ፥ ወደ እግዚአብሔር ለመግባት ያገኘው ዕድል፥ ርስቱ፥ እንዲሁም መከበሩ እውንና የሚቻል የሆነው አማኙ በክርስቶስ ባገኘው ስፍራ ምክንያት ነው። የዚህን መሠረታዊ

የእምነት ትምህርት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በሚገባ ያለመረዳት፥ ሐሰተኛ ትምህርቶች እንዲነሡና አያሌ ክርስቲያኖችም ደኅንነታቸው ባስገኘላቸው የደስታ ልምምድ ውስጥ እንዳይኖሩ አድርጓቸዋል።

*ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን (ሮሜ 6፡1-5)።* "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን* ሁላችን" የሚለው አባባል በመሠረቱ የሚያሳየው ከክርስቶስ ጋር መዋሃድን ነው። አማኙ በጽድቁ፥ በሞቱ፥ በትንሣኤውና በክብሩ ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናል። እነዚህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በአእምሮአችን ይዘን ከላይ የተጠቀሱትን የሮሜ ጥቅሶች ስናጠና፥ ከክርስቶስ የሞትና የትንሣኤ ታላቅ ተግባር ጋር አማኙ አንድ መሆኑ ግልጥ ይሆናል። "ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ፥ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን" (ሮሜ 6፡3-5)። ከክርስቶስ ጋር አንድ የመሆን የከበረ እውነት፥ ለአማኙ የውኃ ጥምቀት ከመሰጠቱ በፊት የሚያድን እምነት ባሳየበት ቅጽበት የተፈጸመ እውነትና የሚታይ ሐቅ ነው። አማኙ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት ከክርስቶስ ጋር በተገናኘ ጊዜ፥ ከክርስቶስ የመስቀል ሞትና የድል ትንሣኤ ጋር አንድ ይሆናል። የውኃ ጥምቀት አምሳያነት የደኅንነት ሳይሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። የመንፈስ ጥምቀትም ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንን ያከናውናል። የሚያሳዝነው፥ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ከቅዱሳት ምሥጢራት በአንዱ ላይ (በውኃ ጥምቀት ላይ) ስታተኩር በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ላይ የሚገባውን ትኩረት ሳትሰጥ ማለፏ ነው። የውኃ ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አምሳያ ብቻ መሆኑን ልትረዳ ይገባ ነበር። እነዚህ ቅዱሳት ምሥጢራት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስን አካል አንድነትና ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንን በጥሩ ሁኔታ መግለጥ ሲገባቸው፥ ከሰው አሠራር የተነሣ ከፋፋይ ሆኑ። አንድ አማኝ በክርስቶስ ውስጥ የመሆኑ እውነት፥ ይህ ስፍራው ከሚያስገኝለት በረከት ሁሉ ጋር ሲታይ፥ ምንኛ ጠቃሚና የከበረ ነገር ነው?

ከሮሜ 6፡3-4 ጋር ተጓዳኝ አሳብ ያለው ሌላ ክፍል ቈላስይስ 2፡12 ነው:- "... በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።" በቈላስይስ መልእክት የምናገኘው መገለጥ፥ በሮሜ

* የግሪክኛው ጥቅስ ቃል በቃል ሲተረጎም "ክርስቶስ *ውስጥ* ተጠመቅን" የሚል አሳብ እንደያዘ እንረዳለን።

ያለውን የተሟላ የሚያደርግና ከክርስቶስ ጋር የተቀበርን መሆናችንን የሚያመለክት ነው። የመቀበር ጉዳይ በመሠረታዊው ወንጌል ውስጥም የታከለ ነገር ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡4)። ፍጻሜን የሚያመለክት መሆኑ ነው ጠቃሚነቱ። የክርስቶስ መቀበር የሞቱን እርግጠኛነትና የመሥዋዕትነቱን ፍጻሜ በግልጥ ያሳያል። አማኝ ከክርስቶስ ጋር በመቀበር ለኃጢአት ሞተ፥ በትንሣኤ ደግሞ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆነ።

*አዲስ የሕይወት አንድነት።* ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ ለሱ መለየት ብቻ ሳይሆን፥ ከርሱ ጋር አንድ መሆንም ነው። አማኝ በዳግም ልደት የዘላለም ሕይወት ተካፋይ ይሆናል። በመለኮታዊ ፈቃድ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ በዕለት ተዕለት ሕይወቱም ተባብሯል። ይህ አዲስ የሕይወት አንድነት አካሉና ራሱ (አማኙና ክርስቶስ) የሚካፈሉት ሕያው አንድነት ነው። ከዚህ መሠረተ አሳብ አስደናቂ እውነቶች ይመነጫሉ። እነርሱም፥ ኅብረት፥ ፍሬ ማፍራት፥ ለድል ብርታትን ማግኘት ሲሆኑ፥ እነዚህ ከአካሉ ራስ ጋር የአንድነት መሠረት ናቸው። በክርስቶስ መጠመቅን የሚያመለክቱ ሁለት ፅንሰ-አሳቦች (ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንና የአዲስ ሕይወት አንድነት) የማይነጣጠሉና በውህደት ወደ አንድነት የሚያመሩ ናቸው። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር የተባለ የሥነ-መለኮት ምሁር እንደጻፈው፡-

> "ስለ ሉል ጠለቅ ያለ ትርጉም ብንሰጥ፥ የአንድን ነገር ዙሪያ በሁሉም አቅጣጫ የሚከብና እንዲያውም ያን ነገር ዘልቆ የሚገባ ነገርን ማመልከታችን ነው። በአንድ ነገር ክብ (ክልል) ውስጥ መሆን፥ በዚያ ነገርና ከእሱም የሚገኘውን ነገር ሁሉ መካፈል ማለት ነው። በዚህ መሠረት ስናየው፥ ወፍ በአየር ላይ ነች፥ አየርም በእርሷ ውስጥ አለ፤ ዓሣ በውኃ ውስጥ ይኖራል፥ ውኃም በዓሣ ውስጥ አለ፤ ብረት በእሳት ውስጥ ይደረጋል፥ እሳትም በብረት ውስጥ ይገኛል። በመንፈሳዊ ረገድም ክርስቶስ በአማኙ ዙሪያው ነው። እርሱ አማኙን ያካብበዋል፥ ይከብበዋል፥ በውስጡ ያደርገዋል፥ ያድርበታልም። አማኙ በክርስቶስ ውስጥ፥ ክርስቶስም በአማኙ ውስጥ ነው። የወይን ቅርንጫፍ፥ የወይን ግንድ፥ አንድ ብልትም የአካል ክፍል የመሆኑን ያህል፥ አማኙም በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት የክርስቶስ ሕያው አካል ይሆናል። እግዚአብሔር አብ አማኙን ከክርስቶስ ጋር ባለው አንድነት ምክንያት በርሱ ውስጥ ብቻ ያየዋል። ወይም የልጁ ሕያው ክፍል አድርጐ ይመለከተዋል። ስለዚህ ልጁን የሚወደውን ያህል ይወደዋል" (ኤፌ. 1፡6፤ ዮሐ. 17፡23)።

## 5. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በዚህ ስፍረ-ዘመን ብቻ ነው

*የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለስፍረ-ዘመን ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው።* አብዛኞዎቹ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አስፈላጊነት አልተገነዘቡም። ይህ የሆነው በብዙ ምክንያት ነው። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለው ልዩ ዓላማ ተገቢው ስፍራ አልተሰጠውም። ተነጻጻሪ የሆኑት ሕግ፥ ጸጋና የእግዚአብሔር መንግሥት ብዙውን ጊዜ ይምታታሉ። መንፈስ ቅዱስ በማጥመቅ ውስጥ ያለውን ሥራ በሚገባ መረዳት እነዚህን ስሕተቶች ለማረም በጣም ይረዳል። ይህ በዚህ ስፍረ-ዘመን ብቻ የሚገኝ አንደኛው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ወይም ወደፊት የሚኖሩ ናቸው። ስለዚህ የማጥመቅ ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው። የአሁኑ ስፍረ-ዘመን የተጀመረው የማጥመቅ ሥራ በተጀመረበት በጰንጠቆስጤ ዕለት ነበር። ወደፊትም ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የመጨረሻ ሰዎችን ትቀበላለች። ከዚያ በኋላ ክርስቶስ ወደ ራሱ ሊቀበላት ይመጣል። ይህ እውነት በሐዋርያት ሥራ ምስክርነት ግልጥ ሆኗል።

*በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች።* ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚናገሩና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁለት ብቻ ሲሆኑ፥ የሚደጋገፉ ናቸው (ሐዋ. 1፡5፤ 11፡16)። በሐዋርያት ሥራ 1፡5 ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በተናገረው የመሰናበቻ ቃል፥ "ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" አለ። በዚህ ቃል ሁለት አስፈላጊ እውነቶች ተጠቅሰዋል። 1. እስከዚያ ጊዜ ድረስ መንፈስ ቅዱስ አላጠመቃቸውም ነበር። 2. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በቅርቡ ሊቀበሉ ነው። "ከጥቂት ቀናት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እስኪጠመቁ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ" ተነገራቸው (ሐዋ. 1፡4)። በዚህ ትንቢት የተመለከተው ጉዳይ በጰንጠቆስጤ ዕለት የተፈጸመ መሆኑ የሚያሳስት አይደለም። ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር ባይያያዝ እንኳ የመመስከር ኃይል የተሰጠው በጰንጠቆስጤ ዕለት ነው። ደቀ መዛሙርቱም ከእንግዲህ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለመጠበቅ በኢየሩሳሌም መቆየት እንደማያስፈልጋቸው ተረድተው በሐዋርያት ሥራ 1፡8 በተጠቀሰው እቅድ መሠረት የክርስቶስን ሥራ ወዲያውኑ ጀመሩ። በሐዋርያት ሥራ 2፡4 መሠረትም በዚሁ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። ይህ ሥራ በዘመኑ ለነበሩና ለዳኑ ሰዎች ብቻ የተሰጠ በመሆኑ የዳኑ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ (1ኛ ቆሮ. 12፡13)። አማኞች የተጠመቁት አስፈላጊ የሆኑ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በነርሱ በጀመሩበት ቅጽበት መሆኑን እንረዳለን።

በሐዋርያት ሥራ 11፡16 የሚገኘው ሁለተኛ ክፍል በሐዋርያት ሥራ 1፡5 ያለውን ምስክርነት የሚያረጋግጥ ነው። ጴጥሮስ ስለ ቆርኔሌዎስ መዳን በሚጠቅስበት ጊዜ፥ "ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ደግሞ በመጀመሪያ እንደወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው። ዮሐንስ በውኃ አጠመቀ፥ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የጌታ ቃል ትዝ አለኝ" አለ (ሐዋ. 11፡15-17)። ጴጥሮስ በዚህ ንግግሩ በሐዋርያት ሥራ 1፡5 የተጻፈው ቃል "በመጀመሪያ" እንደተፈጸመና ይህም የጰንጠቆስጤ ዕለት ልምምድ እንደሆነ በማያጠራጥር አኳኋን ገልጦታል። ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቃቸው ማረጋገጫ፥ በልሳን መናገራቸው እንደነበር ተገልጧል (ሐዋ. 10፡46)። ብዙ ሰዎች ከዚህ በመነሣት በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በልሳን በመናገር መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለ አድርገው ከተሳሳተ ግንዛቤ እና ውሳኔ ደርሰዋል።

*የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በልሳን ከመናገር ጋር ያለው ግንኙነት።* በጰንጠቆስጤ ዕለት ብዙ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በአንድ ላይ ተጀምረዋል። በቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ውስጥ አዲስ የተለወጡ ሰዎች፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት የተለወጡት ሰዎች፥ ሐዋርያትን ጨምሮ ዳግም እንደተወለዱ፥ መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባቸው፥ በመንፈስ ቅዱስ እንደታተሙና እንደተሞሉ እንረዳለን። በቆርኔሌዎስ ቤትና በጰንጠቆስጤ ዕለት እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተከናወኑት በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቅ ጋር በአንድ ቅፅበት ነው። ማንኛውም የደኅንነት ሥራ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ መፈጸሙ ከተገለጠ፥ በሁለንተናዊ መልኩ ሌሎችም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በሥራ ላይ ውለዋል ማለት ነው። በዚህ መሠረት ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖረውም፥ ማንኛውም የደኅንነት ውጫዊ ምልክት፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማረጋገጫ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል። የዚህ ነገር መኖር፥ ማለትም ክርስቲያኖች ብቻ በልሳን መናገራቸው፥ በቆርኔሌዎስ ቤተሰቦች ላይ መታየቱ፥ ለቆርኔሌዎስ ቤተሰብ መዳንና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃቸው ለጴጥሮስ በቂ ማስረጃ ሆኖት ነበር። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በልሳን መናገር መኖሩ፥ ለወንጌል እውነት ጠንካራ መተማመኛ በሚያስፈልግበት ጊዜ የተከናወነ በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ነበር። ስለዚህ ይህ ነገር በጰንጠቆስጤ ዕለት፥ ወንጌል እንደገና ለዓለም ሁሉ በቀረበበትና ደኅንነት በታየበት የቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ውስጥ በግልጥ ቀርቧል። በልሳን መናገር ለሐዋርያት ዘመን ከተሰጡትና ጊዜያዊ ከነበሩት መንፈሳዊ ስጦታዎች አንዱ ሆኗል። በልሳን መናገር መንፈስ ቅዱስ ለዳነ ሰው ከሚሰጠው ከማንኛውም አገልግሎት ይልቅ፥ አማኙን ከመሙላት አገልግሎት ጋር የሚገናኝ ነው። በልሳን መናገር ከዳግም ልደትና ከቅድስና

ጋር ግንኙነት እንደሌለው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቅ ጋርም ምንም ግንኙነት የለውም። ሁሉም ለዳነ ሰው በሚሆን አገልግሎት ክልል የሚታዩ ነበሩ።

*የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በደኅንነት እምነት ጊዜ የሚፈጸም ነው።* ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከሚናገሩና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከምናገኛቸው ሁለት ክፍሎች እንደምንረዳው፥ ይህ ነገር ከጰንጠቆስጤ ዕለት በፊት እንዳልተከናወነና አማኞች ሁሉ በክርስቶስ ባመኑበት ወቅት ከሌሎች የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ጋር የሚሰጣቸው መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን። አንዳንድ ጸሐፊዎች እንደሚያመለክቱት፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአንዴና ለመጨረሻ በጰንጠቆስጤ ዕለት የሆነ አይደለም። ለምሳሌ ጄምስ ግሬይ [James Gray] "ስለ መንፈስ ቅዱስ የተደረገ ቀላል ንግግር" በሚል ርእስ ዶልመን በጻፈው ጽሑፍ መግቢያ ላይ፥ ሲናገር፦ "በእኔ አመለካከት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በጰንጠቆስጤ ዕለት በደቀ መዛሙርት ላይ የመጣው (ሐዋ. 2) ለአንዴና ለመጨረሻ ነው። አማኞች ወደ ክርስቶስ በእምነት በሚመጡበት ቅጽበት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን አይለማመዱም፤ ነገር ግን የጰንጠቆስጤ ዕለት ክንውን ተካፋዮች ይሆናሉ።"

የክርስቶስ ሥራ ለአንዴና ለመጨረሻ በመስቀል ላይ ተፈጽሟል። ይህ መሥዋዕትነት ለአንዴና ለመጨረሻ የተከናወነ ቢሆንም፥ በእያንዳንዱ ሰው ተግባራዊ የሚሆነው ደኅንነትን በሚቀበልበት ጊዜ ይሆናል። በጥምቀት ጊዜ የሚሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ግን የተለየ ነው። ይህ የአንዲት ነፍስ በአንድ ወቅት ከክርስቶስ አካል ጋር የመገናኘቷ ክንውን ነው። ሰዎች ከመዳናቸው በፊት እንኳ ክርስቶስ ለሁሉም ሞቷል ለማለት ብንችልም፥ እያንዳንዱ ሰው የመዳን ፍላጎትና እምነት ከማሳየቱ በፊት፥ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቀ ለማለት አንችልም።

*የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አይደጋገምም።* በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚፈጸመው ለአንዴና ለመጨረሻ ነው። ተከታታይ ሂደትም የለውም። ስለዚህ ሊደጋገምም ሆነ ሊሻሻል ጨርሶ አይችልም። በሚፈጸምበት ጊዜ ያለው ስፍራና አንድነት ጥምቀቱ ከተፈጸመበት ወቅት ጀምሮ ፍጹም ነው። በአሁኑ ዘመን ፊቱን በእምነት ወደ ክርስቶስ የመለሰ ሰው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል። ስለዚህ ጉዳይ የሚናገር አንድም የብሉይ ኪዳን ጥቅስ የለም። በወንጌላት ውስጥ የተጠቀሱ ነገሮችም በሙሉ ትንቢታዊ ናቸው። ደግሞም ስለ ወደፊቱ መንግሥት በተነገሩ ትንቢቶች ውስጥ ሁሉ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተነገረ አንዳችም ነገር የለም። ስለዚህ ይህ ነገር በዚህ ስፍረ-ዘመን

ብቻ የሆነ፥ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ የተለየ፥ እሷ የተመሠረተችበትና ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም የተዋሐደችበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን እናያለን።

## 6. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሕዋሳዊ ልምምድ አይደለም

*ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር የተያያዘ መንፈሳዊ ልምምድ።* የመንፈስ ቅዱስን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በሚመለከት የሚደረግ ጥንቃቄ የተሞላበት ጥናት የሚያስረዳን፥ የሚኖረው ልምምድ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት መሆኑን ብቻ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ማለት፥ ዳግም ልደት፥ በሰው ውስጥ ማደር፥ ማተም፥ እና ማጥመቅ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ተከትለውት ለሚመጡ ልምምዶች መሠረት ሲሆኑ፤ ሁሉም በራሳቸው የሚከናወኑ እንጂ የሚሰሙን ነገሮች አይደሉም። የዳግም ልደትን ሥርዓታዊ ክንውን ሰው እንደማይሰማው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም እንዲሁ ነው። የሚከተሉት ማጠቃለያዎች በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጉዳይ ላይ በቂ ማብራሪያ ይሰጣሉ።

*የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአማኞች ሁሉ የሚሆን ነው።* አማኞች ሁሉ ደኅንነትን በተቀበሉበት ቅፅበት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቁ ቀደም ብሎ ተመልክተናል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የመንፈሳዊ ብስለት፥ ራስን አሳልፎ የመስጠት ወይም በመሠረታዊ ትምህርት የመገንባት ጉዳይ አይደለም። እያንዳንዱ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቁን እስኪረዳ ድረስ የማያስተውለው ቢሆንም፥ እምነቱን በክርስቶስ ባደረገ ወቅት በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ መሆኑ ግን ሐቅ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያላቸው እውቀት ጥቂት መሆኑ ስውር አይደለም። ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነትና በእርሱ ውስጥ የሚኖረን ስፍራ በሚገባ የምንገነዘበው፥ ልባችንን ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥተን ከርሱ ስንማር ነው። ሰው ከመዳኑ የተነሣ በሕይወቱ የሚያየው ለውጥ በደኅንነቱ ላይ ዋስትና እንዲሰማው ቢያደርግም፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግን የሚሰማ ነገር አይደለም።

*የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የኅብረትን እውነት ያመለክታል።* የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መንፈሳዊ ኅብረትን የሚያመለክት ስለሆነ ለአማኙ የሚሰማ አይደለም። "በክርስቶስ" ያለን ስፍራ ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ከመስጠታችን የተነሣ ለሚሰሙን ስሜቶች መሠረት ቢሆንም፥ ከጌታ ጋር ያለን ሕብረት በራሱ ግን ስሜትን የሚፈጥር ነገር አይደለም። አማኞች ሁሉ ተመሳሳይ የሆነ ግንኙነት ከጌታ ጋር ቢኖራቸውም፥ ብዙዎች ያላቸው መንፈሳዊ ልምምድ ውሱን ነው። በእያንዳንዱ ግለሰብ ሕይወት

ያለው እድገት ይለያይ እንጂ ሁሉም በክርስቶስ ያላቸው ሕብረት ግን አንድ ነው። በተለይ በክርስቶስ ውስጥ እንድንሆን ያደረገን የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ተግባር የስሜት ጉዳይ አይደለም። ወደ ነፍሳችን የገባው አዲሱ ሕይወት በደጎነት የደስታ ጐርፍ ሊያጥለቀልቀን ይችላል። ይቅር መባላችንንና መጽደቃችንን ማወቃችን በውጥረት ውስጥ የነበረውን አእምሮአችንን ሊያሳርፈው ይችላል። “በክርስቶስ ውስጥ” እንድንሆን የሚያደርገን ሂደት (ክንውን) ግን በራሱ የሚሰማን ነገር አይደለም።

*የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ።* የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በባሕርይው እንደ ሂደት ተደርጎ መቆጠርን አይፈቅድም። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የእግዚአብሔር ሥራ እንደመሆኑ መጠን ቅጽበታዊ ነው። ስለዚህ በቅጽበታዊ ተግባር የልምምድ ሂደት ሊኖር አይችልም። ይህን ጥምቀት በሚመለከት ረገድ የሽግግር ወቅት የለም። አማኝ “በአዳም” ከነበረበት “በክርስቶስ” ወዳለው ስፍራ ወዲያውኑ ይመጣል። ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኋላ ምንም ዓይነት ስሜት ይሰማን፥ የጥምቀቱ ክንውን ግን በስሜታችን የሚሰማን አይደለም።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የእግዚአብሔር ቅጽበታዊ ሥራ መሆኑን መገንዘብ፥ ይህን መሠረታዊ ትምህርት ካልተለመደና ከተሳሳተ አመለካከት ነጻ በመሆን የምናቀርበው ያደርገዋል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በመሠረቱ እግዚአብሔር አንድን ነፍስ የራሱ የሚያደርግበት ሉዓላዊ ሥራ ነው።

## 7. ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው

መንፈስ ቅዱስ የጥምቀት ሥራ ፈጻሚ መሆኑን መሠረታዊውን የእምነት ትምህርት ያጠኑ ሰዎች ሁሉ አስቀድመው ተገንዝበውታል። ይሁን እንጂ ይህን አሳብ በሚመለከት አልፎ አልፎ የሚሰነዘር ተቃውሞ አለ። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚናገሩ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጥናት ‘ኧን’ [‘en’] የሚለው የግሪኩ መስተዋድድ ጥቅም ላይ እንደዋለ ያሳየናል። ይህ ‘ኧን’ ተብሎ የሚጠራው የግሪክ መስተዋድድ በሁለት መንገድ ይተረጎማል። አንዱ መሣሪያን የሚያመለክት ሲሆን፥ በአማርኛ በ‘በ’ ይተረጎማል። ሁለተኛው ደግሞ ቦታን የሚያመለክት ስለሆነ በአማርኛ “በ. . .ውስጥ” በሚል ይተረጎማል። የመጀመሪያው አተረጓጎም የምንጠመቀው በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ይገልጣል። በሁለተኛው አተረጓጎም ደግሞ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ እንደሚያጠምቀን ያመለክታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ የምናገኘው የመስተዋድድ አጠቃቀም፥ በመጀመሪያ ያመለከትነው ስለሆነ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን ትርጉም ወስደናል (ማቴ. 12፡24፤ ሉቃስ 22፡49፤ ዕብ. 11፡37፤

ራእይ 2፡16፤ 6፡8፤ 13፡10ን ይመልከቱ)። ፈሪሳውያን "ይህ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም" (ማቴ. 12፡24)፥ ሲሉ ተአምሩን የሠራው "የአጋንንት አለቃ" ነው ማለታቸው እንደሆነ ግልጥ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ደቀ መዛሙርት፥ "ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን?" (ሉቃስ 22፡49) ብለው ሲጠይቁ፥ መሣሪያው በሰው እጅ የሚያዝ ቢሆንም የታሰበው ነገር የሚፈጸምበት መሣሪያ ሰይፍ እንደሆነ መመልከት እንችላለን። በመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ሥራ ውስጥም የመስተዋድዱ አጠቃቀም ምናልባት በተመሳሳይ መንገድ በመሣሪያነት ሳይሆን አይቀርም። የሐዋርያት ሥራ 1፡5ም ሆነ የ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 አሳብ ይህ ነው።

ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ ያለው ጠቅላላ አገልግሎት የሚፈጸመው፥ በክርስቶስ ፈቃድ መሆኑ ግልጥ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ የእርሱ ወኪልና ሥራውን የሚያከናውንለት ነውና። ስለዚህ የተጠመቅነው ክርስቶስ በላከው መንፈስ ቅዱስ ነው ለማለት ይቻላል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተፈጸመው በክርስቶስ ስለሆነ፥ የተጠመቅነው በክርስቶስ እንደሆነ የሚናገሩ ክፍሎች አሳብንም በዚህ መሠረት ለመረዳት እንችላለን። ልክ የሊቀ ካህኑ አገልጋይ ጆሮ በደቀ መዝሙሩ ወይም በደቀ መዝሙሩ ሰይፍ ተቆረጠ ማለት እንደምንችል፥ በመንፈስ ቅዱስ ወይም በክርስቶስ ተጠመቅን ማለትም እንችላለን (ሉቃስ 22፡49)።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ትክክለኛ ተግባር አማኙን ወደ ክርስቶስ አካልና ወደ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ክልል ማምጣት ነው። በዚህ መሠረት በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 እንደተመለከተው፥ "እኛ ሁላችን አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።" ይህ ቃል የሚያመለክተው፥ በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ውስጥ መሳተፍን ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ ዳግም ልደት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደሆነ ሁሉ፥ ጥምቀትም የርሱ ሥራ ነው። በሥላሴ ሥራ ውስጥ ሊነጣጠል የማይችል የአሠራር አንድነት ቢኖርም፥ የዩኒተሪያኒዝም ተከታዮችን ስሕተቶች ለማስወገድ ከፈለግን በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ያለውን የእያንዳንዱን አካል ኃላፊነት በማሳየት ረገድ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

## 8. በእሳት መጠመቅ

አራቱም ወንጌላት መጥምቁ ዮሐንስ ሊመጣ ስላለው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሰጠውን ምስክርነት መዝግበዋል (ማቴ. 3፡11፤ ማር. 1፡8፤ ሉቃስ 3፡16፤ ዮሐ. 1፡33)። ሦስቱ ወንጌላት (የማቴዎስ፥

የማርቆስና የሉቃስ) መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ መምጣት የሰጠውን ምስክርነት የተወሰነ ክፍል ይናገራሉ። የወንጌላዊው ዮሐንስ ምስክርነት ደግሞ ክርስቶስ ተለይቶ የሚታወቀው በላዩ ወርዶ በነበረው መንፈስ መሆኑን ያመለክታል። ሁሉም ጸሐፊዎች ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ልዩ ባሕርይ እንዳለው የሚያሳዩ ሲሆኑ፥ ትረካዎቹ ደግሞ በባሕርያቸው ትንቢታዊ ናቸው።

በሁለት ወንጌላት ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው መግለጥ፥ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል የሚለው ነው (ማቴ. 3፡11፤ ሉቃስ 3፡16)። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች፥ ይህ ነገር በጰንጠቆስጤ ዕለት ተፈጽሟል፥ ምክንያቱም ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች እንደታዩዋቸው፥ በእያንዳንዳቸውም ላይ እንደተቀመጡባቸው ተገልጧል ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ ይህ ሁኔታ ዛሬም የምንለማመደው፥ ዳግም ጰንጠቆስጤ ነው ይላሉ። በወንጌላት ውስጥ የሚገኙትን ጥቅሶች በጥንቃቄ በምንመረምርበት ጊዜ ግን ሁለቱንም አተረጓጎሞች ውድቅ እናደርጋቸዋለን። የክፍሉቹ ዐውደ ንባብ የሚናገረው በክርስቶስ ዳግም ምጽዓትና መንግሥቱ በሚመሠረትበት ጊዜ ስለሚፈጸም ፍርድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ዘመን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንደተጀመረ ሁሉ፥ የሺህ ዓመት መንግሥትም በእሳት ጥምቀት ይጀምራል። የእሳት አጠቃቀም ብዙ ጊዜ ስለ ወደፊት ፍርድ የሚናገር ሲሆን፥ በእሳት ስለ መጠመቅ በመልእክቶች ውስጥ የተጻፈ አንዳችም ነገር የለም። ይህ በእሳት የማጥመቅ ነገር በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ማብራሪያ ያልተሰጠበት ጉዳይ ነው። ስለሆነም ጥቅሱ የሚያመለክተው ለአሁኑ ጊዜ የሚጠቅም ወይም ተግባራዊ የሚሆን ነገርን ሳይሆን፥ ክርስቶስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ በዓለም ላይ ስለሚያመጣው ፍርድ የሚናገር ነው ማለት የተሻለ አተረጓጎምና ውሳኔ ይሆናል።

## 9. በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ዘላለማዊ ውጤቶች

የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አሠራር መመርመር፥ በክርስቲያናዊ ደኅንነት ረገድ በርካታ እውነቶችና ኗሪ ውጤቶችን ይገልጥልናል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለስሜት የሚሰማ ባይሆንም፥ አስፈላጊ የሆኑና በርሱ አማካይነት እውን የሚሆኑት ክርስቲያናዊ ልምምዶች በሙሉ የሚፈልቁት ከዚህ እውነታ ነው። በዚህ የሚካተቱ እውነቶች እዚህ ላይ ተሟልተው ሊቀርቡ ባይችሉም፥ ዋና ዋና መሪ አሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው በአጭር በአጭሩ ተገልጠዋል።

*አዲስ አንድነት።* አዲስ ግንኙነት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቋሚ ውጤት ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ክርስቲያን ሕያው አባል ለመሆንና የጋራ ሕይወትን ለመካፈል ወደ ክርስቶስ አካል ይጨመራል። ይህ መሠረታዊ እውነት፥ ክርስቲያኖችን ለዘላለም አንድ የሚያደርጉ እውነቶች ሁሉ መሠረት ነው። ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ አካል መጨመር ብቻ ሳይሆን፥ ከርሱ ጋር ዘላለማዊ አንድነትም ይኖረዋል። የአንድነቱ ባሕርይ ለቅዱሳን የዘላለም ዋስትና የሚሰጥ ደጋፊ አሳብ ነው። ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በምንም አኳኋን የሚጠፋ አይደለም።

*አዲስ ስፍራ።* ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት በሚገኝ አዲስ አንድነት ወደ አዲስ ስፍራ ይገባል። ይህ አዲስ ስፍራ አብዛኛዎቹን የደኅንነት አስደናቂ እውነታዎች የያዘ ነው። ክርስቲያን ለሰይጣን ዓላማ መሣሪያ በመሆን ፋንታ፥ በክርስቶስ አካል ውስጥ በመሆን የጌታን ዓላማ የሚፈጽም ይሆናል። በክርስቶስ አካል ውስጥ ባለው አዲስ ስፍራ፥ የእግዚአብሔር ዓላማ መፈጸሚያ ይሆነው ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ ስጦታዎች ሁሉ ከርሱ ይሰጡታል። አማኝ በክርስቶስ ውስጥ አዲስ ስፍራ አለው። ክርስቲያን በአዳም ከነበረው የቀድሞ ስፍራው ወጥቶ በክርስቶስ አዲስ ስፍራ ተሰጥቶታል። ይህ አዲስ ስፍራ ቋሚ ርስት ነው። ወደ እግዚአብሔር የመቅረብና የመግባት መብት አግኝቷል፤ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ፥ ቀድሞ ሊሆን ያልቻለ፥ በዚህ ዘመን በሙላት የሚያገለግልበትን ነገር ሁሉ እንዲያገኝ ያደርገዋል። የክርስቲያን አዲስ ስፍራ እግዚአብሔርን በመፍራት ለመኖር የሚገፋፋና የሚያበረታታ፥ ኃጢአትንም ድል ለመንሳት መሠረት ነው።

1513 *አዲስ ኅብረት።* ክርስቲያን ባለው አዲስ አንድነትና በተሰጠው አዲስ ስፍራ ምክንያት፥ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወደ ብዙ አዲስ ኅብረቶች ይመጣል። ከሥላሴ ጋር ያለው ኅብረት በሙላት የሚገለጠው ወደፊት ቢሆንም፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱም በዚህ ዘመን ላለው ልምምዱ ወሰን የሌለውና አስደናቂ ነገር ነው። ሰው ደኅንነት ሲያገኝ ከዓለም ጋር የነበረው ኅብረት ይለወጣል። በዓለም የሚኖርና ለሰብአዊ መንግሥት የሚገዛ ቢሆንም፥ ከዚህ ዓለም አሠራር በእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ሊወጣ ይችላል። በዚህ አዲስ ኅብረቱ ምክንያትም የሰይጣን የጥቃት ዒላማ ይሆናል። ይህ ጥቃት ሰይጣን እግዚአብሔርንና የእርሱ የሆኑትን ሁሉ የሚዋጋበት ነው። ለዚህ ነው ክርስቲያን ይህን አዲስ ጠላት መቃወሚያና ነጻ የሚያወጣው የእግዚአብሔር ኃይል ያስፈልገዋል የሚባለው። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ አማኙ ሌሎች የኅብረት ገጽታዎች ይናገራሉ። ከተደራጀች ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ኅብረትም ይገልጣሉ። በወላጆችና በልጆች፥

በባልና ሚስት፥ በባሪያና በጌታ፥ በመሳሰሉትም መካከል መኖር ስለሚገባው ግንኙነት ይጠቅሳሉ። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ኅብረትም በተደጋጋሚ ተጽፏል። ይህ ኅብረት አማኙ ከማያምነው ጋር፥ ከኃጢአተኛ ወንድሙ ጋር፥ በእምነት ወይም በተግባር ከደከሙ ጋር ሁሉ ስላለው ኅብረትና ተግሣጽ ወይም እርማት ከሚሰጡ ወንድሞች ጋር ስላለው ግንኙነት ሁሉ የሚናገር ነው። የእግዚአብሔር የተትረፈረፈ ቸርነትና ስጦታ፥ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ክርስቲያን የተጠራበት ጸጋ በሚጠይቀው አዲስ ሕይወት እንዲኖር የሚያስችለው ነው። በአጭሩ የክርስቲያን ሕይወት ከየትኛውም አንጻር የሚለወጠው፥ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት ይሆናል። የዚህ መሠረታዊ ትምህርት አስፈላጊነት ለክርስቲያንም ሆነ ለሥነ-መለኮት ሊቃውንት ሁሉ ግልጥ ነው።

---

## ከአሳታሚው መግለጫ

የታወቀ ሰባኪና የመቶዲስት ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ጃን ዌስሊ (1703-1791) ከመጀመሪያ በክርስቶስ ማመን ካለ እምነት የላቀ፥ ማለት አማኝን በክርስትና ሕይወቱ ድል እንዲቀዳጅና በክርስቶስ ከፍ ያለን ኑሮ እንዲኖር የሚያደርገው ነገር እንዳለ አስተምሯል። ቢሆንም ዌስሊም ሆነ የእርሱ ተከታዮች ይህን እምነት በደንብ አላተኮሩበትም ነበር። ነገር ግን ይህ ትምህርት ለዛሬው "የቅድስና እንቅስቃሴ" ፅንሰ-አሳብ መነሻ ሆኗል።

"የቅድስና እንቅስቃሴ፥ በ19ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ገደማ አንዳንድ ሰዎች የአማኞች የቅድስና ሕይወት ማሽቆልቆል ጉዳይ በጣም አሳስቧቸው ነበር። ከዚህ የተነሣ ሰውን በቅድስና በመኖር ወደ ፍጹምነት ሊያደርሰው የሚችል ሁለተኛ የጸጋ ሥራ ሊኖር ይገባል ወደሚል አሳብ ላይ ተደረሰ። የዚህ እንቅስቃሴ አቀንቃኞች፥ ይህን ልምምድ ለማግኘት የሰው ጥረት አስፈላጊ እንደሆነ ያምኑ ነበር። ስለዚህም ይህን ልምምድ "የዳግመኛ በረከት" ልምምድ በማለት ይጠሩታል። ኋላም ይህ ተቀይሮ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" በመባል የሚታወቅ ሆነ። እነዚህ ሰዎች፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድ አማኝ ብስለት የተሞላበትና ምሳሌያዊ የሆነ የክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖር የሚያስፈልገውን የመንፈስ ኃይል ሁሉ እንደሚያስገኝለት ያስተምሩ ነበር።

በዚያን ወቅት ያስተምሩት እንደነበረ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን" "በመንፈስ ስጦታዎችም" ሆነ በልሳን ከመናገር ጋር በማያያዝ አልተመለከቱትም ነበር።

"ጰንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ" [Pentecostal Movement]፥ በ1901 ቻርልስ ፓርሃም [Charles Parham] በተባለ ሰው ተጀመረ። ይህ ሰው አሜሪካን አገር በካንሳስ በተለይ ቶፒካ በተባለ ስፍራ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከፍቶ ነበር። ዳግመኛ በረከት በሚለው አሳብ ላይ በልሳን መናገር ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምልክት ነው የሚለውን አሳብ ያከለው እርሱ ነው። የዚህ ሰው ተማሪዎች ይህን ትምህርት በየአካባቢያቸው አስፋፉት።

ይህ እንቅስቃሴ በ1906 በጥቁር አሜሪካዊው ሰባኪ በዊሊያም ሲሞር [William Seymour] በካሊፎርኒያ በመቀጠል "የአዙዛ ጎዳና" [Azuza Street] መንፈሳዊ መነቃቂያ በመባል በመላው አሜሪካ የታወቀ ሆነ።

ዛሬ "ጰንጠቆስጤያዊ እንቅስቃሴ"፥ "የካሪስማዊ እንቅስቃሴ" በመባል ይታወቃል። (እነዚህ ቡድኖች ከቅድስና እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ቢሆኑም በታሪካቸው ትንሽ ለየት ያሉ ናቸው።)

የዚህ ቡድን ዋና የእምነት መለያዎች፦ 1. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከደኅንነት የተለየ ክንውን ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የእግዚአብሔር ጸጋ ሁለተኛ ሥራ ሲሆን ያም "ዳግመኛ በረከት" በመባል የታወቀ ነው። 2. በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግለሰቡ መንፈስ ቅዱስን በሙላት ይቀበላል። ይህን አሳብ "የመንፈስ ቅዱስ ሙላት" በማለት ይገልጡታል። 3. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአማኝ ምስክር እንዲሆን እና ጌታን እንዲያገለግል የሚያስችለው ልዩ ክንውን ነው። 4. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሙላት ተሰጥተዋል። 5. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንደኛው መረጃ፥ አንድም ሆነ ከዛ በላይ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በአማኝ ውስጥ መታየታቸው ነው።

# 16

# የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር

## 1. የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ማደር ሁለንታዊ ነው

የጸጋ ስፍረ-ዘመን ከቀደሙት ዘመናት ሁሉ የሚለይበት አንዱ ትልቅ ነገር፥ መንፈስ ቅዱስ ዳግም በተወለዱ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የማደሩ እውነታ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር በሚሆንበት ዘመን ደግሞ፥ የዳኑ ሰዎች በሙሉ በመለኮታዊ በረከት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆኑበት ሁኔታ ግልጥ ይሆናል። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የመሆን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጠቀሜታ በዚህ ዘመን ለዳኑ ሰዎች አገልግሎቶች ሁሉ መሠረት መሆኑ ነው። መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ልብ ውስጥ ከማደሩ የተነሣ፥ የመሙላት ሥራው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሚሰጡ (ልባቸውን ባዘጋጁ) ሰዎች ውስጥ እውን ይሆናል። የእግዚአብሔር በአማኝ ውስጥ የማደር እውነታ መሠረታዊና ጠቀሜታ ያለው ትምህርት ነው። አንዳንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሕይወት መኖርን ራስን በተለየ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ከመስጠት ጋር አንዳንዶች ያያይዙታል።

ከዚህ በተቃራኒ ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ያደረበት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ በሰው የማደሩ ሐቅ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተጠቅሷል (ዮሐ. 7፡37-39፤ ሐዋ. 11፡17፤ ሮሜ 5፡5፤ 8፡9፥ 11፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡12፤ 6፡19-20፤ 12፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡5፤ ገላ. 3፡2፤ 4፡6፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡24፤ 4፡13)። በጰንጠቆስጤ ዕለት መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ በማደር ቤተ ክርስቲያንን መኖሪያው ለማድረግ መጣ። ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚያመለክቱ በርካታ ነጥቦች አሉ።

*የመንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ውስጥ አለማደር አለመዳንን ያመለክታል።* መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሁሉ ውስጥ እንደሚያድር ከሚያሳዩ ጥሩ መረጃዎች አንዱ በሮሜ 8፡9 በቀጥታ የተነገረው ቃል ነው፡- "እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም።" በክርስቶስ በራሱ የተላከውንና ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠውን ይህን መንፈስ ማግኘት ለመዳን እና

የክርስቶስ ለመሆን አስፈላጊ ነው። በዚህ መሠረት ያልዳኑ ሰዎች "መንፈስ የሌላቸው" ተብለው ተገልጠዋል (ይሁዳ 19)።

*በኃጢአታቸው የቀጠሉ ክርስቲያኖች እንኳ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች ናቸው።* በዚህ የጸጋ ስፍረ-ዘመን ክርስቲያኖች ኃጢአትን ቢያደርጉ መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ እንደሚወሰድ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ጨርሶ የለም። በተቃራኒው ሊጠቀሱ የሚገባቸው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለሆኑ ኃጢአትን እንዲክዱና እግዚአብሔርን የመፍራት ሕይወት እንዲኖሩ ተመክረዋል። "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? የራሳችሁ አይደላችሁም" (1ኛ ቆሮ. 6፡19)። መንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን በሚገባ ባልሰጡና በኃጢአት በሚኖሩ ክርስቲያኖች ውስጥ እንኳ የሚያድር መሆኑን ይህ ጥቅስ ያመለክታል ለማለት ይቻላል። በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ራስን ለመንፈስ ቅዱስ መስጠት የግድ አስፈላጊ ቢሆንም፥ የእርሱ በእውነተኛ ክርስቲያኖች ውስጥ ማደር ግን ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የማይጠይቅ ነው።

*መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው።* በብዙ ቦታ መንፈስ ቅዱስ "ስጦታ" መሆኑ ተገልጧል (ዮሐ. 7፡37-39፤ ሐዋ. 11፡17፤ ሮሜ 5፡5፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡12፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡5)። እግዚአብሔር ስጦታን የሚሰጠን ለዚያ የምንገባ ሆነን አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለጽድቃችን እንደ ሽልማት የተሰጠ ስለመሆኑ የተነገረ አንዳችም ነገር የለም። አስፈላጊው ነገር ክርስቶስን የግል አዳኝ አድርጎ መቀበል ብቻ ነው። በዚህ መሠረት ነው ስጦታው ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚሰጥ።

*ጌታ የሚጠብቅብን የሕይወት ደረጃ መለኮታዊ እርዳታን ይጠይቃል።* ለክርስቲያኖች በተጻፈ መልእክት እንደተገለጠው፥ እግዚአብሔር በአማኝ ሕይወት ከመኖሩ የተነሣ የሚታዩት ከፍተኛ የሕይወት ደረጃዎች፥ የመንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ የማደሩ ሌላ ማረጋገጫ ነው። ክርስቶስ በዮሐንስ 7፡37-39፥ "የሕይወት ውኃ ወንዝ" ከክርስቲያኖች እንደሚፈልቅ አስቀድሞ ተናግሯል። የበረከት እና የብቃት ምንጭ ከውጭ የሚመጣ ሳይሆን፥ ከክርስቲያኑ ከራሱ የሚወጣ ነው። የሐዋርያት ትምህርት የተመሠረተው በዚህ ላይ መሆኑንና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ እንደሚከናወን ክርስቶስ በተዘዋዋሪ መንገድ ተናግሯል። እነዚህ በርካታ የቅዱሳት መጻሕፍት መረጃዎች በግልጥ የሚያሳዩት፥ የመንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ የማደር በረከት፥ ልክ እንደ ዳግም ልደትና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ለአማኝ ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ነው።

## 2. አስቸጋሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

የመንፈስ ቅዱስን በሰው ውስጥ ማደር የሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በይዘቱ ቀለል ያለና ለመግለጥም የማያስቸግር ነው። ነገር ግን ትምህርቱን በአግባቡ የመረዳት ችግር የሚታይበት ስለሆነ፥ አስቸጋሪዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄ ማጥናት ይገባል። በአጠቃላይ ሲታይ እነዚህ ሰባት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በከፍተኛ ደረጃ በተሳሳተ መንገድ የሚተረጐሙ ሆነዋል (1ኛ ሳሙ. 16፡14፤ መዝ. 51፡11፤ ሉቃስ 11፡13፤ ሐዋ. 5፡32፤ 8፡14-20፤ 19፡1-6፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡20፥ 27)።

*የስፍረ-ዘመናትን ልዩነት ባለመገንዘብ የተነሣ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ምንባቦች።* የሦስቱ ምንባቦች ችግር የመጣው፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በዘመናት ሁሉ አንድ ነው ከሚለው የተሳሳተ ግምት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ከሳኦል መለየት የሚያረጋግጠው፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳን ሁሉ ውስጥ የማይኖር መሆኑን ብቻ ነው (1ኛ ሳሙ. 16፡14)። ዳዊትም ከመዝሙር 51፡11 በሚገኘው ጸሎቱ መንፈስ ቅዱስ እንዳይወሰድበት የለመነው፥ በኃጢአት ምክንያት በሳኦል ላይ እንደሆነው ይወሰድብኛል ብሎ በማሰብ ነው። የዳዊት ጸሎት፥ መንፈስ ቅዱስ አብሮት የሚኖር ስጦታ እንደሆነ ለተረጋገጠለት ክርስቲያን የሚሠራ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ለሚለምኑ ሰዎች መሆኑን ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለ የቅርብ ተከታዮቹ ለነበሩት ሰዎች ነግሯቸዋል (ሉቃስ 11፡13)። ነገር ግን በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት ደቀ መዛሙርቱ የወሰዱት እርምጃ ስለመኖሩ የተጻፈ አንዳችም ነገር የለም። በተቃራኒው ክርስቶስ ከተለያቸው በኋላ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣና እንደሚያድርባቸው ቃል ሲገባላቸው ወይም ተስፋ ሲሰጣቸው እንመለከታለን። ይህ ተስፋ የሚያሳየው ጌታ አብሯቸው በነበረበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ያላደረባቸው መሆኑን ነው። የእነዚህን ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አጠቃላይ አሳብ ስንመለከት *መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን በክርስቲያኖች ውስጥ ስለማደሩ የሚያመለክቱ እንዳልሆኑ በግልጥ ለመናገር እንችላለን።

*የሐዋርያት ሥራ 5፡32።* የሚቀጥሉት ሦስት ክፍሎች (ሐዋ. 8፡14-20፤ 19፡1-6) የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ከአዲስ ልደት ቀጥሎ የሚፈጸም ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተተርጉሟል፤ አንዳንድ ጊዜም የአማኝ ሁሉ እንዳልሆነ ሆኖ ይቀርባል። ከእነዚህ ሦስት ጥቅሶች የመጀመሪያ የሆነው የሐዋርያት ሥራ 5፡32 እንዲህ ይላል፡- "እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው።" አንዳንድ ጊዜ ይህ ቃል፥ መታዘዝ ወይም ራስን

ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ መስጠት ለመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ የሚቀርብ ይመስላል። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው "ለሚታዘዙት" የሚለው ቃል አሳብ፥ ግብረ ገብነትን ወይም የሕይወት ጥራትን ለማመልከት ሳይሆን፥ ልንታዘዘው የሚገባን ነገር በክርስቶስ ማመን እንደሆነ መግለጥ ነው። ይህ እግዚአብሔር መንፈሱን በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑ ይሰጣል፥ ወደሚል ድምደማ ያደርሳል። መታዘዝ የሚለውን ቃል ከመጀመሪያው የግሪክ ቃል አንጻር ስናየው፥ ለአንድ ባለሥልጣን ስለ መታዘዝ የሚናገር ነው። ስለዚህ ቃሉ ክርስቶስንና ሥልጣኑን መገንዘብን ይመለከታል።

*የሐዋርያት ሥራ 8፡14-20።* እላይ ከተጠቀሱት ሰባት ክፍሎች ሁሉ የሐዋርያት ሥራ 8፡14-20 በአማኞች ሁሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያድራል የሚለውን አሳብ የሚቃረን ይመስላል። በዚህ ቃል መሠረት በፊልጶስ የተጠመቁት አማኞች መንፈስ ቅዱስን አልተቀበሉም ነበር። ጴጥሮስ በመጣ ጊዜ ግን እጁን እንደጫነባቸውና መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ እናያለን። ከነዚህ ሁኔታዎች በመነሣት መንፈስ ቅዱስን መቀበል ከደኅንነት በኋላ የሚሆንና እጆችን መጫን የሚጠይቅ ነው የሚል የተሳሳተ ትርጉም እናገኛለን።

ይህ ችግር በሦስት ልዩ ልዩ መንገዶች መፍትሔ ሊገኝለት ይችላል። የመጀመሪያው፥ ምንም እንኳን የተለመደው የመንፈስ ቅዱስ መቀበል እስከ ጴጥሮስ መምጣት ድረስ መዘግየቱን ብንቀበልም፥ ይህ ድርጊት ጨርሶ እንዳልተደገመ ግልጥ ነው። የሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያ ክፍሎች ስለ ሽግግር ወቅት የሚናገሩ ናቸው። እግዚአብሔር ለዚህ ዘመን ያለው ትክክለኛ አሠራር የተገለጠው ቀስ በቀስ ነው። ለወንጌል መስፋፋት ዋና ምክንያት፥ ሐዋርያት ከጌታ የተቀበሉትን አደራ ከመፈጸማቸው ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። ያልተለመደ ከፍተኛ ኃይልና የሚያነቃቃ በረከት በፊታቸው የተገለጠበት ምክንያትም ይህ ነው። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በሙላት በአሕዛብ መካከል የተጀመረው፥ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 አሕዛብ በወንጌል አምነው መንፈስ ቅዱስ ባደረባቸው ጊዜ ነው። ከዚህ ክንውን የተነሣ፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በክርስቶስ ላይ ካለ እምነት እንጂ፥ በጴጥሮስ ማንነት ላይ እንደማይደገፍ ለጴጥሮስ በግልጥ ተነገረው። ከላይ የተነጋገርንበት መሠረታዊ አሳብ መፍትሔ፥ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ ሕይወት ውስጥ እንደሚያድር የሚናገረውን መሠረታዊ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ይደግፋል።

ሌሎች ሁለት መፍትሔዎችን በተጨማሪ ለማቅረብ ይቻላል። ሁለተኛው መፍትሔ የሚገኘው ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10

በፊት የመንፈስ ማደር ምናልባት በሐዋርያት አማካይነት አገልግሎት በተሰጣቸው አሕዛብ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን አይቀርም፤ መንፈስ ቅዱስን ወዲያው የተቀበሉት አይሁድ ብቻ ነበሩ። ቢያንስ ቢያንስ ወንጌል አዲስ በሚስፋፋባቸው ቦታዎች ሁሉ ቅድሚያ እየሰጡ በቀጥታ ያገለግሉ የነበሩት ሐዋርያት እንደነበሩ ግልጥ ነው። ሦስተኛው መፍትሔ የሚገኘው ደግሞ፥ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" የሚለው ቃል (ሐዋ. 8፡17) ትርጉም እንደ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ያለ ውጫዊ ሂደት እንጂ፥ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር አይደለም በሚለው አሳብ ውስጥ ነው። "ተቀበሉ" የሚለው ቃል በሁሉም ቦታ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገር ነው ብሎ ማመን ግን አጠራጣሪ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሁለት መፍትሔዎች ለምንባቡ በቂ መግለጫ የሚሰጡ ናቸው። በማንኛውም ጊዜ ዘግይቶ የሚፈጸም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ጨርሶ ተደግሞ አያውቅም። ስለዚህ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ውስጥ ባለው አሳብ በመመርኮዝ ለአጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን ዘመንም የተለመደ አሠራር ነው ወደሚል አሳብ መድረሱ ልናመክረው ለምንፈልገው አሳብ በቂ ዋስትና አይሰጥም።

*የሐዋርያት ሥራ 19፡1-6።* የንባቡን አጠቃላይ ይዘት ማየት፥ በጥንቃቄ ማጥናት፥ እና ጥቅሱን በትክክል መተርጎም ለዚህ ክፍል ችግር መፍትሔ ያስገኙለታል። በኤፌሶን የነበሩ ደቀ መዛሙርት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እንደነበሩና ከጸጋው ወንጌል ጋር ገና እንዳልተገናኙ ከዓውደ ንባቡ እንመለከታለን። በተጠመቁና በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ መጣ። "ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ" (ቁ. 6) የመንፈስ ቅዱስ ሕልውናም በመካከላቸው በልሳን በመናገራቸውና ትንቢት በመተንበያቸው ተገለጠ። ከታሪኩ የምንረዳው ነገር፥ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እንዳደረና እንደሞላቸው ሲሆን፥ ይህ የሚያሳየው መንፈስ ቅዱስ በእነሱ ከማደሩ የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ያስከተለ መሆኑን ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ሊያድርባቸው የመጣው ከደኅንነት ቀጥሎ እንደነበር ሆኖ ሊጠቀስ አይገባም፤ ምክንያቱም ከጳውሎስ ጉብኝት በፊት እነዚህ ሰዎች ደኅንነትን አላገኙም ነበር።

በሐዋርያት ሥራ 19፡2 ያለው፦ "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" የሚለው የጳውሎስ ጥያቄ፥ ዳግም ስለመወለዳቸው ያቀረበው የማረጋገጫ ጥያቄ እንጂ፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆኑት የተወሰኑ ክርስቲያኖች ናቸው የሚለውን ፅንሰ-አሳብ ጨርሶ የሚደግፍ አይደለም። ጥያቄው የሚያመለክተው ግን ዳግም በተወለዱ አማኞች ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚያድርባቸው መሆኑን ነው። የመንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው አለመኖር የሚያመለክተው ደኅንነት

አለማግኘታቸውን ነው። በዚህ ክፍል የተፈጸመው ነገር የሚያመለክተው፥ ክርስቲያኖች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆኑት ዳግም በተወለዱ ጊዜ ነው ከሚለው ከተለመደው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የተለየ አሳብ አለመኖሩን ነው።

*በመንፈስ ቅዱስ መቀባት።* ሌላ ተጨማሪ ችግር የምናየው በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀባት በሚናገሩት ክፍሎች ነው። አንዳንዶች ከእነዚህ ክፍሎች በመነሣት በመንፈስ ቅዱስ መቀባት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከመሆን ጋር በተነጻጻሪነት የሚቀርብ የተለየ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው ይላሉ። በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀባት ስለሚናገሩ ሰባቱም ክፍሎች (ሉቃስ 4፡18፤ ሐዋ. 4፡27፤ 10፡38፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡21፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡20፥ 27፥ ሁለት ጊዜ) በጥንቃቄ የሚደረግ ጥናት፥ መቀባት የሚለው ቃል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተያይዞ የተገለጠባቸው ክፍሎች ሁሉ፥ ድርጊቱ የመጀመሪያው የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማደር ተግባር መሆኑን ለመተርጐም የሚያስችሉ ናቸው። መቀባት የሚለው ቃል አገባብ፥ አንድ ነገር ሰው ላይ በማፍሰስ ወይም በማኖር የመደባበስን ስሜት የሚያሳይ በመሆኑና ዘይትም በመንፈስ ቅዱስ አምሳያነት በመጠቀሱ፥ ከዚህ አመለካከት ጋር የሚስማማ ያደርገዋል። የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና የመቀባት ውጤት ሲሆን፥ ስለ መቀባት የሚናገሩ ጥቅሶች በሙሉ በዚህ ስሜት የተነገሩ ናቸው።

## 3. የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማደር ልዩ ባሕርያት

መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር የሚጀምረው፥ እግዚአብሔር አዲስ ለሚድነው ነፍስ ከሚያደርገው በርካታ ክንውኖች ጋር ቢሆንም፥ በተለያዩ የእግዚአብሔር ሥራዎች መካከል ያለው ልዩነት በወጉ ሊጤን ይገባል። የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር፥ ከዳግም ልደት ጋር ተመሳሳይ አይደለም። የአማኙ አዲስ ሕይወት መለኮታዊና በባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር የተመሳሰለ ቢሆንም፥ የመለኮታዊ ሕይወት ባለቤትነትና የመለኮት ሕልውና የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ሥራና በሰው ውስጥ ማደር የተለያዩ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአንዴና ለመጨረሻ የሚሆን ሲሆን፥ ከዓለም ከመለየትና ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆን ክንውን ጋር የተያያዘ ነው። የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር የሚጀምረው፥ ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር በተመሳሳይ ሰዓት ቢሆንም፥ የሚቀጥል ጉዳይ ነው። በውጤቱ ማረጋገጥ እንደሚቻለው፥ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ መኖር፥ በመንፈስ ቅዱስ ከመታተም ጋር ፍጹም የጠበቀ ግንኙነት ያለው መሆኑን ማኅተምን በሚያካትተው የመንፈስ ቅዱስ መገኘት እናያለን።

ለመለየት በጣም የሚያስቸግረው፥ ምናልባት የመንፈስ ቅዱስን በሰው ውስጥ ማደርና ሙላትን ነው። ሁለቱ መሠረታዊ ትምህርቶች እጅግ የተዛመዱ ቢሆኑም፥ አንድ ግን አይደሉም። ሙላት አጠቃላይ ልምምድ ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ግን በራሱ ልምምድ አይደለም። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ጥቂት ቅዱሳን በቋሚነት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሳይሆኑ ለተወሰነ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል። በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላታቸው ስንናገር በአዲስ ኪዳን እንደተገለጠው በቋሚነት ባይሆንም፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆነዋል። በቤተ ክርስቲያን ዘመን አንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አይሞላም። ማደር የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር ሲሆን፥ ሙላት የሚጠቁመው ግን መንፈስ ቅዱስ የፈቃደኛ ግለሰቦችን ሕይወት የመቆጣጠር አገልግሎቱን ነው። የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር የሰው ሥራ አይደለም። ከኅብረትና ከፍሬ ጋር የተያያዘው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትና ልምምድ የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት የተነሣ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንሆን ዘንድ ባንደፋፈርም፥ በመንፈስ ቅዱስ እንሞላ ዘንድ ግን ጠበቅ ያለ ምክር ቀርቦልናል (ኤፌ. 5፡18)።

## 4. መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማደሩ አስፈላጊነት

የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የመኖሩ አስፈላጊነት ሊገመት የሚችል አይደለም ስንል ማጋነናችን አይደለም። ይህም በፍሬያማነትና በቅድስና ረገድ ያለውን መለኮታዊ ዓላማ እንዲሁም ጸጋ የሚያረጋግጥ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ከፊታችን ያለውን በረከት የማግኘታችን "መያዣ" ነው (2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ 5፡5፤ ኤፌ. 1፡14)። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሕይወት ላለው አገልግሎት ዋስትና ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን የማያቋርጥ እንክብካቤና የገባልንን የማይሻር ቃልና ዓላማ እንዲፈጸም የሚያደርግ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና የአማኞችን አካል የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አድርጎታል (1ኛ ቆሮ. 6፡19)። የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ማደር፥ በዚህ ምድር ላይ ለዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ዓላማ የሚገልጥ ነው። ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ቸል ማለት፥ ወይም የነገሩን እርግጠኛነት ጥያቄ ውስጥ መጣል፥ በክርስትና አጠቃላይ የእምነት ትምህርት ላይ ከፍተኛና አወዛጋቢ ችግር ያስነሣል። እግዚአብሔር በአሁኑ ጊዜ የክርስቲያኖችን አካል ምድራዊ ቤተ መቅደስ የማድረጉ የተባረከ እውነት፥ ለሕይወትና ለአገልግሎት ኃይል እጅግ ጠቃሚ ለሆነ ክርስቲያናዊ ልምምድ ሁሉ ዋና ጉዳይ ነው።

# 17

# የመንፈስ ቅዱስ ማተም

## 1. ማኅተሙ መንፈስ ቅዱስ ነው

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ‘‘በማኅተም’’ አምሳያነት እንደተገለጠ የሚናገሩ ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ (2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ ኤፌ. 1፡13፤ 4፡30)። የነዚህ ክፍሎች አጠቃላይ አሳብ፥ ማተም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን ይገልጣል። ክርስቶስ ራሱ በእግዚአብሔር አብ የታተመ ሲሆን፥ ይህ ሥራ ግን በቀጥታ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ የተገለጠ ነገር የለም (ዮሐ. 6፡27)።

ሁሉም ክፍሎች ግልጥ የሚያደርጉት፥ የማተም ተግባር ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር የሚፈጸም መሆኑን ነው። ክርስቲያንን በሚያበረታታ ሁኔታ ወይም ጥረት አድርጎበት የሚደረስበትም ግብ እንደሆነ ተደርጎ የተገለጠ ነገር አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ባዳናቸው ሰዎች ሕይወት በቸርነቱ የሚፈጽመው ተግባር ነው።

በኤፌሶን 1፡13፤ 4፡30 መሠረት አማኙ የታተመው በመንፈስ ቅዱስ ነው ወይም በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ነው። የዚህ ተግባር ተከታይ የሆነ አንዳችም ነገር የለም። ከ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡22 ልንረዳው የምንችለው፥ ማኅተሙ መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንጂ ሌላ ሊሆን እንደማይችል ነው። እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ በመንፈሱ አማካኝነት በምንም ዓይነት ነገር ውስጥ የማይገኝን እጅግ የከበረ ማኅተም ሰጥቶናል። ይህ ማኅተም የሚያመለክተው ያለቀና የተፈጸመ የውል ስምምነትን ነው። በምዕራፍ ሦስት ውስጥ እንደተመለከትነው ማኅተም ዋስትናን፥ ደኅንነትን፥ ባለቤትነትን፥ ሥልጣንንና ኃላፊነትን ያመለክታል። ማኅተም የተሰጠው በመዋጀት ቀን ከፍጻሜ ለሚደርሰው ነገር ምልክት ሆኖ ነው።

## 2. የመንፈስ ቅዱስ ማተም ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚሆን ድርጊት ነው

የመዋጀትን ማኅተም የሚያካትተው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት፥ በተሳሳተ መንገድ ከደኅንነት ቀጥሎ የሚመጣ የጸጋ አገልግሎት ተደርጎ በመቆጠሩ፥ ሰዎች ለማግኘት ሲመኙትና ሊያገኙትም ሲጥሩ ይታያሉ። ስለ መታተም የሚናገሩትን ሦስት ክፍሎች በጥንቃቄ

በምናጠናበት ጊዜ ግን፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የታተመው በደኅንነቱ ጊዜ እንደሆነ ያረጋግጡልናል። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በርካታ ውድቀቶች ቢኖሩባቸውም፥ በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸው ተገልጧል (2ኛ ቆሮ. 1፡22)። በመንፈስ ቅዱስ የመታተምን በረከት ያገኙት አንዳንድ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው የሚለው አስተሳሰብ ከዚህ አሳብ ጋር ይቃረናል።

ሁለተኛው፥ በኤፌሶን 1፡13 ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የተናገረው ነው፦ "ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ፥ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ።" እዚህ ላይ ሁኔታዎች የተከሠቱበትን ቅደም ተከተል መገንዘብ እንደሚያስፈልግ ይገልጣል፦ ወንጌልን ሰሙ፥ በክርስቶስ አመኑ፥ በመንፈስ ቅዱስ ታተሙ። ይህ ቅደም ተከተል የሚያመለክተው፥ የጊዜን ሁኔታ ሳይሆን፥ በአንዱ አንዱን ከማድረግ የተነሣ የሚመጣ ውጤትን ነው። ጸሐፊው የሚያብራራው፥ በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸው በክርስቶስ የማመናቸው ግልጥ ውጤት እንደነበር ነው። መታተሙ የሚፈጸመውም ልክ ሰዎች በሚያምኑበት ጊዜ ነው።

በኤፌሶን 4፡30 የሚገኘው ሦስተኛ ክፍል የመንፈስ ቅዱስ ማተም ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም ተግባር ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ነው። በዚህ ክፍል፥ "የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ" የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ምክንያቱም በእርሱ የታተምነው በተቤዠንበት ቀን ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ እንደታተሙ ስለሚታመን፥ መንፈስ ቅዱስን እንዳያሳዝኑ የምክር ቃል ተሰጥቷቸዋል። የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም መንፈሳውያን ለሆኑ ብቻ ከሆነ፥ እንደዚህ ያሉትን ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን ስለ ማሳዘን መምከር አስፈላጊ አይደለም። ስለ መታተም የሚገልጡት ጥቅሶች በሙሉ ድርጊቱ በሚያድን እምነት ላይ የተመሠረተና የተፈጸመ ተግባር መሆኑን ያሳያሉ። በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ክርስቲያን በእምነት ሊቀበለው የሚገባ እውነት፥ የእግዚአብሔር ማኅተም የሆነው መንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑንና ለዘላለም በመዋጀት የተለየ ሰው መሆኑን ነው።

## 3. በመንፈስ ቅዱስ መታተም ሕዋሳዊ ልምምድ አይደለም

ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ታተሙ ሲባል፥ ድርጊቱ በሚፈጸምበት የደኅንነት ጊዜም ሆነ በኋላ በሕዋሳቸው የሚገነዘቡት አለመሆኑን በግልጥ ለማየት ይቻላል። የታተሙ ሁሉ እስከ መቤዠት ቀን ድረስ የመታተማቸው እውነት (ኤፌ. 4፡30)፥ ለአንዴና ለመጨረሻ

የሚከናወን ነው። ስለዚህ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ይታተም ዘንድ ሊጸልይም ሆነ ልዩ ልምምድ ሊጠብቅ አይገባውም። ይህ በማይሻረው በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ያለና በእምነት ልንቀበለው የሚገባ አስደናቂ እውነት ነው።

## 4. በመንፈስ ቅዱስ መታተም ቁም ነገር

በመንፈስ ቅዱስ መታተም የሚያመለክተው ታላቅ ነገር የአማኙን የዘላለም ዋስትና ነው። የአማኙ መታተም ከኃጢአት ሙሉ በሙሉ ነጻ እስከሚሆንበት እስከ መቤዥት ቀን ድረስ መጠበቁን የሚያሳይ መሆኑ ግልጥ ነው። ጉዳዩ በሰው እጅ የተተወ ሳይሆን፥ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ኃይል የተደገፈ ነው። የማኅተሙ ባሕርይ ማንኛውንም ተመሳሳይ ወይም አሳሳች ነገር ይከለክላል። የእግዚአብሔርን ባሕርያት ሁሉ የያዘው መንፈስ ቅዱስ ከሁሉ የላቀውና ማለቂያ የሌለው የእግዚአብሔር ሰፊ ጸጋ መግለጫ ነው። እግዚአብሔር በመንፈሱ በአማኙ ውስጥ ሊኖር ተስፋ እንደሰጠ ሁሉ፥ የደኅንነታችን ማኅተም የሆነው መንፈስ ቅዱስም አማኝ ሊኖሩት የሚገባውን ዋስትናዎች ሁሉ በልቡ ውስጥ ያኖራቸዋል።